# 1.ፅኛ. እና 2.ያኛ መጽሐፍ

# የቢ.ቢ.ሲ. (B.B.C.) የጥያቄ ጥበቦችና

# የአባ ተስፋ ሥላሴ የምሥጢር መልስ

1998ዓ.ም



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ
ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወአጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት

# ማስገንዘቢያ፤

ለወገኖችና ለባዕዶች ይህ በጣም ምርምራዊ የሆነ ጥበብ በጥያቄና መልስ ሆኖ የቀረበ አዲስ ጥናት ሲሆን እስከ ዛሬ ድረስ በዓለም ያልቀረበ መሆኑን ጥያቄው በቂ የሆነ ማስረጃ ነው።

ስለዚህ ማንኛውም ምሁር ሰው ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች እንዲተረጉመው ፈቅጃለሁ።

አባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ፤

፲፱፻፹ (1993)

# ምሥጋና

በማንኛውም ነገር ሁሉ ለተባበሩኝና ለረዱኝ ለሚረዱኝ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ፣ እንዲሁም የራማው ቅዱስ ሚካኤልና ቅዱስ ገብርኤል ፣ ቅዱስ ሩፋኤል ማኅበርተኞች በሙሉ፤

በተለይ ደግሞ ይህ በጣም ጥልቅ የሆነ ምርምር የተደረገበት ከቢ.ቢ.ሲ. (B.B.C.) ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ መሠረት የተዘጋጀ፣ የእናት ሀገራችንና የእናት ቤተ ክርስቲያናችንን ጥንታዊና ዘመናዊ የሆነ ታሪክ በሚገባ የሚያስረዳና የሚገልጽ መጽሐፍ በአሁኑ ዘመን ከራሳቸውና ከልጆቻቸው ከወዳጅ ዘመዶቻቸው አፍ ነጥቀው ለሀገራቸውና ለእምነታቸው ለታሪካቸው ቅድሚያ በመስጠት መጽሐፉ እንዲታተም ያደረጉልኝ ምርጥ የእናት ኢትዮጵያ ልጆች በከፊል እንደሚከተለው ናቸው፡-

1. ፩ኛ/ ለክብርት ሙሉነሽ መታፈሪያ ታችበልና ለክቡር ባለቤቷ አቶ ካሳሁን ተፈራ በላቸው፣ እንዲሁም ለክቡራን ልጆቻቸውና ለእናታቸው እማሆይ አስካለ ፈቂ ደማኑ፣
2. ፪ኛ/ ለክብርት መቅደስ ሰይፉና ለክቡር ባለቤቷ አቶ ያፈት ተክለ ብርሃን እንዲሁም ለቤተሰዎቻቸው፣
3. ፫ኛ/ ለክብርት ፍቅሬ ወልደ አማኑኤልና ለክቡር ባለቤቷ ደግሞም ለክቡራን ልጆቿ፣

ዘለዓለማዊ የሆነ የብርሃን አምላክ ቅዱስ መድኃኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በምድርም በሰማይም እንደ ቸርነቱ ብዛት ዋጋቸውን እንዲከፍላቸው እማጸንላቸዋለሁ።

## በማስተባበር ለረዱኝ

1. ለክቡር አቶ በቀለ አሣምነው
2. ለክቡር አቶ ብርሃኑ ሥዩም
3. ለክቡር አቶ ወልዴ ተረዳ
4. ለክቡር አቶ ዳምጠው ዝየሁ
5. ለክቡር አቶ መኮንን ኃይሌ
6. ለክብርት መቅደስ ኃይሌ
7. ለክብርት አዲስ ዓለም ሽታዬ
8. ለክብርት ሣራ ታደሰ

ሕያው እግዚአብሔር ከእነቤተሰዎቻቸው ጭምር እንዲጠብቃቸው እጸልይላቸዋለሁ።

1. እንዲሁም በጣም ምርጥ የሆነ ንጹህ ኢትዮጵያዊ ለሐጉስ አለማየሁ ሜሪላንድ፣
2. ደግሞም ለተመራማሪው ኢትዮጵያዊ መሪ ራስ ኤኤም በላይ የጥንት ኢትዮጵያ ትንሣኤ ደራሲ፣
3. ለኢትዮጵያዊው ወጣት አጥኚ አማረ ፈለቀ ብሻው ኢትዮጵያ የሰው ዘር ምንጭ ናት ደራሲ፣
4. ለዶክተር ተሻለ ለሆነ የአዶናይ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ክሊኒክ ባለቤት፣

አባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ

# <u>የዚህ መጽሐፍ መታሰቢያነቱ፤</u>

ሀ. ለኢትዮጵያዊ ሰማዕት ቅዱስ አቡነ ጴጥሮስ፤

ለ. ለብፁዕ ወቅዱስ ታላቁ አባት ፓትርያርክ አቡነ ባስልዮስ ኢትዮጵያዊ፤

ሐ. ለብፁዕ ወቅዱስ ሰማዕቱ አባቴ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ኢትዮጵያዊ፤

መ. ለብፁዕ ወቅዱስ ባሕታዊ ፓትርያርክ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ኢትዮጵያዊ፤

1. ለኢትዮጵያዊው ተመራማሪ /ሣይንቲስት/ ለነበሩ ለዶ/ክ ኃይለ ጊዮርጊስ ወርቅነህ።

አባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ

፲፱፻፺፰ (1998)

# ለገዝረ አበው ሊቃውንት፤

እንዲሁም ደግሞ በእየገዳማቱና አድባራቱ በእየገጠር አብያተ ቤተ ክርስቲያናቱ ሁሉ ያለ ደመወዝ በነፃ ቤተ ክርስቲያንንና ሕዝብን እየገለገሉ ከ፬፻ እስከ ፱፻ (400 – 900) በላይ ተማሪዎችን ላስተማሩ አባቶች፤

በተለይ ደግሞ የተለያየ ሰባት ዓይነት ቀለም አውጥተው ብራና ፍቀውና ዳምጠው በተለያየ ሥዕልና ሐረግ ያሸበረቁ መጻሕፍቶችን ለጻፉልን፤

እንዲሁም በጣም አስደናቂ የሆኑ በዓለም የማይገኙ በልዩ ልዩ ሐረጉች የተዋቡና ያሸበረቁ መስቀሎችና በጣም ያማረ ቅርጻቅርጽ ያላቸው ቅርሶችን ላቆዩልን አባቶችና ሊቃውንት መታሰቢያ ይሁናቸው።

ልጃቸው አባ ተስፋ ሥላሴ፤



## Title

## From the psalms of David in the Art that shook the World Series.

### The 10 questions from B.B.C.

### የ፲ሩ ቃለ መጠይቆች ከቢ.ቢ.ሲ.

1. How does the Ethiopian Orthodox Church use the psalms? What language are they usually sung in?
2. Are there particular psalms that the Ethiopian Orthodox church regards as important?
3. Does the congregation take part in singing the psalms?
   Do they understand the words When they do so? (the comparison here with parts of Roman Catholic Church where Latin is still used and the congregation do not know what they're listening to.)
4. How old is the Ethiopian Orthodox Church? How far back in time do its traditions and history extend?
5. What is the story of the Lalibela Churches? How were they built, who by, and when?

6. What does the Ethiopian Orthodox Church thinks of the Rastafarian vision of Haile Selassie? Do you agree with, or share, any elements of Rastafarian belief?
7. How would the Ethiopian Orthodox Church describe the Linage and Image of the Haile Selassie? Was he, in your view, a descendant of Solomon and Sheba?
8. Ethiopia has proved hospitable to many religions the Beta Israel, the Rastafarians, and of course your own church.
9. Why do you think Ethiopia has proved to be such a special place?
10. Where is the Promised Land?

By Tony Hicky,
Ethiopia Village General Manager
1993 (፲፱፻፺፫ ዓ.ም)
The Ethiopic translation of these, questions
by Abba Tesfa Selassie Moges
see next page.



## አንደኛ መጽሐፍ
## አርእስት
# የቢ.ቢ.ሲ (B.B.C) የጥያቄ ጥበቦችና የአባ ተስፋ ሥላሴ የምሥጢር መልስ፤

1.ፊ. የቢ.ቢ.ሲ. (B.B.C.) ቃለ መጠይቆች፣ስለ አሥሩ ጥያቄዎች፣ ከመዝሙረ ዳዊት ውስጥ ይኸው ዓለምን በእርግጥ ያንቀጠቀጠ ሥነ ጥበብ /አርት/ በሚል ርዕስ የቀረበ በቶኒ ሂኪ፣ 01/11ኛ/ ያገሥት 2ሺ.1/2001/ትርጉም በአባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ፣

## ክፍል ፩/1/

1.ሀ. የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን መዝሙረ ዳዊትን እንዴት ትጠቀማለች? በምንስ ቋንቋ ነው የምትዘምረው?

2.ለ. የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከዳዊት መዝሙር ውስጥ በጣም ጠቃሚ የሆኑና የተለዩ የምትጸልያቸው አሉ?

3.ሐ. ሕዝቡ መዝሙረ ዳዊት በሚዘመርበት ጊዜ አብረው ይዘምራሉ? የሚዘምሩትስ ቃሉ ምን እንደሚል ይገባቸዋል? /ለምሳሌ ያህል ከዚህ ላይ የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያንን የመሰድን

እንደሆነ እስከ ዛሬ ድረስ የላቲን ቋንቋ እየተጠቀመች ነው ነገር ግን ሕዝቡም ዘማሪዎቹም ቃሉ ምን እንደሚል አይገባቸውም /እናንተስ እንደነሱ ናችሁ?/

## ክፍል ፪/2/

4.መ. የኢትዮጵያ ተዋሕዶ አርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ዘመኗ ስንት ነው? ወደኋላ ተመልሰ በጊዜ ሰተነተን ምን ያህል ይርቃል? ሲያያዝ የመጣው ታሪኳስ ምን ያህል ይረዝማል?

5.ሠ. የቅዳሰ ላሊበላ ቤተክርስቲያኖች ታሪክ ምንድን ነው? እንዴት ተሠሩ? በማንስ እጅ? መቼ?

6.ረ. የኢትዮጵያ ተዋሕዶ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ስለ ራስ ተፈሪያን በኃይለ ሥላሴ ላይ ያላቸው ራዕይ? ምን ታስባለች? ትስማማለች እነርሱ ከሚያምኑትስ የምትጋራው ነገር አለ?





## ክፍል ፫/3/

7.ሰ. የኢትዮጵያ ተዋሕዶ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የኃይለ ሥላሴ ሥርወ መንግሥት አመጣጥ እንዴት ነው የምትገልጸው? እሱ በታሪካችሁ ውስጥ ከሰሎሞንና ከሳባ ሲያያዝ የመጣ ነው ብላችሁ ታምናላችሁ?

8.ሸ. ኢትዮጵያ የብዙ ሃይማኖት መጠጊያ እንደ ሆነች ይገመታል? ከእነዚህም ውስጥ ቤተ እሥራኤል ራስ ተፈሪያን በእርግጥ የአንተ ቤተ ክርስቲያን?

9.ቀ. ኢትዮጵያ የተለየች ሀገር መሆኗ ተረጋግጧል፤ ስለዚህ አንተ ምን ትላለህ?

10.በ. የቃል ኪዳን ሀገር ወዴት ነው?

ተርጓሚ አባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ፤

፪ሺ፩ (2001)

## ማሳሰብያ፤

ከዚህ በላይ የቀረቡልኝ ፲(10) ጥያቄዎች ፈረንጆች ስለ እናት ኢትዮጵያ ለማወቅ ምን ያህል ጉጉትና ፍላጉት እንዳደረባቸው የሚያስረዱ ናቸው።

ቢሆንም ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ እንዲረዱት ለማድረግ የእንግሊዝኛውን ጥያቄ አብሮ ከማስቀመጥ ቃል በቃል ወደ ኢትዮጵያዊኛ (አማርኛ) የተረጐምኩት መሆኑን በአክብሮት አሳስባለሁ።

አባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ፤

፲፱፻፺፫ (1993)





## አርእስት

2.፪. ስለ /፲ሩ/ /10/ ጥያቄዎች እና ሌሎች በጣም ጠቃሚ የሆኑ የቃል ጥያቄዎች ጭምር የተሰጠ መልስ፤ የካቲት ፪-፮ /2-6/፤ ፩ሺ፱፻፺፫ /1993/ አዲስ አበባ
በአባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ

ማውጫ

ክፍል ፩ /1/

ሀ. የኢትዮጵያ ተዋሕዶና መዝሙረ ዳዊት፤

መግቢያ እውነት ምንድን ነው? ------- ፲፩/ 11

አጭር የሆነ መቅድም ---------- ፲፭/ 15

A. To her Excellency ..... ፲፰/ 18

1.ሀ. የጥያቄ አንድ መልስ ቁጥር 1 ..... ፲፱/ 19

2.ለ. የጥያቄ ሁለት መልስ ቁጥር 2 ..... ፳፩/ 21

3.ሐ. የጥያቄ ሦስት መልስ ቁጥር 3 ..... ፳፫/ 23

4.መ. የጥያቄ አራት መልስ ቁጥር 4 ..... ፳፬/ 24

## ክፍል ፪/2/

### ለ. በይበልጥ ታሪኩን ግልጽ ለማድረግ፤

1. ድንቅነሽ /ሉሲ/ አዳምና ሔዋን ..... ፴፯/ 37
2. ጤፍ የኤደን ምርጥ ተክል ነው ..... ፵፪/ 42
3. ጤፍ ከምግብነት ሌላ ምን ይሆናል.... ፵፮/ 46
4. ታሪካዊ የሆኑ ሄኖኮች ሦስት ናቸው ...፵፱/ 49

## ክፍል ፫/3/

### ሐ. እውነትን ለማወቅ ለሚፈልጉ ሁሉ፤

5.ሠ. የጥያቄ አምስት መልስ ቁጥር 5 ..... ፶፬/ 54
6.ረ. የጥያቄ ስድስት መልስ ቁጥር 6 ..... ፷፬/ 64
7.ሰ. የጥያቄ ሰባት መልስ ቁጥር 7 ..... ፷፱/ 69
8.ሸ. የጥያቄ ስምንት መልስ ቁጥር 8 ..... ፸፭/ 75
9.ቀ. የጥያቄ ዘጠኝ መልስ ቁጥር 9 ..... ፸፰/ 78
10.በ. የጥያቄ አሥር መልስ ቁጥር 10 ..... ፹፩/ 81





## ክፍል ፬/4/

### መ. አጭር የታሪክ መልስና እምነት ምሥጋና፤ በግና በኢትዮጵያ፤

1.ሀ. ቅዱስ ዳዊትና በግናው ..... ፺፩/ 91
2.ለ. አጭር የእምነት ርዕስ በኢትዮጵያዊኛ... ፻፭/ 105
2.B. Short Title Of Faith In English ..... ፻፮/ 106
3.ሐ. አጭር መልስ ለኢ.ኤ.ዋሊስ.ባጅ.....፻፯/ 107
3.C. A short answer for E.A. Wallis Budge ..፻፲፩/ 111
4.ሠ. አጭር ምስጋና ከቢ.ቢ.ሲ. ..... ፻፲፬/ 114
5.ረ. ስለ ሰብአ ሰገል ..... ፻፲፭/ 115
6.ሰ. ማስረጃ ዋቢ ወይም ቢብልዮግራፊ በጥናቱ ውስጥ አብሮ የገባ መሆኑን አሳስባለሁ።

# ኦርእስት፤
# አንደኛ መጽሐፍ፤
# የቢ.ቢ.ሲ. (B.B.C.) የጥያቄ ጥበቦችና፤
# የአባ ተስፋ ሥላሴ የምሥጢር መልስ፤
# የሥዕሎች ማውጫ፤


የውጭ ሽፋን የታቦተ ጽዮን በመሐል ኢትዮጵያ የመጀመሪያ ምስል፤ ----------

1. የታቦተ ጽዮን 1ኛ በመሐል ኢትዮጵያ የውጭ ሽፋን እንደገና በመጽሐፉ የመጀመሪያ ገጽ፤ ------- ገጽ:24
2. የታቦተ ጽዮን 2ኛ ምስል በላዕላይ ግብጽ /ምሥር/፤–
3. ተዓምረኛዋ ዐይን ባለቀስተ ደመና በቶ ፊደል ውስጥ ያለበት አንበሳ፤ ----------
4. የደራሲው ምስል ወይም ፎቶግራፍ፤ ---------- ገጽ:24
5. የድንቅነሽ /ሉሲ/ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ምስል፤
6. ተዓምረኛዋ ዐይን በቶ ፊደል ላይ በሰንደቁ ሙሉ አንበሳ ያለበት፤ ---------- ገጽ:37
7. የእመብርሃን ሥዕል ስለ ሰብዓ ሰገል በ2ኛው መጽሐፍ ሽፋን ላይ፤ ----------
8. የአዳምና ሔዋን ምስል እንደገና በ2ኛው መጽሐፍ ላይ፤ ---------- ገጽ:115






# ክፍል ፩/1/

## ሀ. የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶና መዝሙረ ዳዊት፤

## መግቢያ እውነት ምንድን ነው?

የዓለም ብርሃንና የእውነት አምላክ የሆነ መድኃኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ወደ ፍርድ ሸንጎ ሲቀርብ እኔ ስለ እውነት ልመሰክር ነው የመጣሁት በማለቱ፤ ፈራጁ ጲላጦስም ስለጨነቀው እውነት ምንድን ነው? ብሎ መጠየቅ ተገደ ነበር፤ ዮሐ.ም ፲፰፤ቁ.፴፯-፴፱ /18፤37-39/ ስለዚህ በዚህ ዓለም ውስጥ እውነት የሚመስሉና የሚያስመስሉ ብዙ ሐሰቶች እና ሐሰተኞች ስለሚገኙ፤ አብዛኛው የዓለም ሕዝብ እውነቱን ከሐሰቱ መለየት እንደተቸገረ አይካድም።

ምክንያቱም በአሁኑ ዘመን በዓለም ውስጥ ዛሬ በሬድዮ የሚሰማውና በቴሌቪዥን የሚታየው እንዲሁም በዜና /በጋዜጣና/ በመጽሔት በመጽሐፍ የሚጻፈው፤ ደግሞም ሰው የሚነጋገረው ሁሉ

የማይታመን፤ እውነት መሳይ የዘመኑ ጉግማንጉግ ስለሆነባቸው ነው፤ የእውነት ሰዎች እውነትን ፍለጋ ከባሕር ማዶ አገር አቋራጭ የሆነ ምድር ተነስተው የተለያዩ የዓለም ምሁራንን በመጠየቅ ከለቃውንቱ ሁሉ ያገኙትን ውጤት እራሱ በራሱ እያንዳንዱ የዓለም ሕዝብ ሁሉ በዓይኑ ተመልክቶ በማነጻጸር እንዲረዳ በማለት በቪዲዮ ቀርጾው ለአየር ስላበቁት አደንቃቸዋለሁ፤ ሕያው እግዚአብሔርም እውነተኞችን በማስነሳቱ የተመሰገነ ነው።

## A.ሀ. በቢል ሉኬ መሪነት፤

ይሁን እንጂ እውነትን ፍለጋ ከቢ.ቢ.ሲ.(B.B.C.) ስኮትላንድ ተነስተውና ብዙ ገንዘብ አውጥተው ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ስለ ሰብአ ሠገሌች በኖቬምበር ፲፰፤፲፱፻፺፮ ዓ.ም. 18፤1996 እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር በቢል ሉኬ መሪነት የወጣቶች ዝግጅት በማይ ርዕስ ጠይቀው የቀረጹትን እውነት የሆነ ታሪካዊ የቪዲዮ ካሴት ለዓለም ሕዝብ በሲኤን ኤን (በCNN) ታይቶ ነበር፤ ስለዚህ በጣም





የሚያስገርም እና የሚያስደንቅ በሥዕል የተደገፈ እንደነበር አይካድም።

## B.ለ. በፕሮፌሰር ጀርማይኔ ግሪር መሪነት፤

ከዚህ በላይ በአጭሩ ሆኖ የተገለጸው የቢ.ቢ.ሲ. የወጣቶች ዝግጅት የተመለከተ፤ ነገሩ ሁሉ እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ አሁንም በድጋሚ ሌላ ፪ኛ/2ኛ/ የጥናት ቡድን፤ እውነት ፍለጋ ከቢ.ቢ.ሲ. (B.B.C) ስኮትላንድ ተነስቶ ከዳዊት መዝሙር ውስጥ የተውጣጣና በተለያየ ሁኔታ የቀረበ ቃለ መጠይቅ በመያዝ?

ይኸውም በእውነት ዓለምን ያንቀጠቀጠ አርት በሚል ርዕስ፤ በፕሮፌሰር ጀርማይኔ ግሪርና፤ በጆአን ራባ የሚመራ ፯/7/ አባላት ያለው አጥኚ ቡድን፤ ከስኮትላንድ ተነስቶ በ፲፩ኛ /11ኛ/ ያገስት በ፪ሺ፩ /2001/ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደገባ ካሜራውን /መጽሔተ አሚኑን/ አነጣጥሮ የሚፈልገውን እውነት አግኝቶ በመቅረጽ እውነቱን በሲኤን ኤን

/በCNN/ በማስተላለፍ ለአየር አብቅቶታል፤ ያየና የሰማ እውነቱን ይመስክር በማለት ነበር ሁለቱም የቢ.ቢ.ሲ. የጥናትና የምርምር ቡድኖች ያረጋገጡት። ስለዚህ እውነቱን ለዓለም ህዝብ ስለአስተዋወቁት መለኮታዊ አምላክ ረድኤ እድሜ እንዲሰጣቸው እመኛለሁ።

ይሁን እንጂ ከዚህ በላይ በአጭሩ ሆኖ እንደገለጽኩት ሁሉ፤ ሁለቱም የቢ.ቢ.ሲ /B.B.C/ የታሪክ ተመራማሪዎች ቡድን ጥያቄውን ያቀረቡልኝ በእንግሊዝኛ ሆኖ መልሱንም በእንግሊዝኛ እየሰጠሁ በቪዲዮ ተቀርፆ በሲኤን ኤን (በCNN) የተላለፈ ቢሆንም በይበልጥ ግልጽ ለማድረግ የ፲ሩ/10/ ጥያቄዎች <u>አንደኛ</u> መጽሐፍ እንዲሁም የ፱ኩ/4/ ጥያቄዎች ደግሞ <u>ሁለተኛ</u> መጽሐፍ በማድረግ በጽሑፍ በአንድ ላይ ማቅረቤን በትህትና አሳስባለሁ።

አባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ

ዕሸ፱የ፯ር-ዕሸ፱የ፲፮ /1995-1996/





# <u>አጭር የሆነ መቅድም</u>

ይሁን እንጂ ይህ ምርምራዊና ታሪካዊ የሆነ ጥናት አዘጋጅቼ እንዳቀርብ ምክንያት የሆነኝ፤ አስቀድሜ ከላይ በመግቢያው እውነት ምንድን ነው፤ በሚል በአጭሩ እንደጠቀስኩት ሁሉ በቢል ሎኬ (Bill Lokea) መሪነት ከቢ.ቢ.ሲ. (B.B.C.) ቴሌቪዥን የወጣቶች ዝግጅት በሚል ርዕስ፤ ስለ ሦስቱ ሰብአ ሰገሎች (About the three wise men) እነማን ነበሩ በማለት ላቀረቡልኝ በጣም ታሪካዊ የሆነ ቃለ መጠይቅ በቪዲዮ ካሴት እየተቀረፀ የሰጠሁት በሥዕል የተደገፈ አጭር ማብራርያና ገለፃ ከቢ.ቢ.ሲ በሲኤን ኤን (በCNN) እና በኢንተርኔት የዓለም ሕዝብ እንዲያውቀው መተላለፉን የተረጋገጠ እውነት ነው፤ ይህም ታሪካዊ የሆነ ንግግር በጽሑፍ ተዘጋጅቶ ፪ኛ/2/ መጽሐፍ ሆኖ ሙሉ የሆነ ታሪኩን ለማስረዳት ከዚህ ጋር የቀረበ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ በድጋሚ እገልፃለሁ።

ቢሆንም ከዚህ በላይ እንደ መንደርደሪያ ሆኖ በአጭሩ የተገለጸውን ታሪክ የተመለከተ የቢ.ቢ.ሲ. (B.B.C.) የታሪክ ማህደርና ተመራማሪ የሆነ ቡድን ከዳዊት መዝሙር ውስጥ ይኸውም በእውነት ዓለምን ያንቀጠቀጠ ጥበብ፤ (From the psalms of David in the Art that shook the world series.) በሚል ርዕስ በፕሮፌሰር ጀርማይኔ ግሪር (Professor Germaine Greer.) የሚመራ ቡድን ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣቱ በፊት፤

በእናት ኢትዮጵያ ውስጥ ለብዙ አመታት የተቀመጠና የኢትዮጵያ መንደሮች (Village Ethiopia) ለሚባል ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ የሆነ ቶኒ ሂኪ (Tony Hickey) በሚባለው ወኪላቸው አማካኝነት በዚህ ታሪካዊ የሆነ ጥናት ውስጥ የተጠቀሱት ፲/10/ ጥያቄዎች አስቀድመው ተልከውልኝ እኔም በሚገባ አብራርቼ ለወኪላቸው መልስ ከሰጠሁኝ በኋላ ነው፤

ከላይ እንደተገለፀው ሁሉ በፕሮፌሰሯ የሚመራ ፯/7/ አባላት ያለው ቡድን ከቢ.ቢ.ሲ ስኮትላንድ ተነስቶ





ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ሁለት ሰዓት ተኩል የሆነ የቪዲዮ ፊልም በቃለ መጠይቆቹ መሠረትና ሌሎችም የቃል ጥያቄ ሳይቀር መቀረፃቸው የተረጋገጠ ሲሆን፤ .

እንዲሁም ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ የእኔ ልጅ የሆነ የበገና ሊቅ አቶ ዓለሙ አጋ ተመሳሳይ የሆነ ጥያቄ ተጠይቆ በጣም አጥጋቢ መልስ መስጠቱን እውነት ነው፤

ደግሞም ሦስተኛ ከኢትዮጵያ ተጠያቂዎች የሆኑት በአቶ ይታገሥ ኪንግና በአቶ ቶኒ ሂኪ መሪነት በሻሸመኔ የሚኖሩ የራስ ተፈሪያን ሽማግሌዎች ተጠይቀው ለሚያምኑበት ከበቂ በላይ የሆነ መልስ መስጠታቸው በአየር ላይ የታየው የቪዲዮ ክር እንደሚያስረዳ አይታበልም።

ይሁን እንጂ የቢ.ቢ.ሲ (B.B.C.) የታሪክ ተመራማሪዎች ከኢትዮጵያና ከሌሎች የተለያዩ ሀገሮች ሃይማኖታዊ እና ታሪካዊ የሆነ ከተለያዩ ሊቃውንቶች ጠይቀው የቀረፁትን ታሪክ አንኳር አንኳሩን መርጠው አንዱን ከሌላው ጋር በማነፃፀር የዓለም ሕዝብ እንዲያውቀው በማድረጋቸው በራሴና በሌሎቹ ስም በመሆን ከልብ በአመሰግናቸዋለሁ።

# ለክብርት ፤ (To her Excellency)

A. Professor Germain Greer she is absolutely loves Ethiopia and Ethiopians. Also she loves the Ethiopian straight Tewahido (Orthodox) church.

Because of this the chosen Ethiopians we love her too.

B. Also I wanted very diply in heart to thank the production manager the psalms of David, very clever Joan Raba.

I wish for them, and for all the membership of the B.B.C. Television; long live by the name of ours savior eternal God Jesus Christ, Forever.

By Abba Tesfa Selassie Moges.





## 1.ሀ. የጥያቄ አንድ መልስ ቁጥር ፩/1/

የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን መዝሙረ ዳዊት እንዴት እንደምትጠቀምበት ለመግለጽ አስቸጋሪ ቢሆንም፤ ጠቅለል ባለ መልኩ መዝሙረ ዳዊት ለእናት ኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እንደመሠረት እና ግድግዳ ጣራ ሆኖ የሚያገለግል ከመሆኑም በላይ የሰው ሁሉ የደም ምንጭ የልብ ትርታ እንደሆነ የታወቀ ነው።

እንደዚሁም ደግሞ መዝሙረ ዳዊት በቤተክርስቲያኗ ስነ ሥርዓት ሁሉ እንደ ደም ዝውውር የማይገባበት ቦታ በፍጹም አይገኝም፤ ለምሳሌ ያህል የሹቱ /5/ ጽዋትወ ዜማዎች መሠረታቸው ቅዱስ ዳዊት ነው።

እንዲሁም በሰዓታት፤ በስብሐተ ነግሁ፤ በቅዳሴው፤ በጸሎተ ፍትሐቱ፤ በግል ጸሎቱ፤ የዚህ ሁሉ ምንጩና መሠረቱ መዝሙረ ዳዊት ሲሆን፤ የእናት ኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ዳዊትን የምትጸልየው እና የምታዜመው ወይም የምትዘምረው በግዕዝ ነው።

በሆነም ዳዊት ለኢትዮጵያውያን ከፈጣሪያቸው ጋር የሚያገናኝ የልብ ትርታ ስለሆነ በማዕዘና በኢትዮጵያዊኛ /በአማርኛ/ ዘወትር ያለማቋረጥ ይጸልዩታል።

ይሁን እንጂ የጸሎቱ ስነ ሥርዓት በይበልጥ ተግባራዊ የሚሆነው ደግሞ በየገዳማቱ ለጸሎት ብቻ የተመደቡ አባቶች ፩፻፶(150) መዝሙረ ዳዊት በሙሉ በቀን ሲጸልዩት ፩፻፶(150) ተረፈ ዳዊት ደግሞ በሌሊት እንደሚጸልዩት በማንም ሰው ዘንድ የተረጋገጠ ነው።

ይህም የዳዊቱን አርኬ ወይም ግጥም ሳይጨምር መሆኑን አይታበልም፤ ማለትም መዝሙረ ዳዊትና ተረፈ ዳዊት ከአርኬ ግጥሙ ጋር ፬፻፶/450/ ሲሆን፤ በተለይ ደግሞ በአብይ ፆም በየአመቱ በአድባራት እና በገዳማት ሁሉ መዝሙረ ዳዊትን ከላይ እንደተብራራው ከሹቱ /5/ ጽዋትወ ዜማዎች ጋር በማዋሐድ በአማረ ያሬዳዊ ዝማሜ ያለከበሮና ጸናጽል በየቀኑ በዝማሜ እንደሚዘመርና እንደሚጸለይ የተረጋገጠ ነው።





## 2.ለ. <u>የጥያቄ ሁለት መልስ ቁጥር ፪/2/</u>

አዎ የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከዳዊት መዝሙር ውስጥ የተወሰኑ ሊቃውንቶች ብቻ የሚያውቋቸው ሀገርንና እምነትን ለመጠበቅና እንዲሁም ለሕዝብ፣ ለግለሰብ የሚጸለዩና በጣም ጠቃሚ የሆኑ መዝሙሮች እንዳሉ የታወቀና የተረጋገጠ የማይካድ እውነት ነው ካልኩኝ በኋላ።

እንደገና ሀገራችሁንና ሕዝባችሁን የሚጠብቅ የምትጸልዩት ከዳዊት መዝሙር ካለ? ለምን ጣልያኖች ወረሯችሁ? ተብሎ ለቀረበው የቃል ጥያቄ መልስ ደግሞ፤

ጣልያኖችማ በአባቶቻችን ጸሎት በሕያው እግዚአብሔር ትእዛዝ እንደፈረስና በቅሎ በልጓም ተጐትተውና ተገደው የኢትዮጵያውያን ባርያ በመሆን ቅኝ ግዛት እናደርጋለን በሚል ሽፋን ኢትዮጵያን በመንገድ ለማገናኘት ነው የመጡት እንጂ ሀገርን ለመውረር አይደለም የሚል ሲሆን፤ ሌላውን በጣም ብዙ የሆነውን ትቼ በአጭሩ

ልጠቅስ የምፈልገው ለምሣሌ ያህል ጣልያኖች ባሪያ ሆነው ከሠሩዋቸው ጥቂቶቹን እጠቅሳለሁ፤ ይኸውም የአምባ አላጌ፤ የአላማጣ፤ የጣርማ በር፤ የለ.ማለ.ሞ፤ እነዚህ በቂ የሆኑ ማስረጃዎች ናቸው።

እነዚህ መንገዶች ጣሊያኖች ለጊዜው ለጥቅማቸው ሲሉ የገነቧቸው ቢሆንም ለዘለቄታው ደግሞ ለእናት ኢትዮጵያ በጣም ጠቃሚ እንደሆኑ የማይታበል እውነት ነው። ስለዚህ ሕያው አምላክ ይመስገን። አሜን።

ኢጣልያኖች ብዙ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ፈጅተው የለም ወይ! የሚል ጥያቄ ቢነሳ፤ ጣሊያኖች ሥራ ሠርተው ራሳቸውም እየሞቱ ከገደሏቸው ኢትዮጵያውያን ይልቅ ያለ ምንም ሥራ ለግል ሥልጣናቸውና ክብራቸው ብቻ ሲሉ በእየጊዜው የተነሱ የኢትዮጵያ አምባገነን የሆኑ መሪዎችና ዲክታተሮች የገደሏቸውና የሚገድሏቸው ወገኖቻችን በሰባት እጅ ይበልጣሉ የሚል ይሆናል መልሱ እስከ ዛሬ ድረስም በመግደል ላይ እንደሆኑ አይካድም እውነት ነው።





## 3.ሐ. <u>የጥያቄ ሦስት መልስ፤ ቁጥር ፫/3/</u>

አምን የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ከሕፃናት በስተቀር የቅዳሴው ሥነ ሥርዓት በሙሉና መዝሙረ ዳዊትም በሚዘመርበት ጊዜ ሁሉ ከካህናቱ ጋር አብረው በመሳተፍ ይዘምራሉ፤ ቃላቱም ምን እንደሚል ይገባቸዋል፤

የሚጸልዩትም መዝሙረ ዳዊት ነው፤ ለምሳሌ የህል በቅንፍ ውስጥ እንደተጠቀሰው እንደ ሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ምዕመናን የላቲን ቋንቋ እንደማይገባቸው አይደሉም።

በዚሁም ላይ ግዕዝ የሕያው አምላክና የአዳም የሰማይ መላእክት ቋንቋ በመሆኑ እንኪንስ ኢትዮጵያዊ የሆነ ፍጹም ሰው ይቅርና ለይምሰል ሰው ብቻ ማለትም ደመነፍስ የሆነ ሳይሆን በትክክል ሕያዊት የሆነች ደመነፍስ የተወሐደችው ፍጹም የሆነ ሰው ሁሉ የግዕዝን ቋንቋ እንደሚሰማ የተረጋገጠ ነው እላለሁ።

ግዕዝ ማለት በሰብአ ቋንቋም፣ በአረማይስጥም፣ በራሱ በግዕዝም የመጀመሪያ አንደኛ ቀዳማዊ ነው፤ ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ የተረጋገጠ ነው፣ በዘፍጥረትና በመጽሐፈ ኩፋሌ ይመልከቱ፤ ምሥጢረ ካህናት ዘአዶናይ ራፋኤልም፣ ከሰብአ ቋንቋ አረማይስጥ መጣ፤ ግዕዝ ደግሞ የተሻሻለው አረማይስጥ መሆኑን ያረጋግጣል።

## 4.መ. <u>የጥያቄ አራት መልስ፣ ቁጥር ፬/4/</u>

ሀ. ቀጥተኛዋ ተዋሕዶ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በመሐል ኢትዮጵያ በሚገኘው በአክሰደናቂው የአማልክት ሕንፃ በካራን ቤተ መቅደስ፣ በሺሺ፬የ፯ /5450/ ከ.ፌ./B.C/ <u>ለመጀመሪያ</u> ጊዜ የተመሠረተ ሲሆን፣

ለ. እንዲሁም ደግሞ <u>ለሁለተኛ</u> ጊዜ ከ፫ሺ፬የ፯ /3950/ ከክርስቶስ ልደት በፊት ጀምሮ በላዕላይ ምሥር /ግብጽ/ በሚገኘው የጥንት ኢትዮጵያ በነበረውም የአምልኮተ ፀሐይ በሚመለክበት ፕራሚድ ውስጥ ጭምር ነው።






ግዕዝ ማለት በሰብአ ቋንቋም፤ በአረማይስጥም፤ በራሱ በግዕዝም የመጀመሪያ አንደኛ ቀዳማዊ ነው፤ ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ የተረጋገጠ ነው፤ በዘፍጥረትና በመጽሐፈ ኩፋሌ ይመልከቱ፤ ምሥጢረ ካህናት ዘአዶናይ ራፋኤልም፤ ከሰብአ ቋንቋ አረማይስጥ መጣ፤ ግዕዝ ደግሞ የተሻሻለው አረማይስጥ መሆኑን ያረጋግጣል።

4.መ. **<u>የጥያቄ አራት መልስ፤ ቁጥር ፬/4/</u>**

ሀ. ቀጥተኛዋ ተዋሕዶ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በመሐል ኢትዮጵያ በሚገኘው በአስደናቂው የአማልክት ሕንፃ በካራን ቤተ መቅደስ፤ በ፳፻፬፻፺ /5450/ ከ.ፌ./B.C/ <u>ለመጀመሪያ</u> ጊዜ የተመሠረተ ሲሆን፤

ለ. እንዲሁም ደግሞ <u>ለሁለተኛ</u> ጊዜ ከ፲፻፱፻፺ /3950/ ከክርስቶስ ልደት በፊት ጀምሮ በላዕላይ ምሥር /ግብጽ/ በሚገኘው የጥንት ኢትዮጵያ በነበረውም የአምልኮተ ፀሐይ በሚመለክበት ፕራሚድ ውስጥ ጭምር ነው።






የመጽሐፉ ደራሲ
አባ ተስፋ ስላሴ ሞገስ



አባ ተስፋ ሥላሴ ከመጻሕፍቶቻቸው ጋር፣
Father Tesfa Selassie with his books



ፅ.፩. ፩ኛው የታቦተ ጽዮን ምስል በመሐል ኢትዮጵያ፣ በካራን የፀሐይ አምላክ ቤተ መቅደስ ውስጥ፣ በ፭ሺ፱፻፶ (5950) ከ.ፌ. (B.C.)

፩.1. The 1st Symbol the Ark of Zion in the middle Ethiopia in Karan the temple of Sun God. 5950. (፭ሺ፱፻፶) ከ.ፌ. (B.C.)



2.፪. ፪ኛው የታቦተ ጽዮን ምስል ደግሞ የጥንት ኢትዮጵያ በላዕላይ ግብጽ የፀሐይ አምላክ ቤተ መቅደስ ውስጥ በ፫ሺ፱፻፶. (3950.) ከ.ፌ. (B.C.)

፪.2. The 2nd Symbol the Ark of Zion, also the Ancient Ethiopia in Upper Egypt the Temple of Sun God. 3950. (፫ሺ፱፻፶.) B.C. (ከ.ፌ.)



በነዚህ የሕያው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደሶች የሆኑ ፕራሚዶች ውስጥ በስተምሥራቅ በግርግዳው ላይ ከአልማዝና ከዕንቁ ከእምራልድና ከወርቅ በተለያዩ የድንጋይ ማዕድኖችና ፈርሞች በሂሮግሊፊክ ጽሑፍ የተዋበ ፮/6/ ሜትር ቁመትና ፬/4/ ሜትር ስፋት የሆነ፤ ከታች የ፪ት/2/ ሴት አንበሳ ቅርጽ ያለበት ሲሆን፤ ከላይ ጨረሮቹ ሜፋቸው የሰው ጣቶች የሆኑ መሐሉ የሕይወት ምስልና ምልክት የሆነ ክርስቶስን የሚወክል "ቶ" ፊደል ያለበት ሀሐይ ነው፤

እንደገና መሀል ለመሀሉ ደግሞ በአልማዝና በዕንቁ በእምራልድና በወርቅ ያሸበረቁ እናትና ልጅ የሆኑ ቀለማቸው የወይን ፍሬ የሚመስል በጣም የሚያማምሩ የ፪ት/2/ ጠያይም ኢትዮጵያውያን ሴቶች የምስል ሥዕል አለበት፤

ይህም በትንቢቱ መሠረት <u>የመጀመሪያው</u> የታቦተ ጽዮን ምሳሌ እንደነበረና እንደሆነ የማይካድ እውነታ ነው፤

መጽሐፈ ሚስጢር ዘአዶናይ ራፋኤል በሚገባ ያብራራል፤ ይህ አስገራሚና አስደናቂ የሆነ፤ በጣም በሚያምር የተለያዩ የድንጋይ ፈርጠች /ሞሳይክ/ ተገጣጥሞ የተሠራ የእናትና ልጅ ሥዕል ወይም ምስል፤ በሰው እጅ እንዳልተሠራ መጽሐፈ ምስጢር በድጋሚ ያስረዳል።

ይሁን እንጂ በዚህ ዓለም ውስጥ ሁሉን እናውቃለን የሚሉ ክፍሎች አሉ፤ እነዚህም ጠንቋዮችና ሐኪሞች ጥቂት የታሪክ ጸሐፊዎችና ብዙ የፖለቲካ ሰዎች ሲሆኑ፤ በዚህ ዓለም ውስጥ አናውቀውም የሚሉት ነገር በፍጹም የላቸውም።

ለሁሉም ነገር አዲስ የሆነ ስም እንደሰጡ የሚኖሩ የለየላቸው የሰይጣን ቁራጮች እንደሆኑ አይካድም፤ ቢሆንም ከዚህ በላይ ጀምሮ ታሪኩ የተገለጸው የ፪ት/2/ ሴቶች የሥዕል ቅርጽ <u>ቱታንክሐሜንና</u> <u>ነፈርትቲ</u> ናቸው በማለት ብዙዎችን አደናግረዋል፤ ቱታንክሐሜንና ነፈርትቲ ኢትዮጵያውያን ቢሆኑም፤ ነገር ግን የነበሩበት ዘመን በጣም የተራራቀ ነው፤ በአንድ ጊዜ አልነበሩም፤





ማለትም ቱታንክሐሜን በ፩፹፱፻፶ (1950) ከ.ፌ. (B.C.) የነበረች ሲሆን፤ ነፈርትቲ ደግሞ በ፩፹፲፳፩ (1821) ከ.ፌ. (B.C.) ነው፤ ስለዚህ አንተስ ማን ነህ የሚል ጥያቄ ቢነሳም ትክክለኛው ታሪክ ግን በዚህ ጥናት ውስጥ የተገለጸው መሆኑን አረጋግጣለሁ።

በእውነትም እንኳንስ በዚያ ዘመን ይቅርና በአሁኑ ዘመንም ቢሆን መሥራት የማይቻል የጥበብ ምሥጢር መሆኑን ሥራው ይመሰክራል።

የ፪ት/2/ ሴቶች ሁኔታ በሥዕሉ ሲታይ ጎብሩን ለመግለጽ በጣም አስቸጋሪ ቢሆንም በመጠኑ እሞክራለሁ።

መሀከለኛ እድሜ ያላት ሴት የቆመች ስትሆን፤ ወጣቷ ሴት ልጅ ደግሞ ሥራው ግሩም የሆነ እግሩ በእምራልድ በተሠራ ወንበር ላይ ተቀምጣለች፤ ትልቋ ሴት በቀኝ እጇ የልጅቱን፤ የግራ ትክሻ ይዛ የምታነጋግራትና የምትኪኩላት የምትመስል ሲሆን፤ በራሷ ላይ ያደረገችው ዘውድ ፩ድ/1/ የወይን ፍሬና የስንዴ ዘለላ ያለበት ሆኖ በእምራልድ በአልማዝና በዉርቅ ያሸበረቀ ነው።

ይህም የምስሉን ሥዕል በዓይን ለሚያዩ በይበልጥ እንደሚገባቸው አምናለሁ።

የተቀመጠችው ሴት ልጅ ደግሞ በራሷ ላይ ያደረገችው ዘውድ በእምራልድ በወርቅና በልዩ ልዩ የከበረ ድንጋይ የተንቆጠቆጠ ብዙ የወይን ፍሬና የስንዴ ዘለላ ያለበት ሲሆን፤ በእናትና ልጅ አንገትና ደረት ያለው ጌጣጌጥ የለበሱትም ልብስ መግለጽ ስለማይቻልና ገዢም ስለሚመስድ ሰማያዊ መረግድና ያክንት ነው፤

በእግዚአብሔር አገር በኤደን ገነት በምድረ ኢትዮጵያ የሚገኝ ዕብነ አድማስ፤ የከበረ ዕንቁ ሰርድዮን፤ ጳዝዮን፤ አልማዝ፤ ሰምፔር የሚባልና የሚያንፀባርቅ ወርቅ ሞ ብርሌ መራውሬ፤ ማለትም በዓይን ዓይቶ ከማድነቅ በስተቀር ከዚህ በላይ ስለማይበራራ እጹብ ድንቅ ነው በማለት አልፈዋለሁ። ሕዝ.ም.ሸ፰ቁ.፲፫-፲፮(28.13-16) ራዕ.ም.ሸ፳፩ ቁ.፲፯-ሸ፳፩ /21.17-21/ ይመልከቱ።





ይሁን እንጂ የመጀመሪያው ሰውንና ክርስቶስን የሚወክለው "ዮ" ፊደል ያለበት ፀሐይ ጨረሮቹ ጫፋቸው ፭ት/5/ የሰው እጅ ጣት ያላቸው ሲሆኑ በጀቱም /2/ ሴቶች እናትና ልጅ እራስ ላይ አንዣበው ይታያሉ፤ ይህም ሌላው አስደናቂ ምስጢር ነው። በየፒራሚዱ ሁሉ በተፈለፈለ ቅርፃቅርፅ ሆኖ በአይን ይታያል።

ከዚህ በላይ በአጭሩ ለተገለጸው በይበልጥ ታሪኩን ለማወቅና ዋናውን በዓይኑ ለማየት የሚፈልግ ሰው ቢኖር በኢትዮጵያ ያለው ገና ያልወጣው ሳይሆን፤

ነገር ግን በግብጽ /ምሥር/ ውስጥ የነበረው ተፈልፍሎና ተሰባብሮ ተነቅሎ ተወስዶ በለንደን ሙዚየም የሚገኘው ዋናውን በዓይኑ አይቶ የሚረዳ ከመሆኑም በላይ፤

እንዲሁም ደግሞ ሥዕሉን ብቻ ለማየት የፈለገ ስለግብጽ ወይም ምሥር የተጻፉ መጻሕፍቶችንና የተለያዩ የቱሪስት መጽሔቶችን ተመልከቶ

መረዳት የሚችል ከመሆኑም በላይ ሥዕሉን በተመለከተ የጥንቱ የኢትዮጵያም የግብጹም በዚህ ጥናት ውስጥ ያስገባሁት ስለሆነ እንዲመለከቱት አሳስባለሁ።

ቢሆንም ከላይ ከጥያቄ ፬ት/4/ ጀምሮ በመጠኑም ቢሆን ታሪኩ ስለተገለጸው የ፪/2/ ሴቶች እናትና ልጅ የቅርፅ ምስል ወይም ሥዕል፤ ትክክለኛው ትርጉም ወይም ፍች በመጽሐፈ ሔኖክ ዘአዶናይ ራፋኤል እናገኘዋለን፤

የመጽሐፈ ምስጢር ዘአዶናይ ራፋኤልም ሥዕሉን በተመለከተ የመዘገቡት እንደ መፅሐፈ ሔኖክ ዘአዶናይ ራፋኤል ቃሉ አንድ አይነት ነው።

በአምልኮተ ፀሐይ በሚታመንበት ፕራሚድ ውስጥ ስለነበረው የ፪/2/ ሴቶች እናትና ልጅ ምስል ወይም ሥዕል በመጽሐፈ ሄኖክና መጽሐፈ ምስጢር ከተገለጸው ውስጥ በአጭሩ እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

ይኸውም ትርጉሙ በሥዕሉ ላይ እንደሚታየው ሁሉ ቁማ በሯሷ ላይ ፩ድ/1/ የወይን ፍሬና የስንዴ ዘለላ





ያለው ዘውድ ያደረገችው ሴት በትንቢቱ መሠረት ቅድስት ሐና ነች፤ ወይኑ ፩ድ/1/ የሆነበት ምክንያት ደግሞ ለወደፊት በስተእርጅና የምትወልዳት ሴት ልጅ አንዲት ስለምትሆን ነው፤

ስለዚህ ሰሎሞን አስቀድሞ ለእናቷ ፩ዲት/1/ ነች እርሷን የወለደች የተመረጠች የተባረከችና የተቀደሰች ናት ብሎ በመሀልየ መሀልይ ያመሰገናት ናት። መሐልይ ም.፮ ቁ. ፱-፲ (6.9-10)

እንዲሁም በሥዕሉ እንደሚታየው ሁሉ ተቀምጣ ብዙ የወይን ፍሬና የስንዴ ዘለላ ያለበት ዘውድ በራሷ ላይ ያደረገችው ሴት ልጅ እመብርሃን ስትሆን፤ ወይኑንና ስንዴው ብዙ የሆነበት ምክንያት ደግሞ ድንግል ማርያም ለወደፊት የዓለም እናት መሆኗንና የማያልቅ ጎብስትና ወይን መጣኛ እንደሆነች የሚያመለክት እውነታ ነው፤ በፀሐዩ መሐል ላይ ክርስቶስን የሚወክለው "ዮ" ፊደል ያለበት ባለጨረር የሆነ ፀሐይ ደግሞ ከድንግል

ማርያም ለወደፊት የሚወለደው እውነተኛው ፀሐይ የኢየሱስ ክርስቶስ አማናዊ ምሳሌ ሲሆን፤

ስንዴውና ወይኑ ደግሞ ለአሁኑ ለአዲሱ ዘመን ሕያው እግዚአብሔር መድሐኒዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ ሐሙስ ይህ ኅብስት ነኝ በመስቀል ላይ የሚፈተተው እውነተኛ ሥጋዬ ነው፤

ይህ ወይን በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ የሚፈሰው እውነተኛ ደሜ ነው በማለት በመጨረሻ ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ባደረገው እራት ላይ በዮሐንስና በማቴዎስ ወንጌል በሚገባ አረጋግጦታል። ዮሐ.ም.፮ ቁ. ፶፩-፶፱ /6-51-59/ ማቴ.ም. ፳፮ ቁ. ፳፮-፴ /26፣ 26-30/ ይመልከቱ።

ይሁን እንጂ ከላይ አስቀድሞ ታሪኩን ባጭሩ እንደተገለጸው ሁሉ ከፍጥረተ ፱ /5450/ ከ.ፊ. /B.C./ በካራን የአምላክ ቤተ መቅደስ በመሐል ኢትዮጵያ ከኤደን ገነት አንስቶ እስከ ፫ሺ፱፻፶ /3950/ ከ.ፊ. /B.C./ በላዕላይ ግብጽ ቤተ መቅደስ ጀምሮ ፀሐይ አምላክ ነው ተብሎ በሚታመንበት ፕራሚድ ወይም መቅደስ ውስጥ <u>እመብርሃን</u> ከእናቷ ከሐና





ጋር ከፍ ብሎ እንደተብራራው ሁሉ በአስደናቂ ሁኔታ ተቀርፆ ወይም ሕብሩ በማይታወቅ ተሥሎ የታቦተ ጽዮን ቀዳማዊ ምሳሌ በመሆን ይመለክበት እንደነበር እውነት ነው፤

ስለዚህ በተአምረ ማርያም ላይ እመቤታችን ቅድስት ማርያም ዓለም ሳይፈጠር በዓምላክ ልቦና አስቀድሞ ነበረች ለሚለው አንጋገር በቂ የሆነ ማስረጃ ከመሆኑም በላይ፤

መድኃኔዓለም ራሱ ባለቤቱ ሕያው እግዚአብሔር በቅዱስ ዳዊት አድሮ ጽዮንን ለዘለዓለም ማደሪያዬ ትሆን ዘንድ ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሜ መርጫታለሁ በማለት አጽድቆታል። መዝ. ፩፻፴፩ ቁ. ፲፫-፲፭ /131.13-15/ ይመልከቱ።

በመጽሐፈ ምስጢር ዘአዶናይ ራፋኤልና ሔኖክ ዘአዶናይ ራፋኤል እንደጻፉት፤ እኔም ከፍ ብሎ በተደጋጋሚ እንደገለጽኩት ሁሉ አምልኮተ ፀሐይን በሚመለክበት ፕራሚድ /ቤተ-መቅደስ/ ውስጥ የሚያገለግሉ ሊቃነ ካህናቶችንና ካህናቶች መዘምራን ነበሩን፤

የመዘምራኑና የካህናቱ ቁጥር በጣም ብዙ ስለነበሩ ለጊዜው ባይታወቅም፤ የሊቃነ ካህናቱ ቁጥር ግን በመጽሐፈ ምስጢር ዘአዶናይ ራፋኤል የተመዘገበ ስለሆነ ከአማን ራሔ እስከ ኢዮተር ድረስ ፱፻፸፩ /2021/ መሆኑን በድጋሚ መጽሐፈ ምስጢረ ካህናት ዘአዶናይ ራፋኤል ይናገራል።

ከጥንት ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ ፀሐይ የኢትዮጵያ አምላክነ ለመሆኑ በርካታ ማስረጃዎች አሉ፤ ከብዙዎቹ ጥቂቶቹን እጠቅሳለሁ፤ የአባ ሳሙኤል ዘዋልድባ የአጐት ልጅ የሆነ የብሂንሣው በመባል የሚታወቀው አባ ሕርያቆስ ሲሆን፤ ብሂንሳ ማለትም በዛሬው ዘመን በዋልድባ ገዳም ውስጥ አርምሐ ደጋ እየተባለ የሚጠራው ሥፍራ ነው።

ስለዚህ አባ ሕርያቆስ በደረሰው በቅዳሴ ማርያም ላይ ስለ ፀሐይ አምላክነ መሆን በምሳሌነት ሲያብራራ አብ ፀሐይ ነው ፤ ወልድ ፀሐይ ነው ፤ መንፈስ ቅዱስ ፀሐይ ነው ብሏል፤ በማንኛውም ጊዜ በታተመው በቅዳሴ ማርያም ላይ ይመልከቱ።





ነው፤ የሚለው ቃል የማይሻገር ግስ ሲሆን፤ ከሁሉ በላይ የሆነ ፩ድ/1/ የሕይወት ፀሐይ ነው፤ ያለውን መድኃኒታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ እውነት መሆኑን በዮሐንስ ወንጌል ሲያረጋግጥ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ ጨለማ ሳይመጣ በብርሃን ተመላለሱ፤ ለዘለዓለም የማይጠፋ እውነተኛ ፀሐይ እኔ ነኝ በማለት አትሞታል። ዮሐ.ም.፩ ቁ.፭ /1.5/ ዮሐ.ም.፰፤፲፪ /8:12/፤ ዮሐ.ም.፱፤፭ /9:5/ ይመልከቱ።

የእምነት ፍልስፍና ወይም ምርምር ከዚህ በላይ የተገለጸውን የሕያው እግዚአብሔር ቃል መሠረት በማድረግ ስለ ፀሐይ አምላክነት በአባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ፤ ፀሐይ በወንድና በሴት ፆታ እንደምትጠራ የማይካድ እውነት ነው።


ይሁን እንጂ ፀሐይ በዓይን የምትታይ በእጅ የምትዳሰስ ግዙፍ የሆነች ኃይል መሆኗ የተረጋገጠ ሲሆን፤ ነገር ግን ከብርሃኗና ከሙቀት ነበልባልነቷ የተነሳ በዚህ ዓለም በሚገኙ ጥበበኞችና አዋቂዎች

ዘንድ ያልታወቀችና ለወደፊትም ቢሆን የማትታወቅ የጥበብ ሁሉ እናትና ምንጭ ነች።

ፀሐይ በምድሮችና በሰማያቶች፤ በላያቸውና በውስጣቸው፤ ለሚንቀሳቀሱና ለማይንቀሳቀሱ፤ ሕይወት ላላቸውና ለሌላቸው፤ ለሚናገሩና ለማይናገሩ፤ ለፍጥረታት በሙሉ፤ መገኛና የሕይወት ሁሉ ምንጭ እንደሆነ የማይታበል እውነት ነው፤

ስለዚህ ፀሐይ ፍጡር ነው፤ ናት፤ ወይንስ ፈጣሪ? ሕይወት ያላቸውም የሌላቸውም ፍጥረታት ሁሉ፤ ያለ ፀሐይ ብርሃንና ሙቀት ጨረር መኖርም ሆነ ማደግ መራባት እንደማይችሉ የታወቀና የተረጋገጠ ነው፤ የዚህንስ ሁኔታ ምክንያቱና ምሥጢሩ ምን ይሆን? መልሱን ለአንባብያን እንዲመራመሩበት ይሆን ዘንድ በመተው፤ በታላቅ ትህትና አሳስባለሁ፤ ጊዜ ከተገኘም ለወደፊት በሚገባ ይብራራል።





1.ፅኛ. የተዋሕዶ አንበሳ፤ ማያ ኢትዮጵያ፤
(ተአምረኛዋ ዐይን በሕይወት ምስል
በ ቶ ፊደል ውስጥ)

ፅ.1ኛ. The Lion of Tewahido, Mayia Ethiopia.
(The Miracle Eye in the Symbol of Life
letter "ቶ")




፩. ቅድስት ድንግል ማርያም የመድኃኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ እናት፣

1. St. Vergne Merry, the Mother of Salivation Jesus Christ.



1.፩ኛ. የተዋሕዶ አንበሳ፣ ማያ ኢትዮጵያ፣ (ተአምረኛዋ ዐይን በሕይወት ምስል በ ቶ ፊደል ውስጥ)

፩.1ኛ. The Lion of Tewahido, Mayia Ethiopia. (The Miracle Eye in the Symbol of Life letter "ቶ")



ፅኛ. የሰው ዘር መጀመሪያ ማን ነው፤
ድንቅነሽ (ሉሲ) አዳምና ሔዋን፤
የጥቁር ወይም ኢትዮጵያውያን፤
ሀ. (ተዓምረኛዋ ዐይን በሕይወት ምስል ውስጥ)
2ኛ. Who is the origin of the man.
Dinkinesh (Lucy) Adam & Hewan. (Eve)
The black (brown) Ethiopians.
A. (The Miracle Eye in the symbol of life)



# ክፍል ፪/2/

## ለ. በይበልጥ ታሪኩን ግልጽ ለማድረግ፤

### 1. ድንቅነሽ /ሉሲ/ አዳምና ሔዋን፤

ዘለዓለማዊ የሆነ የብርሃን አምላክ ሕያው እግዚአብሔር የሰው ዘር መገኛ ምንጭ ያደረጋቸው ዕንቆች ሲሆኑ፤ ሁሉም ኢትዮጵያውያን እንደሆኑ ማስረጃ ያለው ስለሆነ የማይታበል እውነት ነው፤

ይኸውም ስለ ሰው ዘር አመጣጥ አጥኝዎች የሆኑ ተመራማሪዎች አንስሮፖሎጂስቶች እና አርኪዮሎጂስቶች በዓለም ውስጥ ሰው መሰል የሆነ ብዙ ቅሪተ አፅሞችን አግኝተዋል።

ነገር ግን ከብዙ ድካም በኋላ በፕሮፌሰር /1974/ ዓ.ም. እንደፈረንጆች አቆጣጠር በሴተ አማራ ወይም ወሎ ክፍለ ሀገር በአፋር ሐዳር ወረዳ በትክክል የመጀመሪያው ሰው የሆነ የሴት አፅም እንዳገኙ የተረጋገጠ እውነት ነው፤ ይህም አጥንት ድንቅነሽ ወይም ሉሲ ብለው ሰይመውታል፤

ከዚያም በኋላ በተከታታይ በአዋሽ ወንዝ ሸለቆ አካባቢ ብዙ የሰው ቅሪተ አጽሞችን እንዳገኘ በተለያዩ መጽሔቶችና ዜናዎች /ጋዜጣ/ የተመዘገበና የቀረበ ስለሆነ የማይካድ እውነት ነው።

እንዲሁም ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ መጀመሪያው አዳም በአሪት ዘፍጥረት ም.፩ ቁ. ፳፮ /1:26/ እንደተጻፈው ሕያው እግዚአብሔር ሰውን በመልካችን በእኛ አምሳል እንፍጠር ያለውን በማዕከለ ምድር በኢየሩሳሌም ነው የሚሉ አሉ፤

በዚያን ዘመን ኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ የነበረ ቢሆንም ነገር ግን ማዕከለ ምድር ኢየሩሳሌም ነው ማለት ፍጹም የሆነ ስህተት ነው፤ ማዕከለ ምድር ማለትም የመሬት ወገብ ሲሆን፤ የምድር ወገብም የሚያቋርጠው ኢትዮጵያን ነው እንጂ ኢየሩሳሌምን አይደለም።

ኤደን ገነት ማለትም ከዓለም ውስጥ በቀን አራት አየር ንብረት የሚገኝባትና ዘጠኝ ፱ /9/ ሀገር አቋራጭ የሆኑ ወንዞች የሚፈልቁባት ተራራማዋ ኢትዮጵያ ብቻ እንደሆነች የማይካድ ቢሆንም፤





ራሱም ሕያው አምላካችን በአሪት ዘፍጥረት ም.፪ ቁ. ፲-፲፬ /2:10-14/ ላይ ከአራቱ ታሪካዊ የሆኑ ወንዞች አንዱ የሆነ ግዮን ወይም ዓባይ የኢትዮጵያን ምድር ከቦ ያጠጣል በማለት ኤደን ገነት መሆኗን አረጋግጧል።

ሌሎቹ ወንዞች ማለትም በኤፌሶን ዙሪያ ብቻ ወርቅና የከበረ ድንጋይ ያለው መሆኑን ሲገልጽ፤ ጤግሮስና ኤፍራጥስ ደግሞ ይፈሳሉ አለ እንጂ ያጠጣሉ አላለም።

ስለዚህ ከዚህ በላይ እንደተብራራው ሁሉ የመጀመሪያዋ የሰው ዘር ምንጭ የሆነች ለሰ. ወይም ድንቅነሽ በኢትዮጵያ ምድር እንደተገኘች ሁሉ፤

የመጀመሪያዎቹ የሰው ልጅ ሁሉ አባትና እናት የሆኑ አዳምና ሔዋንም በምድረ ኢትዮጵያ ለመፈጠራቸውና በኤደን ገነት ለመኖራቸው ከፍ ብሎ በዘፍጥረት በተገለጸው መሠረት የማይታበል እውነት ነው።

A.ሀ. <u>ማስረጃ</u> Lucy the Beginngs of Human kind, by

Donald Johanson, and maitlend Edey, 1981, New York.

1.ሀ. National Geograph, Vol. 138. No. 6 pp. 856 to 884. December, 1970.

2.ለ. Vol. 150, No.6 pp.180 to 811. December 1976.

3.ሐ. Vol. 168. No.5 pp.500 to 505. November 1985.

4.መ. Vol. 181. No 3, pp. 2 to 53. March 1992.

5.ሠ. Vol. 189, No 3. pp.96 to 117. March 1995.

6.ረ. Vol. 191 No.2 pp. 72 to 99. February, 1997.

ሀ.A. News week, the international news magazine, January 29, 1976.

ለ.B. January 11, 1988. April2,2001, July 23,2001

ሐ.C. Time Vol. 154, No 8. August 23, 1999.

መ.D. Time Vol. 158. No 4. July 23, 2001.

ሰ.E. Time Vol. 155, No 9. July 22, 2002.

ረ.F. Time Vol. 161. No 25 pp. 68 to 70 June23, 2003.





ሀ.1. Selamta the in Fliaht magazine of Ethiopian airlines. Vol. 9, No 1. pp.11 to 18, April to June, 1992.

ለ.2. Vol. 17, No. 2 pp. 62 to 64. April to June, 2000.

**ክቡራን አንባብያን ብዙ ማስረጃ መጥቀስ ይቻላል ነገር ግን ለማያምን የተጠቀሱት ይበቃሉ።**

B.ሀ. The desruction of Black (Brown) civilization. Great issues of a Race, From 4500 B.C. to 2000 A.D. The Ethiopian empire, Ethiopia's oldest dauahter Egypt 1976 pp. 62 to 66.

**ትርጉም፣ በመጥፋት ወይም በመደምሰስ ላይ ያለ የጥቁሮች ሥልጣኔ ፣ ይኸውም ትልቅ አስፈላጊ ስለአንድ ሕዝብ ወይም ነገድ፣ ከዕሺሪያ /4500/ ከ.ፊ. /B.C/ እስከ ፪ሺ. /2000/ ዓ.ም. (A.D.) የኢትዮጵያውያን መንግሥት ወይም አገዛዝ፣ ትልቋ የኢትዮጵያ ሴት ልጅ ግብጽ ናት። ዕሺ.ዘያሪሄ ገጽ ፷፪-፷፮ /1976/. /pp.62-66. በቻንስለር ዊሊያም ችካጐ።**

## 2. ጤፍ የኤደን ምርጥ ተክል ነው፤

በኤደን ገነት ልዑል እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ዕፀዋት ውስጥ ለሰው ዘር ሁሉ ለምግብነት ከተሰጡት በከፊል፤

1.፩ኛ. ከማይነቅዙት ጤፍ፤ ዳጉሳ ሰናፍጭ፤ ጐመን ዘር ወዘተ፤

2.፪ኛ. ከሚነቅዙት ውስጥ ደግሞ ገብስ፤ ስንዴ፤ አጃ፤ ባቄላ፤ ወዘተ ፤

3.፫ኛ. ከሚፋጁት ውስጥ በርበሬና ሚጥሚጣ፤ ቂንጮ በርበሬ፤ ወዘተ...

4.፬ኛ. ከቅባት እህሎች ደግሞ ተልባ፤ ሰሊጥ፤ ኑግ ሱፍ የመሳሰሉት ናቸው።

በእንጀራና በዳቦ ተጋግረው ከሚበሉት የእህል አይነቶች ውስጥ በሕያው እግዚአብሔር ፈቃድ ለመጀመሪያዎቹ የሰው ዘር ሁሉ ምንጭ ወይም አባትና እናት ለሆኑ ለኢትዮጵያውያን ብቻ ለምግብነት ባርኮ የፈቀደላቸው ከማይነቅዙት ውስጥ





ከላይ እንደተጠቀሰው ጤፍ መሆኑን በተግባርና በዐይን የሚታይ ስለሆነ እውነት ነው፤ አይካድም።

ይሁን እንጂ ዘለዓለማዊ የሆነ ሕያው አምላክ በቅዱስ ዳዊት አድሮ እንደተናገረው አንተ ባሕርን እንዳትናወጥ አጸናህ ከውሀውም ውስጥ ሁለት ዘንዶዎችን አወጣህ የዘንዶዎችንም ራስ ቀጠቀጥህ አጣፍጠህ ለኢትዮጵያውያን ምግባቸውን ሰጠሀቸው ነው ያለው፤ መዝ.፸፫/፸፬/ ቁ.፲፫-፲፭ /74:13-15/፣ እንደገና ጤፍ ከሌሎች እህሎች ጋር ተቀላቅሎ መድኃኒት ስለመሆኑ ደግሞ ሕዝ.ም.፬ ቁ.፱-፲ /4:9-10/፣ ዕዝ.ስቱኤ.ም.፬ ቁ.፶፩-፶፫ /4:51-53/ ይመልከቱ።

ዘንዶ ወይም እባብ ያለው አነጋገር ትርጉሙ በጥንቱ የኢትዮጵያውያን ሰብአ ቋንቋና በጥንቱ ግዕዝ አረማይስጥ ቋንቋ እንዲሁም በዛሬው ግዕዝና ኢትዮጵያዊኛ /አማርኛ/ ጥቁር ጤፍና ነጭ ጤፍ ማለት ነው እንጂ በቁሙ ዘንዶ ማለት አይደለም።

የዘንዶና የእባብ ሥጋ በአሁኑ ዘመን በዓለም ዘንድ ተወዳጅ የሆነ ምግብ መሆኑን የታወቀና የተረጋገጠ ቢሆንም፤ ነገር ግን ኢትዮጵያውያን

በአሪቱ ሕግ መሠረት ርኩስ የሆነ እንስሳ ፈጽሞ ስለማይበሉ ብቻ ነው። ዘዳግ.ም. ፲፬ ቁ. ፩-፵፯ /11:1-47/፣ ዘሌዋ.ም.፲፬ ቁ.፫-፵፫ /14:3-23/ ይመልከቱ።

ከላይ በተጠቀሰው መሠረት ዘንዶ ያለመሆኑን የሚያረጋግጥ በቂ የሆነ ማስረጃ ነው እላለሁ።

በአሁኑ ዘመን የጤፍ ምርትና ምግብ ሁለት ዓይነት መሆኑ ቀርቶ በማዳቀል ማለትም በሰው ሳይሆን በሕያው አምላክ ፈቃድ አምስት ዓይነት ሆኗል፤

A.ሀ. ይኸውም ጥቁር ጤፍ፤

B.ለ. ቀይ ጤፍ፤

C.ሐ. ሰርገኛ ጤፍ፤

D.መ. ነጭ ማኛ ጤፍ፤

E.ሠ. እንዲሁም ከሁሉም ዓይነት የሆነች ቡኒ የምትባለው ደግሞ በፎድ ወር የምትደርስ የጤፍ ዝሪያ ነች።

(1.) ፩. ስለዚህ ነብዩ ጤፍን ከባሕር ተገኘ ያለበት ትርጉም ደግሞ በጥሩ መሬት በተንጣለለ ሜዳ ላይ የተዘራ ጤፍ ቡቃያው





እንደ ወለደ ነፋስ ሲነፍስበትና ሲያወዛውዘው የጥዋት የፀሐይ ፈካራ እንደ አረፈበት ሲመለከቱት እንደ ባሕር ማዕበል ሲገለባበጥ ስለሚታይ ነው በባሕር የመሰለው። መዝ.፸፫. ቁ.፲፫ /73:13/

(2.) ፪. ቅዱስ ዳዊት ጤፍን በእባብ የመሰለበት ዋና ምክንያት ደግሞ ጤፍ ሲታጨድ ነዶውና ዘለላው የሚያመሳጭልጭ ከመሆኑም በላይ ሲጋገር ደግሞ እንጀራውም በጣም ለስላሳ በመሆኑ ነው። መዝ.፸፫. ቁ.፲፬ /73:14/

(3.) ፫. ራሱን ቀጠቀጥህ ያለበት ደግሞ ጤፍ ሲወቃ በበሬዎች ከተረገጠ በኋላ ምርቱን ከገለባው የሚለየው በረጃጅም ጨንገር ወይም በዱላ ስለሚመታ ሲሆን፤ ገለባው ደግሞ በጣም ለስላሳ ነው፤ ስለዚህም ለፍራሽና ትራስ ሥራ ያገለግላል። መዝ. ፸፫/፸፬ ቁ.፲፪-፲፭/73/74/12-15/ ይመልከቱ።

## 3. ጤፍ ከምግብነት ሌላ ምን ይሆናል?

የንጉሦች ንጉሥ፣ የገሮች ገዢ የአማልክቶች አምላክ የብሃኖች ብርሃን፣ የሆነ እውነተኛው አምላክ ሕያው እግዚአብሔር መዝ.፵፮.ቁ.፩-፱ (46,1-9) መዝ.፵፱ ቁ.፩-፬ (49.1-4) መዝ.፹፫ ቁ.፯ /83.7/ መዝ. ፹፭ ቁ.፰-፲ /85.8-10/ ወዘተ...

የግዮን ወንዝ ከቦ የሚያጠጣት በኤደን ገነት በኢትዮጵያ ፈጥሮ ላስቀመጣቸው፣ የሰው ዘር ሁሉ የመጀመሪያ ላደረጋቸው ለአዳምና ሔዋን ጤፍ ፍሬውን ለምግብነት ሲፈቅድላቸው ገለባው ደግሞ ለልዩ ልዩ ግንባታ እንዲያውሉት አድርጉ ነው የባረከላቸው።

ይኸውም ጤፍ ፍሬውን በወፍጮ ተፈጭቶ በጣም የሚያምር እንደ ንብ ሰፈፍ ዓይናማ የሆነ እንጀራና ዳቦ፣ እንጉቻና ጭኮ፣ ገንፎና ቂጣ፣ ፍርፍርና /ጨጨብሳ/፣ አጥሚት፣ እንዲሁም ጠላና አረቂ፣ በመሆን ለምግብነትና ለመጠጥ የሚያገለግል ሲሆን በተለይ ደግሞ የጤፍ እንጀራ ከዶሮ ወጥ





ጋር የኢትዮጵያውያን ብሔራዊ ምግብ መሆኑን በዓለም ዘንድ የታወቀና የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ያለጤፍ እንጀራ ለመኖር እንደሚያዳግተው አይካድም።

የጤፍ ገለባው ደግሞ እንደ ዛሬው ዘመን በዓለም ውስጥ ሲምንቶና ኖራ ባልተፈጠረበት ዘመን፣ ገለባ ከሲምንቶና ኖራ በበለጠ ሁኔታ ከክርስቶስ ልደት በፊት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ ለተለያዩ ግንባታዎችና ለሕንፃ ሥራ ለቤት ወረቀት ማጣበቂያ በማገልገል ላይ እንደሆነ የተረጋገጠ ነው፣

በገለባ የተለሰነ ቤትም ብርድ የለውም ስለዚህ በመላዋ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ታላላቅ ገዳማትና አድባራት ከክርስቶስ ልደት በፊት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ሳይፈርሱና ሳይጠገኑ እንደነበሩ አሉ፣

ቤተክርስቲያኖቻቸውንና ዕቃ ቤቶቻቸውን እንዲሁም ደግሞ ምርፋቆቻቸውንና ደጀሰላሞቻቸውን በድንጋይም ሆነ በእንጨት የተገነቡትና የተለሰኑት

የጤፍ ገለባ በጭቃ ተቦክቶ ሲሆን፤ ከነዚህም ውስጥ ጥቂቶቹ የተሠሩት ፎቅና ምድር ሆነው እንደሆነ አይካድም፤ እስከ ዛሬ ድረስ በዐይን ይታያሉና ነው።

የነገሥታቱ ቤተ መንግሥቶች አዳራሾችና ቤቶች፤ እንዲሁም የሕዝቡ ቤቶችም ቢሆኑ የተሠሩት የሥነ ጥበብ ቅርጻቸው ወይም አሠራራቸው ሁሉ የተለያየ ሆኖ፤ ነገር ግን እንደ ገዳማቱና አድባራቱ የጤፍ ገለባ በጭቃ ተቦክቶ የተሠሩ መሆኑን እውነት ነው።

ስለዚህ ዘለዓለማዊ የሆነ የብርሃን አምላክ ሕያው እግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃዱ ሆኖ የመጀመሪያው ፍጥረቶቹ ለሆኑ ለኢትዮጵያውያን ጤፍ ፍሬውን ለምግባቸው ባርኮ ሲሰጣቸው ገለባውን ደግሞ ከእንስሳ ምግብና /መኖ/ ጀምሮ ለልዩ ልዩ የእደ ጥበብ ሥራ እንዲያውሉት በመፍቀዱ ስሙ ለዘለዓለም የተመሰገነ ይሁን አሜን።

አባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ፤





## 4. ታሪካዊ የሆኑ ሄኖኮች ሦስት ናቸው

በመሠረቱ ሄኖክ የሚባሉት ሦስት ሲሆኑ እንደ አጋጣሚ ሆኖ ሁሉም ኢትዮጵያውያን ናቸው፤ ስለዚህ ብዙ ሰዎች በትውልድ የአዳም ፯ኛ/7/ የሆነው ሄኖክና መጽሐፈ ሄኖክን የጻፈ ሄኖክ ኢትዮጵያዊ አንድ የሚመስላቸው ሰዎች በብዛት ይገኛሉ።

1.ፅኛ. ስለዚህም ነው ለመጻፍ ያነሣሣኝ፤ ቢሆንም የአዳም ፯ኛ/7/ የሆነው ሄኖክ በነበረበት ዘመን የነበሩ ሰዎች የሚያምኑት በሕገ ልቦና ነበር እንጂ በዚያን ጊዜ ሥነ ጽሑፍ አልተጀመረም ነበር፤ ስለዚህ የአዳም ፯ኛ/7/ የተባለው ሄኖክ ፩ኛ/1/ ሄኖክ ማለት እንደሆነ አይካድም።

በዚህ ምክንያት ነው ሊቃውንቱ ሁለት ሄኖኮች መሆናቸውን ለይቶ ለማስረዳትና ለማረጋገጥ ነው ባለመጽሐፉን ሄኖክ ኢትዮጵያዊ በማለት አበክረው የገለጹት ።

2.፪ኛ. ቢሆንም መጽሐፈ ሄኖክን የጻፈው ሁለተኛ ሄኖክ ኢትዮጵያዊ የነበረበት ጊዜ ደግሞ በመልከ ጼዴቅና በአብርሃም ዘመን ሲሆን፤

መጽሐፉም ከመጻሕፍተ ሕግጋትና ነቢያት ሁሉ የመጀመሪያ ጽሑፍ መሆኑን አይካድም። ይኸውም በ፪ሺ፰፻ /2800/ ከ.ፌ. /B.C./ በእጅ የተጻፈ መሆኑን መጽሐፈ ምስጢር ዘአዶናይ ራፋኤል ያስረዳል።

ነገር ግን በብሉይ ኪዳን ውስጥ አልፎ አልፎ ከአንድም ሦስት ቦታ ላይ ባለመጽሐፉን ሄኖክ ኢትዮጵያዊውን የአዳም ፯ኛ/7/ የሆነው ሄኖክን የሚያስመስሉ ቃላት ይገኛሉ፤

ይህም በማንኛውም የዓለም መጽሐፍ ሁሉ የተለመደ አነጋገር ነው፤ ቃላትና ስም በምሥጢር አገናኝቶ መድገም ሲሆን፤ ለምሳሌ ያህል በሀገራችን አባ ሕርያቆስ የሐዋርያትን ዐይንና እጅ ወክሎ ከአምላካችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በላን ጠጣን ያለው በቂ የሆነ ማስረጃ ስለሆነ ሌላ ተጨማሪ ቃል አያስፈልገውም።





3.፫ኛ. ይሁን እንጂ ሄኖክ ዘአዶናይ ራፋኤል ተብሎ በመጽሐፈ ሄኖክ ዘአዶናይ ራፋኤል ስም የሚጠራ ደግሞ ሦስተኛው ኢትዮጵያዊ ሲሆን፤ በዚህ ጥናት ውስጥ ከፍ ብሎ በተደጋጋሚ ጠቅሸዋለሁ፤

መጽሐፈ ሄኖክ ዘአደናይ ራፋኤል በጣም ጥልቅ የሆነ ሰማያዊ የምርምር አስኪል የያዘና ከሰው ልጆች ሁሉ በላይ የሆነ የምስጢር አቁፋዳ ነው፤

ቢሆንም ለመጽሐፈ ማክስማሮስና ለመጽሐፈ ጊወርጊስ ወልደ አሚድ እንዲሁም ለመጽሐፈ አውሻክር /ሃሣበ ዘመን/ የምሥጢር አባታቸው ነው፤ አስፋፍተው ጽፈውታል።

ሀ. የመጀመሪያዎቹ የሰው ዘር ሁሉ ምንጭ የሆኑ ድንቅነሽ /ሉሲ/ አስቀድሞ ከላይ የተገለጸ ቢሆንም እንደገና በድጋሚ በይበልጥ ግልጽ ለማድረግ፤ አዳምና ሔዋን፤ ፫ቱም/3/ ሄኖኮች ሁሉም ኢትዮጵያውያን እንደሆኑ ተገልጿል።

ሰ. ማለትም ከአዳም ፯ኛ/7/ የነበረው ሄኖክ፤

ሐ. መጽሐፈ ሄኖክን የጻፈ ሄኖክ ኢትዮጵያዊ፤

መ. አሁንም በመጽሐፈ ሄኖክ ዘአዶናይ ራፋኤል የተሰየመ ሄኖክ ናቸው።

እነዚህ ሁሉ የተፈጠሩት የግዮን ወንዝ ከቦ የሚያጠጣት በኤደን ገነት በምድረ ኢትዮጵያ መሆኑን ከላይ አንስቶ በማስረጃ ጭምር እየተብራራ የመጣ ነው፤ አይታበልም።

በዓለም ውስጥ ከእነ ምግባቸውና ቀለማቸው ሳይቀር ተለይቶ አራት ዓይነት አበባ ቀለም ሆነው የተፈጠሩ መጀመሪያዎቹ የሰው ዘር ሁሉ ምንጭ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ብቻ እንደሆኑ እውነት ነው፤ በተደጋጋሚ ተገልጿል። መዝ.ፎሮ/ፎዐ/ ቁ.፲-፲፫ /73/74/10-15/ ኤር.ም.፲፫ ቁ.፳፫-፳፬ /13፤23-24/ ይመልከቱ።

እምነታቸውም ከሕያው አምላክ ከእነ ምሳሌውና ምልክቱ ጭምር በሥዕላዊ ቅርጽ የተቀረጸ ለሚመጣው ለእውነተኛው የፀሐይ አምላክ ምልክት የሆነ ፀሐይ መሆኑን በአምልኮተ ፀሐይ





በሚታመንበት ፕሮግራሚድ ውስጥ ከ፮ሺ፬፻፶ /5450/ እስከ ፫ሺ፱፻፶ /3950/ ከክርስቶስ ልደት በፊት ለኢትዮጵያውያን እንደ ተፈቀደ እውነት ነው፤

ይኸውም እውነተኛው ፀሐይ የሆነ መድኃኒዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ሆኖ እስከሚወለድ ድረስ እንዲያመልኩበት የተሰጣቸው ሕግ ሲሆን ማለትም ከሕገ አሪት በፊት ጀምሮ ለአሪትም ለሐዲስም መሠረት የሆነ ቢሆንም ከላይ ከጥያቄ አሪት ጀምሮ በቃል የተጠየቅሁት ሳይቀር መልስ በአጭሩ ሆኖ በሚገባ የተብራራ ስለሆነ እንባብያን በአጽንዖትና /በማስተዋል/ እንዲመለከቱት እጠይቃለሁ።

<u>ማስረጃ</u> ስለ ጤፍ ምርጥ ምግብነት ከላይ የተጠቀሰ ቢሆንም ለማጠናከር ያህል በድጋሚ ጤፍ ከስንዴና ከገብስ፤ ከእጃና ከባቄላ ከምሥር ጋር ቀላቅሎ ፈጭቶ በኢን በመለኪያ ሰፍሮ በዳቦ ጋግሮ ሲበሉት ከምግብነቱ በተጨማሪ ደግሞ መተኪያ የሌለው መድኃኒት መሆኑን ሕያው እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ አረጋግጦ ለኢትዮጵያውያን

ለምግብነት የሰጠን ምርጥ የኤደን ገነት ተክል ነው፤ መዝ.፹፫ ቁ.፲-፲፩/73.14-15/ ሕዝ.ም.፬ ቁ.፱-፲ /4፤9-10/ ዕዝ.ስቱኤል.ም.፬ ቁ.፶፩-፶፫/4.51-53/ ይመልከቱ።

ስለ ቀለማችን አበባ /ሞሳይክ/ መሆኑን የሚገልጽ ደግሞ፤ ኤር.ም.፲፫ ቁ. ፳፫-፳፬/13.23-24/ መሆኑን አይካድም።

## ክፍል ፫/3/

## ሐ. እውነትን ለማወቅ ለሚፈልጉ ሁሉ፤

## 5.ሠ. የጥያቄ አምስት መልስ፤ ቁ.፭/5/

የቅዱስ ላሊበላ አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ ምን እንደሆነና እንዴት በማንስ እጅ እንደ ተሠሩ ዘመኑስ መቼ እንደሆነ የሚገልጽ በአጭሩ እንደሚከተለው አቀርበዋለሁ፤ ይኸውም በ፲፩ዱ/11/ ቤተ ክርስቲያኖች ሁሉ በሚያስደንቅ ሰማያዊ ሥርዓት የሕያው እግዚአብሔር መላእክት ፳፬/24/ ሰዓት ሙሉ ለቅዱስ አምላክ ምሥጋና





እንዲያቀርቡበት ሆነው በአስደናቂ ሁኔታ የታነጹ ቢሆንም የሠሩት ደግሞ የሕያው እግዚአብሔር መላእክት እንደሆኑ አይታበልም።

ዘመኑም ከ፫ሺ፲፪ /3012/ ከ.ፊ. (B.C.) ከክርስቶስ ልደት በፊት መሆኑንም መጽሐፈ ምስጢር ዘአዶናይ ራፋኤል ያስረዳናል፤ ቢሆንም የተገለጹት ደግሞ በላልበላ ዘመነ መንግሥት ነው እንዳልኩኝ፤ የቅዱስ ላሊበላ ገድል አብያተ ክርስቲያናቱ የሠራቸው ላሊበላ ነው፤ ይላልሳ ተብሎ በቃል ለቀረበው ጥያቄ? መልስ ደግሞ በዚሁ ገድል ጥቂት ወደ ውስጥ ገባ ብሎ መላእክት እየረዱት ነው፤ በማለት ሠራው የሚለው ቃል አፍርሦታል፤

ቅዱስ ላሊባላ መላእክቱንም ለማዘዝ ሥልጣን እንዳለው የተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን የሕንፃው ሥራ በሰው እጅ እንዳልተሠራ ስለሚመሰክር ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ ሳያስፈልገው ይህ በራሱ፤ እውነት ነው።

ይሁን እንጂ ዘለዓለማዊ የሆነ ሕያው አምላክ በ፲፩ዱም /11/ ቤተ ክርስቲያኖች ውስጥ ፳፬ /24/ ሰዓታት ሙሉ ምሥጋና ሲያቀርቡለት የነበሩ አእላፍ መላእክት ወደ ጽርሐ አርያም መልሦ፤ የምድሩን ምሥጋና በመላእክት መሆኑ ቀርቶ ለሰው ልጆች ለኢትዮጵያውያን ባርኮ ሲፈቅድ፤

ለቅዱስ ላልበላ ተገልያለት የአፈር ቁፋሮ ጀመረ፤ ቀን እሱ ሲቆፍር ሌሊት ደግሞ መላእክተ ብርሃን እየረዱት የ፲፩ዱም /11/ ቤተ ክርስቲያኖች ሕንፃ ለዐይን እይታ በቅቶ በሚያስደንቅ ሁኔታ ጥርት ብሎ በዐይን ታየ፤ ሰዎችም መላእክትም በአንድ ላይ ሆነው የአምላክ ሥራ ዕውብ ድንቅ ነው አሉ፤ በአንድነት አመሰገኑ።

ስለዚህ ወዲያውኑ የእግዚአብሔር መላእክት /ቤዛ ኩሉ ዓለም/ የዓለሙ ሁሉ መድኃኒት የሚል ዜማና የምሥጋና ቃል አጥንትን በሚያድስ ሁኔታ በከፍተኛ ድምጽ አሰሙ፤

በዚህ መሠረት በየአመቱ የልደት ቀን መላእክቱን በመወከል በዚያው ቦታ ካህናቱና





ሊቃውንቱ በጣም የሚያስደንቅ በአማረ ዜማ በዓሉን ለማክበርና በረከት ለማግኘት ለመጣው ሕዝብ ሁሉ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ቃሉን ያሰማሉ ያስገርማል።

በቤተ አማራ /ወሎ/ ክፍለ ሀገር በላስታ አውራጃ በመሬት ውስጥ ከአለት ቋጢኝ ድንጊያ ተፈልፍለው በአስደናቂ ሁኔታ በሕያው አምላክ ትእዛዝ የተሠሩ አብያተ ክርስቲያናት ለጊዜው ቁጥራቸው ፲፩ /11/ ሲሆኑ ከላይ ከፍ ብሎ በአጭሩ እንደጠቀስኩት ሁሉ በቅዱስ ላሊበላ /ላልበላ/ እጅ ተሠሩ ብንል፤ እንኳንስ ፲፩ /11/ ቤተክርስቲያናች ይቅርና አንዷም ብትሆን በእርሱ ዘመነ መንግሥት መሥራት ቀርቶ አፈሩንም ቢሆን ቆፍሮ ማውጣት እንደማይቻል የተረጋገጠ የማይታበል ነው፤

የቅዱስ ላሊበላ ትክክለኛ የሆነ የስሙ ትርጉም ላሊበላ ሳይሆን ላልበላ ነው እላለሁ፤ ነገር ግን ቃሉ በአገውኛ ሲሆን፤ አገዎች ደግሞ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ አባቶች እንደሆኑ

አይካድም እውነት ነው፤ የቋንቋዎችም ሁሉ ምንጭ እንደሆነም አይታበልም።

ቢሆንም አብያተ ክርስቲያናቱ ለሕዝብ ዕይታና ለአገልግሎት የበቁት በሕያው እግዚአብሔር ፈቃድ በሰማይ ኃይላት ረዳትነት በቅዱስ ላልበላ አማካኝነት ስለሆነ ሥራው ቢባል የሚያስከብር ነው እንጂ የሚያስነውር አይደለም፤ ካልኩኝ በኋላ፤

ቅዱስ ላልበላ ያላያቸውና ያላወጣቸው በዚያው አካባቢ ተመሳሳይና ተቀራራቢ የሆነ ሥራ ያላቸው ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ ወይ? ተብሎ በቃል ለቀረበልኝ ጥያቄ መልስ ደግሞ፤ አዎ አሉ፤

ለምሳሌ ያህል በ፲፰፻፱፻፹ /1980ዓ.ም./ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ከላልበላ ፳፬ /24/ ኪሎ ሜትር ርቆ ሸደሆ መቄት በሚባለው ወረዳ በኮረብታው ላይ ላሞች ተሰማርተው ሳለ ተራራው ተደርምሶ አንዲ ላም ወደ ውስጥ ገባች። የሸደሆ ተራራ ማለትም ለማያውቁት ሰዎች ልክ እንደ ዝቋላ ተራራ ቅርጽ ያለ ነው፤ በየጁ መስቀሉ የነበረበት





የገነተ ልዑልና በሸዋ የመድኃኔዓለም ተራራም ተመሳሳይነት እንዳላቸው አይካድም።

ስለዚህ ሰዎች ላሚን ለማውጣት ሲገቡ ፹፬/84/ አምዶ ወርቅ /ፒላር/ ያለው በጣም አስደናቂ የሆነ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ተገኝቷል፤ እንዲሁም ደግሞ ሌሎችም በአካባቢው ከመቅደላ ጀምሮ እስከ አምባሰል ድረስ እየተገኘ ነው፤ ቅዱስ ላልበላ ያወጣቸው ለራሱ ከሕያው አምላክ የተፈቀደለትን ብቻ ሲሆን፤ ለወደፊትም ቢሆን ሌሎች በመላ ኢትዮጵያ የሚገኙ ሁሉ፤ ከተሰወሩበት እንደሚወጡ ጊዜው ሩቅ እንደማይሆን አምናለሁ፤

በእናት ኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች የተሰወሩ ገዳማትና ቤተ ክርስቲያናት እንዳሉ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሁሉ የታወቀ ሲሆን፤ በእነዚህም ሥውር ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ በአሳቻ ሰዓት የቅዳሴ ድምጽና የዕጣን ሽታ ሰሸት፤ አልፎ አልፎም የከበሮና የአናጽል ድምጽ ይሰማቸዋል፤ ይህም ቅዱሳን የሆኑ ሰዎችና መላእክት ቦነብረት እንደሚያገለግሉ የሚያመለክት እውነታ ነው።

ይሁን እንጂ አስቀድሜ ከላይ እንደገለጽኩት ሁለ፣ በቅዱስ ላልበላ አብያተ ክርስቲያናት የሚያገለግሉ የነበሩ ግን ፳፬/24/ ካህናተ ሰማይ ናቸው፣ ከእነሱም ውስጥ ፲፪/12/ ቅዱሳን ሊቃነ መላእክት ሲሆኑ፣ ፲፪/12/ ደግሞ ቅዱሳን አበው የኢትዮጵያ ሰዎች እንደሆኑ አይካድም።

ቢሆንም ፳፬/24/ ካህናተ ሰማይ በሕያው እግዚአብሔር ዙፋን በመንበረ ጸባኦት ጽርሐ ዓርያም ውስጥ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ እግዚአብሔር ሕያው አምላክ ዘለዓለም ቅዱስ፣ እያሉ የሚያመሰግኑና የሚያጥኑ ሲሆኑ፣ የቅዱስ ላልበላ አብያተክርስቲያናትም በሥውር ተከፍተው ከመንበረ ፀባኦት ጽርሐ ዓርያም ጋር ግንኙነት እንደነበራቸው መጽሐፈ ሄኖክ ዘአዶናይ ራሱኤል ያስረዳል። እንዲሁም ደግሞ ራእ.ም.ሪ፣ ቁ. ፩-፲፬/5.1-14/ ላይ እንደተነገረው ፳፬ቱ /24/ ካህናተ ሰማይ የሚያጥኑት በላልበላ ቤተ መቅደሶች ጭምር ነው፣

ሄኖክ፣ ሕዝቅኤል፣ ዳንኤል፣ ኢሳይያስ፣ ከአልማዝና ከዕንቁ የተሠራ መብራት ያላቸው ፯/7/





ቤተ መቅደሶች ብለው የተናገሩባቸውና በራእየ ዮሐንስም ፯ቱ/7/ አብያተ ቤተ ክርስቲያናት ተብሎ የተነገረላቸው ቅዱስ ላልበላ ካስወጣቸው ከ፲፩ዱ /11/ ውስጥ ፯ቱ /7/ መሆናቸውን እውነት ቢሆንም፣ ነገር ግን በማወቅም ሆነ ባለማወቅ፣ ወይም በምቀኝነት እስከ ዛሬ ድረስ የሚነገረው ፯ቱ /7/ አብያተ ክርስቲያናት የሚገኙት በመካከለኛው ምሥራቅ ነው እየተባለ ነበር የሚተረከው፣

ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ተብሎ ትንቢቱ በተነገረበት ዘመን በመካከለኛው ምሥራቅ እንኪንስ እንደ ቅዱስ ላልበላ ያሉ ሰማያዊ የሆነ ሥራ ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት ሊገኙ ቀርቶ፣ ሰው ሠራሽ ከሆኑ ውስጥም ቢሆን የሚደነቅ ሥራ ያለው ቤተ ክርስቲያን እንደ ሌላቸው የተረጋገጠ ነው።

የቅዱስ ላልበላ በ፯ቱ /7/ ቤተ ክርስቲያኖች ውስጥ የነበረውና የሚያበራ አልማዝና ዕንቁ በወራሪ ጣሊያኖች ከመወሰዱም በላይ የቀረው ደግሞ በንጉሡ ዘመን እናድሳለን ብለው በጀርመን ጠበብቶች መወሰዱ አይካድም።? እስከ ዛሬ ድረስም

በመመሰድ ላይ እንደሆነ አይታበልም፣ በተለይ ደግሞ በወያኔ ዘመን፣ የይምርሐው በቂ ነው።

ይሁን እንጂ በጊዜው ሰሙ ለሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ቢነገርም መጨረሻው ግን የጌቱ /7/ አብያተ ክርስቲያናት ትርጉምና ወርቁ ደግሞ ስለ እምነት አይደለም ወይ የተነገረው የሚል ጥያቄ ቢነሳ፣ በእምነት ቢሆንም በዚያን ዘመን በኢየሩሳሌምና በሶሪያ፣ በጆርዳንና በሊባኖስ፣ ከነበሩ ሕዝቦች ውስጥ አብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን እንደነበሩ የታወቀ ቢሆንም፣

ነገር ግን፣ ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ በእምነት ቀደምትነት ያላቸው ኢትዮጵያውያን ሲሆኑ፣ በሐዲስ ኪዳንም ቢሆን በትንቢቱ መሠረት ከዓለም ሕዝብ ውስጥ አምኖ የተጠመቀ የመጀመሪያው ሰው ጃንደረባ በመባል የሚታወቀው ኢትዮጵያዊ ልዑል መልከ ጼዴቅ ፪ኛ/2/ እንደሆነ እውነት ነው፣ ኢሳ. ፶፫ ቁ. ፩-፲፫ /53.1-13/ የሐዋ. ም. ፰ ቁ. ፳፯-፴፩ /8.26-41/ ቅዱስ ማርቆስ ኢትዮጵያዊ ነው፣





ክፍል ፲ሯ /15/ ገጽ ፩፻፭-፩፻፲፪ /105-112/ ፲፱፻፹፰ /1988/ ይመልከቱ።

እንዲሁም ደግሞ ሁለቱ ኢትዮጵያውያን ዕዝራ ሱቱኤልና ቅዱስ ያሬድ በጽርሐ አርያምና በቅዱስ ላልበላ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ከ፳፬ቱ /24/ ካህናተ ሰማይ ጋር በጎብረት ፳፬ /24/ ሰዓታት ሙሉ ያገለግሉ ነበር።

የምድሩንም ምሥጋናና ዝማሬም ቅዱስ ያሬድ ከአርያም ይዞልን እንደመጣ ድጓው ያስረዳል፡ እንዲሁም ደግሞ አስቀድሞ በእናት ኢትዮጵያ ውስጥ በብሉይ ኪዳን ጊዜ የነበረው የዜማ ዓይነት ግዕዝና አራራይ ብቻ ነበር፣ ሦስተኛው የዜማ ዓይነት ዕዝል በቅዱስ ያሬድ ጊዜ ነው ከጽርሐ አርያም ይዞልን የመጣው።

ለምሳሌ የስድስት ሰዓት ንቦች ከቀኗቸው ወጥተው እዚያው ላይ በማንጣበብ እንደሚያመሰግኑ ሁሉ የኢትዮጵያ ሊቃውንትም ከእያሉበት ወደ ቤተ መቅደስ መጥተው እንደ ንቦች በአንድነት

ፈጣሪያቸውን ፳፬ /24/ ሰዓት ሙሉ በጎብረት ያመሰግናሉ።

## 6.ረ. የጥያቄ ስድስት መልስ፤ ቁ.፮ /6/

የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ስለ ራስ ተፈሪያን የምኞት ሕልም ስለ አፄ ኃይለ ሥላሴ ያላቸው ራዕይ የምትለውና የምታስበው ምንም ነገር የለም፤ እነርሱ በሚያልሙትና በሚናገሩት ሁሉ በፍጹም አትስማማም፤

ከራስ ተፈሪያን እምነት ጋርም የምትጋራው ነገር ፈጽሞ የለም ለወደፊትም ቢሆን የማይታሰብ ሕልም ነው፤ የእናት ኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ /ኦርቶዶክስ/ ቤተ ክርስቲያን የምታምነው በዘለዓለማዊ የብርሃን አምላክ በመድሐኒዓለም በእየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው።

እንዲያውም አፄ ኃይለ ሥላሴ ሀገር የጋራ ነው ሃይማኖት የግል ነው በሚለው መርሆ ምክንያት በአብዛኞቹ የቤተክርስቲያን ሊቃውንቶችና መካንንቶች ዘንድ እንደ ትክክለኛ ሰው





እንደማይቆጠሩ የታወቀ ነው፤ በተለይም ደግሞ በደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያት ዕይታ፤

ይሁን እንጂ ከብዙ አመታት በፊት በዓለም ውስጥ የባሪያ ሽያጭ ይካሄድ እንደነበር በሁሉም ዘንድ አይካድም፤ ዛሬም ቢሆን የባርነት አገዛዝ መልኩን ቀየረ እንጂ በዓለም ውስጥ መዋቅሩ እንደተዘረጋ ነው። ሕዝብን እንደ ዕቃ እየገለባበጠ የሚኖር፤ የዚህ የመጥፎ ተግባር ምሳሌ የሆኑ ሀገሮችና ሕዝቦች አሜሪካ ራሺያና አውሮፓ ናቸው።

ይኸውም ሲፈልጉ ዲምክራቲክና ኮሚኒስት ሶሻሊስት ብለው ሣይሆኑ እራሳቸውን በራሳቸው የሚጠሩት የአንድ ሣንቲም ገጽታ ሆነው በስም ብቻ የሚለያዩ፤ የማደንዘዣ የዲያብሎስ ቃላት በመጠቀም እንደሆነ አይታበልም። ቢሆንም ቀደም የባሪያ ንግድ ከሚያካሂዱ ሀገሮች አንዷ ኢትዮጵያ ነበረች፤ ስለዚህ ባሪያ ብላ የምትሸጣቸው ሕዝቦች ዓረቦችና አፍሪካውያን እንዲሁም ፈረንጆች ነበሩ፤ ፈረንጅ ማለትም በአባቶች ቋንቋ ባሪያ ነው።

ዛሬም ቢሆን የአሁኑን አያድርገውና ባፅድ በማይደርስበት የሀገሪቱ ሥፍራ የፈረንጅና የዓረብ ዝርያ ያላቸው በባርነት በማገልገል ላይ እንደሚገኙ የታወቀ ነው። በዚህ ምክንያት እነዚህ ሕዝቦች ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን የሚጠሉበት ዋና የሆነ ምክንያት በውስጠ ታዋቂ ይህ ነው፤ በተለይም ዓረቦች።

እንዲሁ ደግሞ አልፎ አልፎ የሚሸጥ ሌላ ዜጋ ሲያጡ ኢትዮጵያውያኑን ሳይቀር ባርያ እያሉ ይሸጧቸው እንደ ነበር አይካድም፤ ስለዚህ ከጃማይካዎቹ ጥቂቶቹ በዘር ሐረጋቸው ከተሸጡት ኢትዮጵያውያን ስለሆኑ ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ እንደ ኢትዮጵያዊ ይታያሉ እንጂ እንደ ውጭ ዜጋ አይታዩም።

ቤተክርስቲያኗም የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ /ኦርቶዶክስ/ እምነት ተከታዮች ናቸው ብላ ነው የምታምነው፤ አፄ ኃይለ ሥላሴም በሻሸመኔ ምርጥ የሆነ ቦታ የሰጧቸው በካሣ





መልክ ነው እንጂ አምላካችን ናቸው ስላሏቸው አይደለም።

ቢሆንም ፲፱፻፹፪ /1982/ ዓ.ም. እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ለራስ ተፈሪያን እንደ ካህናትና መምህራን እንዲሁም ለነርሱ እንደ ነቢያት የሚቆጠሩ ከጃማይካና ከለንደን የተውጣጡ ወደ እኔ መጥተው ነበር፤

ይኸውም በእጃቸው የያዙት ሥዕል መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሐሙስ ማታ ከሐዋርያት ጋር የመጨረሻ ራት ሲያደርግ የመሰለ የኃይል ሥላሴ ሥዕል ሲሆን፤ ዓፄ ኃይለ ሥላሴም ከ፲፪ /12/ ራስ ተፈሪያን ጋር በግራና በቀኝ መሐል ላይ ተቀምጠው ፍራፍሬ ሲበሉና ሲሰጡ የሚያሳየው ሥዕል ማለት ነው፤ ይህም ምስል በራስ ተፈሪያን ዘንድ የታወቀ ስለሆነ አይካድም። እነርሱ በስጦታ የሰጡኝ ሥዕሉ በኔ እጅ ይገኛል።

ይሁን እንጂ ራስ ተፈሪያኑ የኃይለ ሥላሴን ምስል እንደያዙ ዓለም ሁሉ የራሱ የሆነ አምላክ አለው፤ እኛም ዓፄ ኃይለ ሥላሴን በአምላክነት

የመረጥን ስለሆነ አንተ ምን አስተያየት አለህ ብለው ላቀረቡልኝ ጥያቄ?

ከእነርሱ በፊት ሌሎች መጥተው ጠይቀውኝ ኃይለ ሥላሴ ፍጡር ነው እንጂ አምላክ አይደለም ብዬ በማስረዳቴ ሳይቀበሉኝ ቀርቶ በጥል መለያየታችንን አስታውሳለሁ፤

ስለዚህ ለእነዚህም እውነቱን ብነግራቸው ስለማይቀበሉኝ ቢያንስ ስሙ እንኳን ሥላሴን ስለሚወክል ዓፄ ኃይለ ሥላሴ ለእናንተ ነፍስ አምላክ መሆን ሲያንሳቸው ነው በማለት አሰናብቻቸዋለሁ።

ከሚያስገርመው ነገር አንዱ ደግሞ እኔን የጠየቁኝ የቢ.ቢ.ሲ (B.B.C.) መልእክተኞች ወዲያውኑ በሻሸመኔ የሚኖሩትን ራስ ተፈርያን ጥያቄ እቅርበውላቸው ነበር።

የሰጡት መልስ በታሪክ መልኩ ብቻ የሚደነቅ ሆኖ ነገር ግን ስለ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ እነርሱም ሲመልሱ በእርግጥ አምላክ ነው፤ በማለት ነበር ያረጋገጡት፤ ሰዎቹ እንደ ሩቅ ምሥራቅ ሰዎች





በፍጡር የሚያምኑ ስለሆነ አንድ ነገር ይጐድላቸዋል ብዬ አምናለሁ።

## 7.ሰ. <u>የጥያቄ ሰባት መልስ፤ ቁ. ፯/7/</u>

ኃይለ ሥላሴ ከሳባና ከሰሎሞን ሲያያዝ የመጣ ነው ወይ ተብሎ ለቀረበልኝ ጥያቄ? ስለ ዓፄ ኃይለ ሥላሴ ሥርወ መንግሥት አመጣጥ ከመግለጼ በፊት መቅደም የሚገባውና ጠያቂዎቹም የዘነጉትን በጣም ጠቃሚ የሆነ ፍሬ ጉዳይ አለ፤

ይኸውም ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ፤ የሚለው መርሕ ነው፤ የዚህ አነጋገር ትርጉም እንኳንስ በባዕዶች ይቅርና በኢትዮጵያውያን ዘንድም በአብዛኞቹ ትርጉሙ በትክክል ምን ማለት እንደሆነ የሚታወቅ አይመስለኝም፤ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ፤ ማለትም አንበሳ የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን፤ ይሁዳ

ማለት ደግሞ እውነተኛ ታማኝ ነው፤ እንደገና አንበሳ የእንስሳና የሰውም ስም ይሆናል።

ስለዚህ ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ማለት ትክክለኛ ትርጉሙ፤ ከእውነተኛው አምላክ ከኢየሱስ ክርስቶስ የተፈቀደች የኢትዮጵያውያን ሥርወ መንግሥት ማለት ነው እንጂ ከይሁዳ ወይም ከኢየሩሳሌም የመጣች መንግሥት ማለት አይደለም።

ሰብዓ አዜብ /ሼባ/ ማክዳ ለኢትዮጵያውያን በሥርወ መንግሥት ከመጀመርያው የኢትዮጵያ ንጉሥ ከነበረው ኢዮጵያ አንስቶ እስከ ራሷ ድረስ ፪ሺ፱፻ኛ /2900/ ስትሆን፤ ያውም ከ፲፪ /12/ አመት በታች የነገሡት ሳይቆጠር ነው ፤

ሰሎሞን ደግሞ ለእሥራኤላውያን በሥርወ መንግሥት ከመጀመርያው ንጉሥ ከሳያል አንስቶ ፫ኛ /3/ ነው፤ በማለት እየገለጽሁ ሳለ የምትጠይቀኝ ፕሮፌሰር ጣልቃ ገብታ ሰሎሞን ጥቁር ነበረወይ? ብላ ጠየቀችኝ፤ እኔም ሰሎሞን ስለ ራሱ የተናገረውን





ቃል የጥንቱ ያልተበረዘው የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ስላለኝ ከመጋልየ መጋልይ አውጥቼ ሰጠኋት፤

ቃሉ የሚለው ከእኔ በፊት ለነገሡ ነገሥታት ያልተሰጠ፤ ከእኔም በኋላ ለሚነግሡም የማይሰጥ፤ ልዩ የሆነ ጥበብ ለእኔ ለጥቂሩና ለጠይሙ ለሰሎሞን ብቻ ነው የተሰጠው የሚል ሲሆን፤ ይህ ኃይለ ቃል የሚገኘው በጥንት የብራና መሐልየ መሐልይ ብቻና በአንድ የጥንት እንግልዝኛ ብቻ ነው፤

እንደገና ጠየቂዋ በመደንገጥ አስደናቂ ነው፤ ካለች በኋላ ዳዊትም ጥቁር ነበረወይ? በማለት ጠየቀችኝ፤ እኔም መልሼ በእናት ቢሆን ነበር እንጂ የሚያጠራጥረው፤ ልጁ ጥቁር ከሆነ አባቱ ምን እንደሚመስል መገመት አስቸጋሪ አይሆንም ስላት ሁለም ወንድርፉል /አስደናቂ/ ነው ብለዋል፤

ይህም እንዳለ በቢ.ቢ.ሲና (B.B.C.) በሲ.ኤን.ኤን (C.N.N.) አስተላልፈውታል። ስለዚህ ዘለዓለማዊ የሆነ አምላክ ሕያው እግዚአብሔር እውነቱን

ሳይደብቁ ስላስተላለፉ ይባርካቸው ረጅም ዕድሜም እንዲሰጣቸው እጸልያለሁ።

ዋናው ቁምነገር ግን አጥብቆ ጠያቂ የእናቱን መሞት ይረዳል እንደተባለው የአባቶች ምሳሌ ሁሉ፣ የኢትዮጵያ ሥርወ መንግሥት ከእሥራኤል መሆኑን ለማስረዳት መጥተው፣

የሺኤል /የእሥራኤል/ ሥርወ መንግሥትና መሠረት ከኢትዮጵያ መሆኑን ተረድተው መመለሳቸውን ነው፣ ዘለዓለማዊ የሆነ የብርሃን አምላክ ሕያው እግዚአብሔር መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ የተመሰነገ ይሁን አሜን።

እንዲሁም ደግሞ በመቀጠል በቃል ጥያቄ ማርያምስ ጥቁር ነበረች ወይ? ለተባለው መልስ የታተመው ኢትዮጵያውኛውም እንግሊዝኛውም መጽሐፍ ቅዱስ ከአንዷ በስተቀር ሁሉም ስህተት ስለሆነ፣ በብራና የተጻፈው የግዕዙን መዝሙረ ዳዊት እንዳለ እጠቅሰዋለሁ፣ እመቤታችን አስቀድማ ስለ ራሷ በመሀሌ መሐልዬ እንደተጻፈው በሰሎሞን አፍ የተናገረችው ነው።





ይኸውም በግዕዙ "እስመ አነ ጸላም ወሰናይት እምአዋልደ ኢየሩሳሌም፣ ከመምጽላላተ ቄዳር ወሐይመታተ ሰሎሞን" የሚል ነበር፣ መሐልይ ም.፩ ቁ.፭-፮ /1: 5-7/ ይመልከቱ።

ስለዚህ ትርጉሙ በኢየሩሳሌም ፬/4/ ዓይነት የተለያዩ ነገዶች ነበሩ እነዚህም በትንቢተ ኤርምያስ እንደተጻፈው ፬/4/ ዓይነት አበባ ቀለም መልክ ያላቸው ኢትዮጵያውያን፣ ብቻ ሲሆኑ አይሁዶች ዓረቦችና ሩርሦች ደግሞ ቀይ ቀለም እንደሆኑ አይካድም።

በዚህ ምክንያት ነው እመቤታችን ቅድስት ማርያም በሰሎሞን አፍ ሆና ስለራሷ ስትናገር "ከኢየሩሳሌም ልጃገረዶች ይልቅ የጥቁር ጠይሚ ውቡዋ መልክ መልካሚ እኔ ነኝ፣ ብላ የተናገረችው እንደ ሰሎሞን መጋረጃዎች የወይን ጠጅ መልክ፣ እንደ ቄዳር ድንኳኖች የወይን ጠጅ መልክ፣ እንደ ቄዳር የዛፍ ቅጠሎች፣ ጥቁሮች ከእነ ወዛቸው፣

በእነዚህ ሁሉ እመሰላለሁ" ብላ እመቤታችን የተናገረችው ቢሆንም፣ ሰሎሞን ደግሞ ራሱ ስለ እመቤታችን እስቀድሞ የተናገረው ቃል ግዕዙን

እንዳለ እጠቅሳለሁ "ወዓ ነአ ከመትርአያ ያአዋልደ ኢየሩሳሌም፣ ለእምየ ፍቅርትየ ሰናይትየ፣ ምንት ይመስል ላህያ ትመስል ከመወይን ፍሬ" ነው ያለው። መሐል: ም.፮ ቁ. ፱-፲ /6: 9-10/

የትርጉሙ ቃል ደግሞ፣ እናንተ የኢየሩሳሌም ልጃገረዶች ሆይ ኑ ውጡ የእናቴንና የእመቤቴን የመልክ ውበትና ቁንጅና ታዩ ዘንድ፣ ደም ግባቷ ምን ይመስላል የወይን ፍሬ የወይን እሸት ይመስላል በማለት ነው ቃላት እያጠረው የገለጸት፣ የወይን ፍሬ በእሸትነቱ በጣም የሚያምር ጠይም ነው ሲያርቅ ደግሞ ጥቁር ነው የሚሆነው።

በሁሉም ዘንድ እንደሚታወቀው ሁሉ የወይን ፍሬ በዛፉ ላይ ሆኖ ተንጀርግጉ የቀይ ጠይም መልኩን ከእነወዙ በእሸትነቱ ሲመለከቱት እዩኝ እዩኝ ይላል ዐይን አያስቀለብስም፣ ደግሞም የወይን ፍሬ በስሉና ተቆርጦ የጥቁር ጠይም ሆኖ ሲመለከቱት ብሉኝ ብሉኝ ያሰኛል፣

"ኢትዮጵያዊው አባ ሕርያቆስ" ደግሞ እንደ ሰሎሞን ስለ እመቤታችን የሚገልጽበት ቃላት





አጥቶ፣ ማን በመሰለው ምሳሌ እንመስልሻለን እንዲያው ዕውብ ድንቅ ነው ብሏል፣ በቅዳሴ ማርያም ላይ ይመልከቱ።

## 8.ሸ. <u>የጥያቄ ስምንት መልስ፤ ቁ.፹/8/</u>

ኢትዮጵያ የተለያዩ እምነቶች መኖሪያ ነች ለሚለው ጥያቄ መልስ፣ ኢትዮጵያ የብዙ እምነቶች መኖሪያና ማስተናገጃ አይደለችም ሐሰት ነው፣ ቤተአሥራኤልና ራስ ተፈሪያንም የፖለቲካ ድርጅትና በኢትዮጵያ ውስጥ የተቋቋመ የስለላ ቅርንጫፍ ነው እንጂ የእምነት ተቋም አይደለም፣

ሌሎችም በኢትዮጵያ የሚገኙ የሃይማኖት ድርጅቶች ሁሉ እንዳሁ ቅጥረኞች ናቸው፣ በእርግጥ የራሴ ቤተክርስቲያን ግን የእምነት ተቋም እና የኢትዮጵያ ብሔራዊት ሃይማኖት መሆኗ አይካድም እውነት ነው።

ይሁን እንጂ ቤተ ሳኤሎቹና /እሥራኤሎች/ አይሁዶችም በአጥንትና በሥጋ የማይወሐዱኝ

ከመሆኑም በላይ የምወዳቸው ሕዝቦች ሲሆኑ፤ ነገር ግን ሃይማኖትና እምነት ብለው የያዙት ከአዋቂነታቸው ጋር አብሮ የማይሄድ ትንቢቱ ያለፈና የተፈጸመ ነው።

በዚያውም ላይ ለስለላ እንዲያመቻቸው ብለው በየጊዜው የሚፈጥሩት መሠረተቢስ የሆነ አዳዲስ ሃይማኖት የዓለምን ሕዝብ ከማወካቸውም በላይ በተለይ ደግሞ ኢትዮጵያን እየበጠበጧትና እየከፋፈሏት ይገኛሉ። ይህንንም አሳዛኝ የሆነ ድርጊት ቢያርሙት መልካም መሆኑን አሳስባለሁ።

ቢሆንም እንደገና የከፋው ደግሞ በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ መድበው በዓለም ውስጥ መዋቅራቸውን በመዘርጋት፤ ታቦተ ጽዮንን እናገኛለን በማለት የተሳሳተ በጣም ሥውን የሆነ ሰበብ ምክንያት፤

በእየአቅጣጫው ሁሉ የሌቦች ቡድን አቋቁመው በማዘረፍ ኢትዮጵያን ቅርስ አልባ እያደረጓት ይገኛሉ፤ ይህም ድርጊት መጥፎ ስለሆነ የኢትዮጵያውያን አምላክ ሕያው እግዜአብሔር እንዳይበቀላቸው እፈራለሁ።





እንዲሁም ደግሞ ራስ ተፈሪያኑ ጥቂቶቹ በዘር ሐረጋቸው ኢትዮጵያውያን ቢሆኑም ነገር ግን በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ እምነታቸው መሠረተ ቢስ የሆነ እምነት አንድ ግለሰብ አምላክ ነው ብለው የሚያምኑ ከመሆኑም በላይ፤ በተለይ ደግሞ አብዛኞቹ በምግባረ ብልሹነት የተበከሉ ስለሆነ በዚህ ምክንያት ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ የባዕዶች የስለላ ድርጅት ቅጥረኞች እንደሆኑ ባይካድም፤

ከማሪዋና ጀምሮ የተለያዩ የመጥፎ ዕፀዋት ሁሉ ሱሰኞች ስለሆኑ የኢትዮጵያን ወጣት በመበከል ላይ ይገኛሉ፤ በተለይ ደግሞ በሻሸመኔ፤ እነዚህም በሕያው አምላክ እንዳይቀጡ እሰጋለሁ።

ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ያገናኘኋቸውና /ያያያዝኳቸው/ እኔ እስከማውቀው ድረስ ቀደም ብሎም ቢሆን ፤ ለሀገሩ ለሕዝቡና ለሃይማኖቱ የቆመ መሪ በመንፈሳዊም ሆነ በሥጋዊ በኢትዮጵያ ተነስቶ ስለማያውቅና ለወደፊትም ቢሆን ይነሳል ብዬ ስለማላምን ነው። አሁንም ሕያው እግዚአብሔር ሕዝቡን ለበደሉ ሁሉ ፍርዱን

ሰጥቶ፣ በኢትዮጵያ እንደገና ሰው እንዲፈጥርልን በመመኘት እጸልያለሁ።

## 9.ቀ. <u>የጥያቄ ዘጠኝ መልስ ቁ. ፱ /9/</u>

አዎን እናንተም በጥያቄያችሁ እንዳረጋገጣችሁት ኢትዮጵያ ከዓለም የተለየች ሀገር መሆኗን ስለመረጋገጡ እውነት ነው፣ እኔም የማስበውና የምለው ነገር አለኝ፣

ይኸውም ከላይ አስቀድሜ በአጭሩ እንደጠቀስኩት ሁሉ የጽዮን ሀገር የመጠጊያና የመማፀኛ የሆኑ የተቀደሱ ብዙ ተራሮችና ኮረብታዎች ስለሚገኙባት፣ የመማፀኛ የመዳኛ ሀገር ስለሆነች ከዓለም የተለየች ናት።

ግዮንን ጨምሮ ሌሎች ፱/9/ አገር አቋራጭ የሆኑ ትላልቅ ወንዞች ስለሚፈልቁባት፣ አየር ንብረቷም ንፋሱ እንደሌሎች አገሮች ንፋስ አቧራና አሸዋን የሚበትን እንዲሁም ሞቃትና ቀዝቃዛ የሆነ





ነፋስን የሚያመጣ ሣይሆን ለሰው ልጆች ሕይወትን የሚሰጥ ተስማሚ መሆኑን አይካድም።

እንዲሁም ደግሞ ሕዝቦቿ እንደ ሌላው ዓለም ሕዝቦች አንድ ዓይነት ቀለም ሣይሆን ከፍ ብሎ እንደ ተጠቀሰው በነቢዩ ትንቢት መሠረት በቤተሰብና በጐዳና በእየስብሰባው ሁሉ በወይን ለሚመለከታቸው በጣም የሚያምርና የሚያስደንቅ በሌላው የዓለም ሕዝብ የሌለ ውበት ፬/4/ ዓይነት አበባ ቀለም ነው፣ ኤር. ም.፲፫ ቁ.፳፫-፳፬ /13:23-24/ ይመልከቱ።

ደግሞም ዘለዓለማዊ የሆነ አምላክ ከዓለም ሕዝቦች ለይቶ ለሕዝቦቿ ለኢትዮጵያውያን ምግባቸውን የሰጣቸው በመሆኑ፣ ይህም የተለየች ከሚያስደርጋት አንዱ ነው፣ መዝ. ፸፫ ቁ. ፲-፲፭ /73:10-15/ ይህንን ሁሉ በተመለከተ እናንተም የተለየች ሀገር መሆኗን እንዳላችሁት ሁሉ ኢትዮጵያ የተለየች ምርጥ ሀገር ያሰኛታል፣ የማይካድ እውነት ነው።

ትልቁና ዋናው ቁም ነገር ደግሞ ኢትዮጵያ የተለየች ምርጥ ምድር ፣ ያደረጋት፣ ሕያው

እግዚአብሔር አስቀድሞ ከዓለም ሀገራት ሁሉ ለይቶ፣ በቅዱስ ዳዊት አድሮ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች ብሎ ትንቢት ያናገረላት ፳፬ (24) ሰአታት ሙሉ ምሥጋና የምታቀርብ ቅድስት ሀገር ናት። መዝ. ፷፯ ቁ. ፴፩-፴፬ /67:31-34/ ይመልከቱ።

በዚህ መሠረት በመላዋ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ ገዳማትና አድባራት ከብሉይ ኪዳን ጊዜ አንስቶ ያለማቋረጥ ፳፬/24/ ሰዓታት ሙሉ ይጸለይባቸዋል፣ ዕጣን ይታጠንባቸዋል፣ መሥዋዕት ይሠዋባቸዋል፣

ከአሪቱ ሕግና ሥርዓት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ሳይቋረጥ ሲያያዝ የመጣውን ሕግ፣ በቀጥታ ወደ እውነተኛው የሐዲስ ኪዳን መሥዋዕት ሥርዓትና ሕግ በመለወጥ እንደገና እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የሚቀጥል አድርጋዋለች፣

ይኸውም መሥዋዕተ ነግህ፣ የጥዋት ቅዳሴ፣ መሥዋዕተ ሠርክ፣ የዘጠኝ ሰዓት ቅዳሴ፣ በመቀደስ ፳፬/24/ ሰዓት ሙሉ ለሕያው እግዚአብሔር ምሥጋና





የምታቀርብ ኢትዮጵያ ብቻ ስለሆነች ከዓለም የተለየች ቅድስት ሀገር ናት በማለት አረጋግጣለሁ።

ቢሆንም ከላይ በተደጋጋሚ እንደተጠቀሰው ሁሉ የብሉይና የሐዲስን ሕግና ሥርዓት አዋሕዳ የምትገኝ ከዓለም ብቸኛ የግዮን መፍለቂያና የመጀመሪያው አዳም ምድር ከመሆኗም በላይ ይህ ሁሉ ሥርዓትና ሕግ የሚፈጸምባት ስለሆነች ኢትዮጵያ ከዓለም የተለየች የእምላክ ምርጥ ሀገር ናት፤ አይታበልም።

## 10.በ. <u>የጥያቄ አሥር መልስ ቁ.፲/10/</u>

የቃል ኪዳን ሀገሮች ሁለት ናቸው። አንዷ ጊዜያዊት ስትሆን ፤ ሁለተኛዋ ደግሞ እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ የምትኖርና የሰው ዘሮች ሁሉ የተፈጠሩባትና የተገኙባት በሕይወት የሚኖሩባት የግዮን ወንዝ የሚፈልቅባት እውነተኛዋ ምድረ ገነት ኢትዮጵያ ናት በማለት በእውነት እናገራለሁ።

ይኸውም ከላይ ጊዜያዊት የተባለችው ምድር ከነዓን ወይም ኢየሩሳሌም ስትሆን፤ አይሁዶቹ

ወይም እሥራኤሎች በአሪት ዘፀአት እንደተጻፈው ከብዙ ምልክቶችና ተአምራቶች በኋላ በሕያው እግዚአብሔር ፈቃድ በሙሴ መሪነት ከታህታይ ምሥር /ግብጽ/ ተነስተው በመንዝ ከብዙ ችግርና ድካም በኋላ በራምሰስ ሁለተኛ ዘመነ መንግሥት ጊዜ ተለቀው ወደሲና በረሀ መግባታቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል። ራሱ ራምሰስ ፪ኛም /2/ ኢትዮጵያዊ እንደ ሆነ አይካድም።

ይሁን እንጂ ሕዝቡ በሙሴ መሪነት ከተፈቀደላቸው ቦታ እንደደረሱ ሙሴ በማግሥቱ ማለዳ ተነስቶ ወደ አማቱ ወደ ላዕላይ ምሥር /ምድያም/ ገሠገሠ። ሊቀ ካህናትና የመካከለኛ ምሥራቅ ጭምር ንጉሠ ነገሥት የነበረው ኢዮቶርን አገኘው።

ሙሴም ለአማቱ እንደ ኢትዮጵያውያን ልማድ ከእግሩ በታች ወድቆ ሰገደለት፤ የሙሴም አያት ኢትዮጵያዊት እንደነበረች አይታበልም፤ ተሳሳሙም ደኅንነታቸውንም ተጨዋወቱ ሙሴም





የሆነውን ሁሉ ለኢዮተር ተናግሮ ወደ ወገኖቹ ወደ ሲናይ በረሃ ተመለሰ፤

በነጋታውም ኢዮተር ከመኳንንቱም ከመታደሮቹም ከመቶ አለቃ ጀምሮ እስከ ሻለቃ ያሉትን ከእነ ሚስቶቻቸውና ልጆቻቸው ጭምር፤ ልጁ የሆነች የሙሴንም ሚስትና ልጆቹ ሳይቀር አስከትሎ ወደ ሲናይ ወረደ፤ ዘጸ.ም.፲፰ ቁ.፪-፯ (18.2-7)

በዚያም ሥፍራ ሊቀ ካህናቱ ኢዮተር ከታህታይ ምሥር /ግብፅ/ ለመጡ እሥራኤሎች፤ እንደ ሕያው እግዚአብሔር ፈቃድ ከጥንት ሲያያዝ የመጣው እንደ ኢትዮጵያውያን ሥርዓት ነውር የሌለባቸውን ወይፈኖችና ጊደሮች በጉትና ፍየሎች፤ ለእግዚአብሔር የሚቃጠል በተራራው ሥር የነግህና የሠርክ መሥዋዕት አቀረበ፤ ዘፍ.ም.፰ ቁ.፳-፳፪ (8.20-22) ዘጸ.ም.፲፪ ቁ.፭-፳፬ (12.5-24) ወዘተ...

ማለትም የጠዋትና ዘጠኝ ሰዓት የድኅነት መሥዋዕት እንደአዘጋጀ መዝሙር ፳፰/28/, ፵፬/44/ ፻፴፭/135/ እና ፻፵፰ /148/ በመጨረሻም ልዩ የሆነ ጸሎት መዝ. ፷፯ (67) ከአለየ በኋላ ልዑል

እግዚአብሔር ከአማልክት ሁሉ እንደሚበልጥ አውቃለሁ አለ። ዘጸ.ም.፲፰ ቁ.፲-፲፪ (18.10-12)

ይኸውም በይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ለየት ባለ አቀራረብ በድጋሚ፤ ሊቀ ካህናትና ንጉሠ ነገሥት ኢዮተር ከታህታይ ግብጽ /ምሥር/ ወጥተው በሲናይ በረሃ ላይ የሰፈሩ አይሁዶች ከፍ ብሎ በአጭሩ ሆኖ እንደተጠቀሰው ሁሉ፤ እምነት ስላልነበራቸው ለሕያው እግዚአብሔር የሚቃጠል የጥዋትና የማታ መሥዋዕት አቅርቦና በዐይን አሳይቶ እንዳሳመናቸው አይካድም፤ ቢሆንም የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ይህ ታሪካዊ የሆነ ምሳሌ በመከተል እስከ ዛሬ ድረስ ፍሥክ ከሆነ የነግህ መሥዋዕት ፆም ከሆነ ደግሞ የ፱ኻ ሰዓት የሰርክ መሥዋዕት ታቀርባለች፤ ፩ኛ(1) ነገ.ም.፲፰ ቁ.፲፮-፵፩ (1.18.16-41) በተለይ ደግሞ ኪዳን ዘነግህ መሥዋዕት ዘሰርክ እያለች በመጸለይ ነው። ለዚህም ተረፈ መሥዋዕቱን አብረው ከኢትዮጵያውያኑ ጋር መብላታቸው በቂ የሆነ





ማስረጃ ነው። ዘጸ.ም.፲፰ ቁ.፲፪-፲፫ (18.12-13) ይመልከቱ።

እንዲሁም ደግሞ የመንግሥት ሥነ ሥርዓትና አስተዳደርም ስላልነበራቸው፤ ከላዕላይ ግብጽ /ምሥር/ ክወሰዳቸው በአምልኮተ ዐሐይ ቤተ መቅደስ ውስጥ ለሕያው አምላክ ያገለግሉ የነበሩ ካህናቶችና በቤተ መንግሥት የሚሠሩ የነበሩ መኳንንቶችን፤ ደግሞም ሙታደሮችና መኮንኖች አብዛኞቹን ከልጁና ከልጅ ልጆቹ ጋር የሙሴ ሕዝብ እንዲሆኑ በአንድነት ቆመቀላቀል ከሥልጣኑ ከፍሎ በመስጠት መንግሥትና የአስተዳደር ሕግ እንዲኖራቸው አድርጓል።

እንደገና ደግሞ ራሱ ኢዮተር ሙሴን ሕዝቡም አንተም ከጥዋት እስከ ማታ ድረስ ቁማችሁ አያለሁ ለምን ነው ብሎ ሲጠይቀው ሙሴም ችግራቸውን ለመፍታት ነው ብሎ ሲመልስለት ኢዮተርም መልሶ ይህ ነገር ላንተ አይሆንልህም ይከብድሃል፤ ካለው በኋላ?

ስለዚህ እኔ የምነግርህን ሁሉ ስማ እግዚአብሔርም ሥራህን ሁሉ የተቃና ያደርገዋል፤ መንግሥትህም

የፀና ይሆናል ከሕዝቡ ውስጥ <u>የሃምሣና የመቶ የሻለቃ</u> የሆኑትን መርጠህ ሹምላቸው በሕዝቡ ላይ እነርሱ ይፍረዱ አንኳሩን ዋናውን ፍሬ ነገር ወደ አንተ ያምጡልህ በማለት ነበር ኢዮተር ለሙሴ የሰጠው መመሪያ፤

ከላይ ሥርዓተ አምልኮ እንዳስተማረው አሁንም የአስተዳደር ሕግ ሥርዓተ መንግሥት በመስጠት አረጋግጦለታል።

ይሁን እንጂ ከታህታይ ግብጽ ወደ ሲናይ የመጡ አይሁዶች ትምህርት የሌላቸው ሸክላ ሠሪዎችና ግንበኞች ብቻ እንደነበሩ አይካድም፤

ነገር ግን የተማሩት ከላዕላይ ምሥር የመጡት ኢትዮጵያውያኑ ብቻ ሲሆኑ ሁለቱም ሕዝቦች በአንድ ላይ ተቀላቅለው ቤተ ፸ኤል በመባል በሙሴ መሪነት ፩ድ/1/ ሕዝብ ሆነዋል። ሊቀ ካህናቱና ንጉሠ ነገሥቱ ኢዮተር የእምነትና የመንግሥትን ሥርዓት ለማስተማሩ ዘጸ.ም.፲፰ ቁ.፩-፳፯/18:1-27/ ይመልከቱ።





ከአምልኮተ ፀሐይ ጀምሮ እስከ ብሉይ ኪዳን ድረስ ይቀርብ ለነበረው መሥዋዕት ማስረጃ በአሞሩ፣ ሕያው እግዚአብሔር በፀሐይ አምሳል ጨረሮቹ እንደሰው አምስት ጣት ያላቸው የሚመስል ሆኖ መሥዋዕቱን ተቀብሎ ለወደፊት ክርስቶስንና ሥነ ስቅለትን የሚወክለው "ኖ" ፊደል ይሰጥ እንደነበር እውነት ነው።

ይህም በእየፕራሚዱ በሥዕል ይታያል ከመሥዋዕቱም የተረፈውን ኢትዮጵያውያኑና እሥራኤላውያኑ አብረው እንደ በሉ እውነት እንደሆነ ባይካድም፤ ማስረጃው ከላይ ተጠቅሷል፤ ከዚያ በኋላ ኢዮተር ከወሰዳቸው ሕዝቦች አብዛኞቹን የሙሴ ሕዝብ አድርጉ በመተው ወደ ቤተመንግሥቱ ላዕላይ ምሥር /ግብጽ/ ከመመለሱ በፊት የሰጠው መመሪያ ከተጨማሪ ጋር በድጋሚ ለየት ባለ አቀራረብ እንደሚከተለው ነበር።

ይሁን እንጂ ኢትዮጵያውያኑና እሥራኤላውያኑ አብረው በጎብረትና በፍቅር በሲናይ በረሃ ላይ ለ፵/40/

ዓመታት ያህል ሲኖሩ፤ ሕያው እግዚአብሔር ከታህታይ ግብጽ /ምሥር/ ከመጡት ከእሥራኤላውያኑ ወገን የሆኑት ወደ ምድረ ርሥት ከንዓን እንዲገቡ ስላልፈቀደ በሲና በረሃ ላይ ሙሴን ጨምሮ አሸዋ በልቷቸው ነው የቀሩት፤ ፵/40/ ዓመት የተቀመጡበት ዋናው ምክንያት ደግሞ ሕያው እግዚአብሔር በእድሜያቸው እንጂ ያለዘመናቸው እንዲቀስፋቸው ስላልወደደ ሲሆን፤

ለ፵/40/ አመታት ያህል በሲና በረሃ ላይ ከተቀመጡ በኋላ እንደገና በ፵፰ኛው /48/ ዓመት ከእሥራኤላውያኑ ዘር ሳይሆን ነገር ግን ሕዝበ ፳ኤል ተብለው የተመረጡት ከኢትዮጵያውያን ዘር የሆኑት ኢያሱና ካሌብን ከሌሎች ፮ት /8/ ሰዎች ጋር አድርጎ ኢየሩሳሌም ገብተው የከንዓን ምድር እንዲወርሱ አደረጋቸው።

ይህም በዘጸአትና በዘኁልቁ ላይ ታሪኩን በሙሉ ሣይሆን ነገር ግን በተፋለሰ መልኩ ተጽፎ ይገኛል፤ ይህም በብራናው ሣይሆን በታተመው መጽሐፍ ቅዱስ ማለቴ መሆኑን አይዘነጋም።





ቢሆንም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ የምታገለግለው ሁለተኛዋ የቃል ኪዳን ሀገር ደግሞ ከላይ አስቀድሞ በአጭሩ እንደገለጽኩት ሁሉ በእየክፍለ ሀገሩ በሙሉ፤ በአውራጃውና በወረዳው ሳይቀር በቀን አራቱም አየር ንብረቶች የሚፈራረቁባት፤ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ቤተሰብም በነቢዩ በኤርምያስ ትንቢት መሠረት ፬ት/4/ ዓይነት የተለያዩ አበባ ቀለም የሆኑ ሕዝቦች የሚገኙባት ሀገር ኢትዮጵያ ናት።

እንዲሁም ደግሞ አስቀድሜ ከላይ ድንቅነሽ ወይም ሉሲ፤ አዳምና ሔዋን ከሚለው ንዑስ ርዕስ ጀምሮ እንደ አብራራሁት ሁሉ፤ የመጀመሪያዎቹ የሰው ዘር ሁሉ እባትና እናት የሆኑ የተገኙባትና የተፈጠሩባት፤ የግዮን ወንዝ ዙሪያዋን ከቦ የሚያጠጣት ኤደን ገነት ኢትዮጵያ እንደሆነች አይካድም። ዘፍጥረት ም.፪ ቁ. ፲-፲፭ /2:10-16/ ይመልከቱ።

ስለዚህ መጠነኛ የሆኑትን ሳልጠቅስ፤ ፱/9/ ሀገር አቋራጭ የሆኑ ትላልቅ ወንዞች የሚመነጩባት ስትሆን፤ ነገር ግን ጥሩ የሆነ መሪ ስለማይበቅልባት ለሕዝቦቿ በቂሙ የነጎት ገሀነም ሆናባቸው ትኖራለች፤

በጣም የሚያስገርመውና የሚያሳዝነው ደግሞ በእየጊዜው የተነሱና የሚነሱ አምባገነን የሆኑ የባዕድ ቅጥረኞች ወፍአራሽና ማንዘራሽ የሆኑ መሪዎቿ ምክንያት ሕዝቡን በጎሳና በቋንቋ በሃይማኖት እየከፋፈሉ ተገቢ ያልሆነ ጦርነት በማስነሳት ሲያፋጁት ይኖራሉ፣ ገነት መሳይ ሲያልናት ይሏችኋል። ይህ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የሰቆቃ ኑሮ ነው።

በጣም ያሳዝናል፣ በተለይ ደግሞ እናት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ሙሉ በሙሉ በራሺያና በአሜሪካ በእንግሊዝ በባዕድ አረመኔ ጉማግንጎች መዳፍ ውስጥ የገቡት ከንጉሡ ጀምሮ በደርግና በኢሕአዴግ የአገዛዝ ዘመን መሆኑን አይካድም። ሕያው እግዚአብሔር መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ምሕረቱን በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ ያፍስስ አሜን።

አባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ

፲፱፻፺፮-፲፱፻፺፯ /1995-1996/ ዓ.ም.





# ምዕራፍ ፬ /4/

## መ. አጭር የታሪክ መልስና እምነት ምሥጋና፤ በገና በኢትዮጵያ፤

### 1.ሀ. ቅዱስ ዳዊትና በገናው

#### ሀ. በ፭ሺ፬፻፶ /5450/ ከ.ፊ. /B.C/

A. ለመጀመሪያ ጊዜ የበገና መደርደር የተጀመረው በኢትዮጵያ በአምልኮተ ዕሐይ በካራን ቤተ መቅደስ ሲሆን፤

ለ. ደግሞም በ፫ሺ፱፻፶ /3950/ ከ.ፊ. /B.C/

B. ለሁለተኛ ጊዜ በላዕላይ ምሥር/ግብጽ/ በጥንት ኢትዮጵያ በአምልኮተ ዕሐይ በሚታመንበት የኖራሚድ ቤተ መቅደስ ውስጥ ነው።

ሐ. እንዲሁም በ፩ሺ፭፻ /1500/ ከ.ፊ. /B.C/

C. ለሦስተኛ ጊዜ በኢየሩሳሌም ከተማ፤ የነገሠው በትውልድ ሐረጉ ኢትዮጵያዊ የነበረው ቅዱስ ዳዊት አሥር ፲ /10/ አውታር ባለው በገና በመደርደር፤ ለሕያው እግዚአብሔር የምሥጋና መዝሙር ያቀርብበት እንደነበረ እውነት ነው።

በጣም የሚያስገርመውና የሚያሳዝነው ደግሞ በእየጊዜው የተነሱና የሚነሱ አምባገነን የሆኑ የባዕድ ቅጥረኞች ወፍአራሽና ማንዘራሽ የሆኑ መሪዎቿ ምክንያት ሕዝቡን በኑሳና በቋንቋ በሃይማኖት እየከፋፈሉ ተገቢ ያልሆነ ጦርነት በማስነሳት ሲያፋጁት ይኖራሉ፤ ገነት መሳይ ሲያልናት ይሏችኋል። ይህ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የሰቆቃ ኑሮ ነው።

በጣም ያሳዝናል፤ በተለይ ደግሞ እናት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ሙሉ በሙሉ በራሺያና በአሜሪካ በእንግሊዝ በባዕድ አረመኔ ጉማግንጉጎች መዳፍ ውስጥ የገቡት ከንጉሡ ጀምሮ በደርግና በኢሕአዴግ የአገዛዝ ዘመን መሆኑን አይካድም። ሕያው እግዚአብሔር መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ምሕረቱን በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ ያፍስስ አሜን።

አባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ

፲፱፻፺፮-፲፱፻፺፯ /1995-1996/ ዓ.ም.





# ምዕራፍ ፬ /4/

## መ. አጭር የታሪክ መልስና እምነት ምሥጋና፤ በገና በኢትዮጵያ፤

### 1.ሀ. ቅዱስ ዳዊትና በገናው

#### ሀ. በ፭፻፶፬ዓ.ዓ /5450/ ከ.ፊ. /B.C/

A. ለመጀመሪያ ጊዜ የበገና መደርደር የተጀመረው በኢትዮጵያ በአምልኮተ ፀሐይ በካራን ቤተ መቅደስ ሲሆን፤

#### ለ. ደግሞም በ፫፻፶ዓ.ዓ /3950/ ከ.ፊ. /B.C/

B. ለሁለተኛ ጊዜ በላዕላይ ምሥር/ግብጽ/ በጥንት ኢትዮጵያ በአምልኮተ ፀሐይ በሚታመንበት የኦራሚድ ቤተ መቅደስ ውስጥ ነው።

#### ሐ. እንዲሁም በ፩፻፭ዓ.ዓ /1500/ ከ.ፊ. /B.C/

C. ለሦስተኛ ጊዜ በኢየሩሳሌም ኩሎማ፤ የንጉሡ በትውልድ ሐረጉ ኢትዮጵያዊ የነበረው ቅዱስ ዳዊት አሥር ፲ /10/ አውታር ባለው በገና በመደርደር፤ ለሕያው እግዚአብሔር የምሥጋና መዝሙር ያቀርብበት እንደነበረ እውነት ነው።

ስለዚህ አባቶቻችን ከክርስቶስ ልደት በፊት ጀምሮ ይህ ሃይማኖታዊና ታሪካዊ የሆነ ምሳሌ ተከትለው መዝሙረ ዳዊትን ለብቻው በተለያዩ ሐረጉችና በሥዕል አስገጠው ቅዱስ ዳዊትን ከእነ በገናው ከመጀመሪያው ገጽ በሥዕል አስገብተው በብራና በአስደናቂ ሁኔታ በእጅ አጽፈውና በዘመናዊ መኪና አሳትመው በተለይ አስጠርዘው የሚጸልዩ ከዓለም ሕዝብ ውስጥ ኢትዮጵያውያን ብቻ እንደሆኑ እስከ ዛሬ ድረስ በዐይን የሚታይ ስለሆነ አይታበልም።

፩ኛ./1/ የበገና ክሮች ወይም አውታሮች በ፲ቱ/10/ ቃላት የተመሰሉና /የተሰየሙ/ ሲሆኑ እነዚህም በጽላቱ ወይም በታቦቱ ላይ የሚጸፉ፣ <u>አልፋ፣ ወየ፣ ቤጣ፣ የውጣ፣</u> የሚባሉት ናቸው።

እንዲሁም ደግሞ እያንዳንዱ የበገና አውታር ስም በመሆን በቁጥርና በፊደል ለእየብቻ ሲተነተኑ፣

A. <u>1.፩.አ. 2.፪.ል. 3.፫.ፋ. 4.፬.ወ. 5.፭.የ. 6.፮.ቤ.</u>





<u>7.፯.ጣ. 8.፰.የ. 9.፱.ው. 10.፲.ጣ.</u> ይሆናሉ።

እንዲሁም በፊደላት ብቻ የበገናው አውታሮች ስም በመሆን ያለ ቁጥር ሲገለጡ ደግሞ

B. አ. ል. ፋ. ወ. ያ. ቤ. ጣ. የ. ው. ጣ. ናቸው።

ትርጉማቸው በክፊል. <u>አልፋ.</u> ምሥራቅ፤ <u>ወየ</u> ምዕራብ፤ <u>ቤጣ.</u> ሰሜን፤ <u>የውጣ.</u> ደቡብ፤ ማለት ሲሆን፤

እንደገና ደግሞ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ በቅድስት ድንግል ማርያምና በ፲፪(12) ሊቃነ መላእክት ይመሰላሉ ወዘተርፈ።

፪ኛ/2/ የበገና አውታሮች ወይም ክሮች እንደገና በ፲ሩ /10/ ቃሉችና በ፫ት/3/ ዓይነት የቅዱስ ያሬድ የዜማ ምልክቶችን የመሰላሉ።

እነዚህም ግዕዝ፣ አረራይ፣ ዕዝል፣ ሲሆኑ አሁንም እነዚህ በእያንዳንዱ የበገና ክር በስምነት ሲወከሉ በቁጥርና በፊደል በዝርዝር ለእየብቻም ሲተነተኑ፣ እንደሚከተለው ይሆናሉ።

A. 1.ዕ.ግ. 2.ይ.ዕ. 3.ቮ.ዝ. 4.ዎ.አ. 5.ሯ.ረ. 6.ጀ.ራ. 7.ጀ.ይ. 8.ጀ.ዕ. 9.ፀ.ዝ. 10.ፐ.ል. ናቸው።

እንደገና በፊደላት ብቻ ያለቁጥር ሲፃፉ ደግሞ፣

B. ግ. ዕ. ዝ. አ. ረ. ራ. ይ. ዕ. ዝ. ል.

ይሆናሉ ማለት ነው።





## የቅዱስ ያሬድ የዜማ ዓይነትና ምሳሌያቸው፤

እነዚህም ቃላት ግዕዝ፣ አረራይ፣ ዕዝል ሲሆኑ ትርጉማቸው ደግሞ ግዕዝ በአብ፣ አረራይ በመንፈስ ቅዱስ፣ ዕዝል በወልድ በእመ-በርሃን እንደገና ደግሞ በበራሪ ፫ት(3) ዓይነት ወፎች በተመሰሉ በሚካኤል፣ በገብርኤል፣ በሩፋኤል፣ ይመሰላሉ ወዘተርፈ።

እንዲሁም ደግሞ በብሉይ ከዳን ገዜ የነበሩ የዜማ አይነቶች ግዕዝና አረራይ ብቻ ሲሆኑ ዕዝል የመጣው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ሆኖ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከተወለደ በኋላ በቅዱስ ያሬድ ገዜ መሆኑን የተረጋገጠ ቢሆንም በዚህ ምክንያት ነው፣ ዕዝል ከላይ የስም ተራውን ሳይጠብቅ መንፈስ

ቅዱስን አልፎ በወልድ የተሰየመው በማለት በትህትና አስገነዝባለሁ።

እንደገና ደግሞ ፲ሩ/10/ የበገና አውታሮች ወይም ክሮችን የሚወክሉ በ፲ቱ /10/ ቃላት ማለትም በጽላቱ ወይም በታቦቱ ላይ የሚጸፉ አልፋ፣ ወይ፣ ቤጣ፣ የውጣ፣ የአምላክ ነቡዕ /የምሥጢር/ ስሞች ሲሆኑ፣

ደግሞም እንዲሁ በቅዱስ ያሬድ የዜማ ምልክቶች የተመሰሉ 10/፲ሩ/ የበገና አውታሮችን የሚወክሉ ግዕዝ፣ ዕዝል፣ አረራይ የተባሉ እነዚህም የአምላክ ስም ናቸው፣

ሁለቱም የአምላክ ስሞች በፊደልና በቁጥር ሲተነተኑ ሁሉም አሥር በመሆን ፲/10ሩን/ የበገና





አውታሮች ወይም ክሮችን እንደሚወክሉ የታወቀ ነው።

ስለዚህ ሁለቱም የአምላክ ስሞች በመሆን እንደ ቢሆኑም በትርጉም ግን የማይገናኙ የተለያዩ መሆናቸውን ለአንባቢያን አሳስባለሁ።

ትርጉማቸው የተለያየ መሆኑንም አስቀድሞ በመነሻው ላይ በእያንዳንዳቸው ተገልጿል።

ይሁን እንጂ ከላይ በተደጋጋሚ ስለ ፲ሩ/10/ የቅዱስ ዳዊት የበገና አውታሮች ወይም ክሮች በምን እንደሚመሰሉና እንደሚወከሉ ከአነማስረጃውና አመጣጡ ጭምር የቀረበ ስለሆነ በማስተዋል ይመልከቱት።

እንደዚሁም ደግሞ በመጽሐፈ ሄኖክ ዘአዩኅይ ራኁኤል ስለበገና ሲያብራራ ቅዱሳን የሆኑ መላእክት

በጽርሐ አርያም መንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ለሕያው እግዚአብሔር ፳፬/24/ ሰአታት ሙሉ ምሥጋና የሚያቀርቡበት የተቀደሰ መሣሪያ ነው በማለት በሚገባ አረጋግጧል።

ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት ላይ ከፍ ብሎ በፊደላትና በቁጥር ሁለት፤ ሁለት ጊዜ በተደጋጋሚ እንደተብራራው ሁሉ፤

<u>የመጀመሪያው</u> የታቦተ ጽዮን ምስል በሚገኘው በካራን ቤተ መቅደስ ከ፭፻፵፪/5400/ ከ.ፈ./B.C/ በኢትዮጵያ የተመሰረተ መሆኑን በታወቅም፤

<u>ሁለተኛው</u> የታቦተ ጽዮን ምስል በነበረባት በጥንት ኢትዮጵያ በላዕላይ ግብጽ በ፲፰፻፺፱ /3950/ ከ.ፈ. /B.C/ ጀምሮ በገና ለእውነተኛው አምላክ ምሥጋና የሚያቀርብበት መሣሪያ መሆኑን በደንብል





/ፓፒረስ/ የተጻፈ ምሥጢረ ካህናት ዘአዶናይ ራፋኤል ያረጋግጥልናል።

ስለዚህ ከዚህ በላይ ከተገለጸው ጊዜና ዘመን ጀምሮ ሳይቋረጥ ሲያያዝ መጥቶ በገና ለሕያው እግዚአብሔር ብቻ ምሥጋና የሚቀርብበት የተቀደሰ መሣሪያ መሆኑን በመቁጠር በእናት ኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና በሌላ መንግሥት በአጼ ግሥት ጊዜ ብቻ የሚያረያርና የሚዘመር ሲሆን፤

በተለይ ደግሞ በወፀይ ጾምና በገና የልደት ጾም፤ በየመ ፍልሰታ ጊዜ ፍጹም ሰው ለሆነው ለእውነተኛው አምላክ ሕያው እግዚአብሔር ለመድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስና ለእናቱ ለቅድስት ድንግል ማርያም እንዲሁም ለመላእክት፤ ለጻድቃንና ለሰማዕታት፤ ለነቢያትና ለሐዋርያት፤ በክብረ በዓላቸው እነሱን

በማመለክት ለዕለቱ ተስማሚ የሆነ መዝሙር በማዘጋጀት ይዘመርላቸዋል።

የበገናው መዝሙር አብዛኛው መንፈሳዊ ሆኖ ነገር ግን ከሀናቱንና ነገሥታቱን ልዑላኖቹንና መኳንንቱን በቅኔ ግጥም የሚወጋና የሚኮንጥ አልፎ አልፎ እንዳለበት ባይታበልም፤

በገናውን የሚደረድሩት የነበሩ ደግሞ የዛሬን አያድርገውና አብዛኞቹ ካህናትና ነገሥታት ልዑላንና መኳንንት የሴት ወይዘሮዎች እንደነበሩ በሁሉም ሰው ዘንድ የታወቀ ስለሆነ አይታበልም።

ስለዚህ በገና የተለያዩ ቅርፆችንና የበገናው ክሮች ወይም አውታሮች ፲/10/ መሆናቸውን የገለጸልን ደግሞ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ሁሉ የትውልድ ሐረጉ ኢትዮጵያዊ ሆኖ በኢየሩሳሌም





የነገሠው ልበ አምላክ በመባል የሚታወቀው ቅዱስ ዳዊት በ፩ሺ፬፻ /1400/ ከ.ፊ. /B.C./ እንደሆነ እውነት ቢሆንም፣ ቅዱስ ያሬድም በዜማ መልክቶቹ አረጋግጠልናል።

ነገር ግን ከዚያ በፊት የነበረው የበገና ቅርጽ የተለያየ መሆኑን እንደተጠበቀ ሆኖ ክሮቹ ወይም የአውታሮቹ ቁጥር ግን /7/፯ት፣ /10/፲ር፣ /12/፲፪ት፣ /14/፲፬ት፣ /24/፳፬ት እንደ ነበሩ መጽሐፈ ምሥጢረ ካህናት ዘአዶናይ ራፋኤል በሚገባ ያስረዳናል።

ስለዚህ በገናና መዝሙረ ዳዊት ለኢትዮጵያውያን የተቀደሱ የጸሎትና የምሥጋና መሣሪያዎች መሆናቸውን የተረጋገጠ እውነት ነው።

ይሁን እንጂ በቢ.ቢ.ሲ /B.B.C/ ቴሌቪዥን የተጠየቅነው በድጋሚ ከእናት ኢትዮጵያ ውስጥ

አባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስና አቶ ዓለሙ አጋ ብቻ ብንሆንም፤ እኔ አባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ የተጠየኩት ስለ መዝሙረ ዳዊት ታሪካዊ አመጣጥና ሌላም የተለያዩ በጣም ጠቃሚ የሆኑ ጥያቄዎች ሲሆን፤

እንዲሁም ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ የኔ ልጅ የሆነ የበዓና ሊቅ ክቡር አቶ ዓለሙ አጋ፤ የተጠየቀው ስለ በዓና ድርደራና የዜማው ታሪካዊ አመጣጥና ሌሎች የተለያዩ ጥያቄዎች እንደሆኑ አይካድም።

ክቡራን አንባብያን የሁለታችን ቃለመጠይቅ በቪዲዮ ተቀርጾ በቢ.ቢ.ሲ./B.B.C/ እና በሲ.ኤን.ኤን. /C.N.N/ እየታየ ቢሆንም እዚህ ላይ በጥናቴ መጨረሻ ስለ በዓና ታሪካዊ የሆነ አመጣጥ በአጭሩ ሆኖ የገለጽኩት ለመግቢያና ለመታሰቢያ ያህል





ቢሆንም ነገር ግን ጠለቅ ያለ ምርምራዊ የሆነ ዝርዝር ጥናቱን ደግሞ ለባለሞያዎቹ የተውኩት መሆኑን በአክብሮት አስገነዝባለሁ።

**<u>ማስረጃ ስለበዓና ከደራሲው</u>**

መዝ. ፻፵፫፣ ፱፡-፲/143፣9-10/

መዝ. ፴፪፣ ፩-፬ /32፣ 1-4/

መዝ. ፻፶፣፫-፮ /150፣ 3-6/

መዝ. ፺፩፣፩-፬ /91፣1-4/

፩ኛ ዜና መዋ.ም.፲፣፮-፯ /10፣6-7/

፪ኛ ዜና መዋ. ም. ፳፱፣፳፭-፳፮ /29፣25-26/

፩ኛ ዜና ም.፲፭ ቁ.፲፱-፳፱ /15፣19-29/

፩ኛ ዜና ም. ፲፮፣ ፭-፯፣ ፳፰-፵፫ /16፣5-7፣ 28-43/

መዝ. ም.፹ ቁ.፩-፬ /80፣1-4/

መዝ. ም. ፻፵፮፣ ፯-፲ /146፣7-10/

፪ኛ. ሣሙኤል. ም.፭፣ ፬-፮ /5፣4-6/

አባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ

## ስለበገና ጥቅስ

## ከባለሙያው ከዓለሙ አጋ በከፊል፤

ዘፍ.ም.፬ ቁ.፳፬ /4:24/

1ኛ ሣሙኤል ም. ፲፮ ቁ.፲፮-፳፫ /16:16-23/

2ኛ ሣሙኤል ም.፮ ቁ.፭ /6:5/

ራእይ ም.፲፬ ቁ. ፪ /14:2/

ሌላም አለ ለጊዜው ግን እነዚህ ይበቃሉ።

አባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ፤





2. ሐ. **<u>አጭር የእምነት ርዕስ በኢትዮጵያዊ ኦቪ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በመለኮት በባሕርይ በሕልውና ፅድ አምላክ ናቸው።</u>**

ሀ. ትክክል የሚሆኑ በመለኮት ፩ድም ፫ት ናቸው።

ለ. እኔ እውነተኛ መንገድ ነኝ በእኔና በአብ በመንፈስ ቅዱስ መካከል ልዩነት የለንም በስም ፫ት ስንሆን ፩ድ እግዚአብሔር ነን አላቸው።

ሐ. ፫ት፣ ሲሆን ፩ድ ፩ድ ሲሆን ፫ት የሆነ ፈጣሪ /አምላክ/።

መ. መለኮት በተዋሕዶ ፍጹም ሰው ሲሆን፣ ሰውም በተዋሕዶ ፍጹም መለኮት ነው።

ሠ. ጽዮን ታቦት፣ ጽዮን ተራራ፣ ጽዮን መጠጊያ፣ ጽዮን ማደሪያ፣ ጽዮን መድኃኒት፣ ጽዮን እናታችን ቅድስት ማርያም መማፀኛ።

1. ካመንህ ይህ እውነተኛ እምነት ነው።
2. እነዚህ ከዚህ በላይ የተገለጹት የእምነት ቃላቶች ቅዱስ ማርቆስ ኢትዮጵያዊ ነው ከሚለው መጽሐፍ ነው።

በአባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ
፲፱፻፹፬ /1984/

## 2.C. SHORT TITLE OF FAITH IN ENGLISH

**The Father, The Son, The Holy Sprit, by the Divine, by the Nature, by the Existence or by the Almighty, are one (1) God.**

A. The equals are in divine, Unity and Trinity. (1 and 3)

B. I am the right way, in me, and in Father, in the Holy Sprit, no differences between us, in name we are three, (3) and (1) God He said (3 and 1).

C. The Trinity (3) in Unity, (in 1) and the unity, (1) in Trinity, (in 3) is God the creator.

D. The Divine in Unity became a Perfect Man, and the Man in Unity is a Prefect Divine (God).

E. Zion the Ark of covenant, Zion the mountain, Zion the shelter and the forest, Zion the habitation, Zion the medicine, Zion our mother virgin St. Mary, appeals in our Name.

1. If you believe, this is the true Faith.
2. These words of faith mentioned above are from the book "Saint Mark is an Ethiopian".

**By Abba Tesfa Selassie Moges 1984**
**Addis Ababa**





## 4.መ. አጭር መልስ፤ ለኢ.ኤ.ዋ.ሲ፡ ባጅ፡

በእናት ኢትዮጵያ ብቻ በ፲፫ /13/ መሮች በእየቀኑ የሚነበቡ የቅዳሳንና የመላእክት፤ የሰማዕታትና የጻድቃን፤ የነገሥታትና የመኳንንት፤ እንዲሁም የዘመናት ቀመርና በጣም አስደናቂ የሆነ ታሪክን የያዙ በእጅ የተጻፉ የብራና ፬ት /4/ የሥንክሣር መጻሕፍት፤ በብሪትሽ ሙዚየም የምሥራቅ ክፍል ቁ. 660-661 በሰጡት መለያ ቁጥር መኖሩ የተረጋገጠ ሲሆን፤ እንደአጋጣሚ ሆኖ ይህ ቁጥር መጽሐፈ ሥንክሣር በኢትዮጵያውያን ከ500-661 ዓ.ም. በእጅ የተጻፈበት ዘመን ነው።

የሥንክሣር መጻሕፍቶቹ የያዙት ታሪክ በዚያን ዘመን የክርስትና እምነት የተጀመረባቸውና በብዛት የተስፋፋባቸው ሃገሮች እንደሆኑ ባይታበልም፤ እነዚህም የቅዳሳን ታሪክ የሆነ ሥንክሣር የተጻፈበት ሃገር ኢትዮጵያና ዘርፎቿ፤ ምሥር እንዲሁም ኢየሩሳሌም፤ በጠቅላላው መካከለኛው ምሥራቅ ሲሆኑ፤ ከአውሮፓም ሮም ግሪክና አርመን ናቸው፤ የሥንክሣር መጽሐፉ የእነዚህን ሁሉ ሀገሮች የቅዳሳን ታሪክ በመጠኑ የሚዳስስ ሲሆን፤

ስለዚህም ነው ኢትዮጵያውያን አባቶችና ሊቃውንት በሥንክሣሩ ውስጥ የሚገኙ ልዩ ልዩ የሆኑ የባዕድ ስሞችን ያስገቡበት ዋና ምክንያት ደግሞ ሐዋርያት ዲድስቅልያና ቀሌምንሶስ (ሲኖዶስ) በሚባሉ የእምነትና የቀኖና መጻሕፍቶቻቸው ውስጥ

የእየሀገሩ ሰዎች ሁሉ የክርስትና ስም ሆኖ እንዲጠሩበት በወሰኑት መሠረት መሆኑን አይካድም፤ ስለዚህ የብዙ ሰማዕታትና የጻድቃን ስሞችን የያዘ መጽሐፍ ነው።

<u>ነገር ግን</u> ኢ.ኤ. ዋሊስ /ባጅ/ የተባለ ግለሰብ፤ በ፲፱፻፺፮ /1976/ እ.ኤ.አ. መጽሐፍቶቹን ከግዕዝ ቋንቋ ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ተርጉሜያቸዋለሁ ብሏል፤ ሙከራው የሚደነቅ ሲሆን እኔ ግን በትክክል እንዳልተተረጐሙ ነው የምረዳው።

<u>የተርጓሚው</u> ግለሰብ እንደገና ድጋሚ የሆነ ስህተት ደግሞ፤ ሥነክሣሮቹ ወደ ግዕዝ የተተረጎሙት ከግብጽ፤ ከሶርያ፤ ከግሪክ ነው ብሏል፤ ያልሆነውን ሆነ ማለት ቋንቋውን በትክክል እንዳልተረዳው ከመግለጹም በላይ ከቅንአትና ምቀኝነት አልፎ ሌላ መሆን አይችልም፤
እውነት ከሆነ ደግሞ ግዕዙ ተተረጎመባቸው የተባሉ መጻሕፍት የሚገኙበት ቦታና ቁጥርም ጭምር ማለትም ከፍ ብሎ የግዕዙን መጽሐፍ ያገኘበትን እንደጠቀሰው ሁሉ፤ አሁንም ግዕዙ ተተረጐመባቸው የተባሉት መጽሐፍት የሚገኙበትን ቦታና ሀገር ሳይቀር፤ መግለጽ ነበረበት፤ ነገር ግን ስለሌሉና ሐሰት ስለሆነ አልተጠቀሱም።

<u>ለዚህም መልስ፤</u> ለባዕዶችም ሆነ ለወገኖች የማስነገዝበው ዋና ቁም ነገር፤ በመጻሕፍቶቹ ውስጥ ያለው የግዕዝ ቋንቋ በትክክል ከኢትዮጵያዊ ባሕርይ





የፈለቀ የመጀመሪያ ምንጭ የሆነ ቋንቋ ነው እንጂ የትርጉም ቃል ያለመሆኑን በሚገባ ጥርት አድርጎ ሥንክሣሩ ስለሚያስረዳ ከገባቸው እንደገና እንዲያነቡት እጠይቃለሁ።

<u>የተከበራችሁ</u> አንባብያን፤ ከላይ የሥንክሣሩ መጻሕፍት ተተርጎመባቸው የተባሉ ሀገሮች እንደ ኢትዮጵያ ፲፫ /13/ ወሮች የሌላቸው ከመሆኑም በላይ እንኳንስ ከሯያ እስከ ፭፻፷፩ /500-661/ ዓ.ም. ቀርቶ በአሁኑ በ፳፩ኛው /21/ ክፍለ ዘመን ውስጥም ቢሆን የእየወሩ ሆኖ በእየቀኑ የሚነበብ መጽሐፍ ፈጽሞ እንደሌላቸው የተረጋገጠና የታወቀ ስለሆነ የተተረጎመ ነው የሚለው ቃል ፈጽሞ የሐሰት አነጋገር መሆኑን በሚገባ አረጋግጣለሁ።

በተጨማሪ በኢትዮጵያ ፲፫ /13/ ወሮች ስንል ፲፪ቱ /12/ ወሮች እያንዳንዳቸው ፴ /30/ ቀናት ሲኖራቸው ፲፫ኛው /13/ ወር ጳጉሜን ግን ለ፫/3/ ዓመታት ፭/5/ ቀን ሲኖሩት በ፬ኛው /4/ ዓመት ደግሞ ፮/6/ ቀን አለው።

የ፲፫ቱ /13/ ወሮች ትርጉም ደግሞ በ፲፫ቱ /13/ የኢትዮጵያውያን ነገሥታት ስም የተሰየመ ነው፤ ፲፪ቱ /12/ ነገሥታት እያንዳንዳቸው ፴/30/ ዓመት ወይም ቀናት ሲነግሡ፤ ነገር ግን ጳጉሜን በሚል ስም የነገሡ ፪/2/ት ወንድማማቾች ነገሥታት አንዱ ፭/5/ ዓመት ወይም ቀን ሲነግሥ፤ ሌላው ደግሞ ፮/6/ ዓመት ወይም ቀን ነግሷል፤ ሮማውያንም ከእኛ

በመውሰድ የወሮቻቸውን ስም በነገሥታቶቻቸው ስም እንደ ኢትዮጵያውያን ለመቀመር ሞክረው ሳይሳካላቸው ቀርቷል።

## አንባቢያን ሆይ፤

ሌላው በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ ስለተአምረ ማርያም ነው፤ ይኸውም ከዓረብኛ ወደ ግዕዝ የተተረጐመ ተብሎ ነው የሚነገረው፤ ዓረቦች እንኳንስ በዚያን ዘመን መጽሐፉ ሊኖራቸው ቀርቶ በአሁኑ ጊዜም ቢሆን መጽሐፉ የላቸውም፤ ጨርሶ መኖሩንም እያውቁትም፤ በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኘው ዓረፍተ ነገርና ቃላትም ከዓረብኛ ቋንቋ ጋር አይገናኝም።

ስለ እመብርሃን ሥራ በመጠኑ የሚናገረው ተአምረ ማርያምን መጽሐፍ የደረሱና የጻፉ የሐይቅና የዘመዶ ገዳማት የነበሩ አባ ሚካኤልና አባ ገብርኤል የሚባሉ መነኮሳት ናቸው። መቃብራቸውም መጽሐፉ በተጻፈበት የተቀደሰ ሥፍራ በየጁ ገነተ ልዑል ጉባርጇ ማርያም ይገኛል።

ለወደፊት ራሱን በቻለ ርዕስ ይቀጥላል።

አባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ፤
፲፱፻፺፭ /1991





## 4.D. A Short Answer For E.A.Walis Badge

**The Librarian**
**British Council**
**Addis Ababa**

**Dear Sir,**

Aba Tesfa Silassie Mogus a noted Ethiopian scholar and monk has a strong objection against the assertion on the source of the translation of the Ethiopic Synaxarium /መድሐፈ ሥንክሣር/ by E.A. Wallis Budge, being stated that the Ethiopic Geeze were translated from Arabic, Greek, Syriac.

His reasons for his objection is that the countries mentioned as the origin of the Synaskarium do not have 13 months in their calendar. Therefore, since they could not be able to base the histories of the martyrs, saints archangels etc. to be read throughout the year on a daily basis by dividing the year into 13 months and each month into 30 days and the 13th month Pagumen into 5 days and in leap year into 6 days.

The meanings of the 13 months are as the following in short. According to the ancient Ethiopian manuscript book of glory of the kings. The memory to the 13 very earliest the Ethiopian kings, called by their names the

13 months or years stating from the first king September and to the last 2 brother kings called Pagumen.

Also another evidence according to the secret book of Adonay Raphael that tell us about the ancient history of Ethiopia, and the 13 months and years. The 12 kings are ruled Ethiopia each of them 30 days or years, in the 12 months. But from the 13th month and kings there are 2 brothers king in the same name called Pagumen, one of them ruled 5 days or years and the other one also 6 days or years.

Aba Tesfa further mentioned that he admires the British Museum for keeping the Ethiopic Geeze Senksar giving its library code 660, 61 upon which Mr. Budge have been able to translate it into the English language. Furthermore, Budge confirmed that the volumes of the Ethiopic Senkesar were produced written in parchment in Geeze, which he used for his translation.

Nevertheless, there was no mention either on a footnote or any other reference of the whereabouts of the original manuscripts he mentioned as the original source for the translation into Geeze. This by itself proves without any shadow of doubt of the non-





existence of the manuscripts to be the source of the Senkesar.
Therefore until such time that the so-called manuscripts are produced either from the British Library or any library in the world it will be concluded that it is pure fabrication.

From an Observer

እዚህ ላይ ደግሞ የክቡራን ኢትዮጵያውያን ወዳጆቼን ስም እጠቅሳለሁ፤

1.፩ኛ/ ክቡር አቶ በቀለ አሳምነውና

2.፪ኛ/ ክቡር አቶ አበራ ሞልቶትን፤

3.፫ኛ/ ለቅዱስ ሚካኤልና ገብርኤል ሩፋኤል ማኅበርተኞች በሙሉ፤

ከእነሚስቶቻቸውና ልጆቻቸው ጋር ረጅም እድሜ ከእንጀራ ጋር እንዲሰጣቸው ከልብ እመኛለሁ፤

አባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ፤

### 3.ሐ. አሳዕር ምስጋና ከቢ.ቢ.ሲ

British Broadcasting Corporation Broadcasting House Queen Margaret Drive Giasgow G12 8Dg
Telephone 0141 339 8844 Textphone 0141 357 4035

**BBC** Scotland
Arts & Factual Entertainment Television

11th August 2001

Dear Aba Tesfa

I just wanted to thank you very much for agreeing to be interviewed by professor Germain Greer for our network documentary programme on the Psalms of David in the Art That Shook the world series. It was a great pleasure to meet you and thank you for your hospitality. We felt interview was very valuable contribution to the programme and I do hope enjoyed the tape of the programme.

With best wishes

Joan Raba
Production Manager
*The Psalms of David*





# Title

## Who were the three wise men?

**The Four Questions for Abba Tesfa Selassie Moges, B.B.C. Film. About the three wise men and frankincense; for young children's program. November 18,1996.**

## Content

1. **Who were the wise men who visited Jesus in Bethlehem?**
2. **What is the story of their journey to Bethlehem? Did they follow a star?**
3. **Why did the wise men take gold frankincense and myrrh to Jesus?**
4. **Why is Frankincense used by the Ethiopian Tewahido Orthodox Church?**

**Thank you very much for your help with best wishes.**

**By, Bill Locke**
**B.B.C. Television – Scotland**

**This prudence questions is translated in to Ethiopic; by Abba Tesfa Selassie Moges, See next Page.**

# ሁለተኛ መጽሐፍ

## ሦስቱ ሰብአ ሰገሎች እነማን ነበሩ?


ስለ አራቱ ጥያቄዎች፣ በቢል ሉኬ ከቢ.ቢ.ሲ. ቴሌቪዥን ስለ ሦስቱ ጥበበኞች ሰዎችና የክርቤ ዕጣን ለወጣት ልጆች ዝግጅት፣ ለአባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ የቀረበ፣ ኖቬምበር ፲፰፣ ፲፱፻፺፮ /18፣1996 እ.ኤ/ ፱፣፲፱፻፹፱ ኅዳር /9፣1989 ዓ.ም./

## አርእስት

1. ሦስቱ ሰብአ ሠገሎች እነማን ነበሩ? ኢየሱስ ክርስቶስን እስከ ቤተልሔም ድረስ ሄደው የነበኑት?
2. ወደ ቤተልሔም የሄዱት የጉዟቸው ታሪክ ለምን ነበር? በእውነት ኮከቡን ተከትለው ነበር የሄዱት?
3. ሦስቱ ሰብአ ሠገሎች ወርቅ፣ ከርቤና ዕጣን ይዘው ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ የሄዱት ለምን ነበር?
4. ክርቤ በኢትዮጵያ ተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጥቅሙ ለምንድን ነው?

የጥያቄዎቹ ጥበብ
ትርጉም በአባ ተስፋ ሥላሴ





፩ኛ. የሰው ዘር መጀመሪያ ማን ነው፣
ድንቅነሽ (ሉሲ) አዳምና ሔዋን፣
የጥቁር ጠይም ኢትዮጵያውያን፣
ሀ. (ተዓምረኛዋ ዐይን በሕይወት ምስል ውስጥ)
2ኛ. Who is the origin of the man.
Dinkinesh (Lucy) Adam & Hewan. (Eve)
The black (brown) Ethiopians.
A. (The Mir[illegible] Eye in the symbol of life)



ይህ ቅዱስ ገብርኤል ነው::

በቅድስት ማርያም በግራ በኩል የሚሣለው::

This is St.GABRIEL Painting

By the Left side of St.MARY

ዳን.ም.፰.ቁ.፲፮.(8.16) ሉቃ.ም.፩.ቁ.፲፱.(1.19)



ይህ ቅዱስ ሚካኤል ነው::

በቅድስት ማርያም በቀኝ በኩል የሚሣለው::

This is St. MICHAEL Painting

By the Right side of St. MARY

ዳን.ም.፲.ቁ.፲፫,፳፩.(10.13,21.)ም.፲፪.ቁ.፩.(12.1.)



ከዳዊት መዝሙር አንድ ክፍል ከግጥም ጋር፡
From the Psalms of David one part with poem



፩. ቅድስት ድንግል ማርያም የመድኃኔ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ እናት፤
1. St. Vérgne Merry, the Mother of Salivation Jesus Christ.

# ሁለተኛ መጽሐፍ
## አርእስት
## አራቱ ጥያቄዎች፣ ከቢ.ቢ.ሲ. ቴሌቪዥን ስለ ጥበበኞች ሰዎችና ዕጣን ለወጣት ልጆች ዝግጅት፣ በቢል ሎኬ ለአባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ የቀረበ፣ኖቬምበር ፲፰፣፲፱፻፺፮ /18፣1996 እ.ኤ.አ/ ፱፣፲፱፻፹፱ ጎዳር /9፣1989ዓ.ም./ በኢትዮጵያ።

## የጥያቄዎቹ ጥበብ
## ትርጉም በአባ ተስፋ ሥላሴ

1. ሦስቱ ሰብአ ሰገሎች እነማን ነበሩ? ኢየሱስ ክርስቶስን እስከ ቤተልሔም ድረስ ሄደው የነበኑት?
2. ወደ ቤተልሔም የሄዱት የጉዟቸው ታሪክ ለምን ነበር? በእውነት ኮከቡን ተከትለው ነበር የሄዱት?
3. ሦስቱ ሰብአ ሰገሎች ወርቅ፣ ከርቤና ዕጣን ይዘው ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ የሄዱት ለምን ነበር?
4. ከርቤ በኢትዮጵያ ተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጥቅሙ ለምንድን ነው?

# አርእስት

## ሦስቱ ሰብአ ሰገሎችና ሁለቱ ልዑላን ኢትዮጵያውያን መሆናቸው ተረጋገጠ።


አጭር መልስ በአባ ተስፋ ሥላሴ ስለ አራቱም ጥያቄዎች፣ ከቢ.ቢ.ሲ. ቴሌቪዥን ስለ ተበበኞች ሰዎችና ለወጣቶች ዝግጅት፣ በቢል ሉኬ የቀረበ፣ ኖቬምበር ፲፰፣፲፱፻፺፮ /18፣1996/ በፊሪንጅ፣ ጎዳር ፱፣፲፱፻፹፱ /9፣1989 ዓ.ም./ በኢትዮጵያ።

ማውጫ

ክፍል አንድ

መግቢያ ---------- 5/ ፭
መቅድም ---------- 7/ ፯
ሀ. የትርጉም ዘዴ ---------- 9/ ፱
ለ. አጭር ታሪክ ስለ አይሹር ፩/1ኛ/ --10/ ፲
ሐ. ጥበበኞቹ ነገሥታት ማለት? --------15/ ፲፭
መ. አይቴ ብሔራ ለጥበብ ----------17/ ፲፯

ክፍል ሁለት

1. መልስ ስለ ጥያቄ፣ ቁጥር አንድ ------ 21/ ፳፩
ሀ. የነገሥታቱ ስምና የትውልድ ቦታ----- 26/ ፳፮
ለ. ኖስትርዳሞናስና የኢትዮጵያ ፲፱፻፶፬/1994--28/ ፳፰
ሐ. ስለ ሰብአ ሠገል መግለጫ ---------- 31/ ፴፩
1. መልስ ስለ ጥያቄ፣ ቁጥር ሁለት ------ 33/ ፴፫
2. መልስ ስለ ጥያቄ፣ ቁጥር ሦስት -------35/ ፴፭
3. መልስ ስለ ጥያቄ፣ ቁጥር አራት ------39/ ፴፱
ሀ. አጭር ምሥጋና ከቢ.ቢ.ሲ. ------45/ ፵፭


ማስረጃ/ዋቢ/፡አብሮ ከጥናቱ ጋር የተካተተ ነው።





## መግቢያ፤

በጣም ብዙ የሆኑ የዓለም ተመራማሪዎችና ሊቃውንት ምሁራን፤ አገር ጉብኝ የሆኑ /ቱሪስቶች/፤ በእየጊዜው የሚቀያየሩ የተለያዩ ሀገሮች አምባሳደሮችና ጸሐፊዎች/ዲፕሎማቲኮች/ እንዲሁም ደግሞ የተለያዩ የግል ተመራማሪዎችና ሰላዮች የሆኑ አጥኝዎች፤

የእናት ቤተክርስቲያናችንና የእናት ሀገራችንን ቅድመ ጥንታዊና ጥንታዊ ዘመናዊ ታሪክና በከርሠ ምድር ውስጥ የሚገኙ ልዩ ልዩ የሆኑ ማዕድናቷ ሳይቀር ከሞላ ጐደል ከፍ ብሎ በቅደም ተከተል የተጠቀሱ ሰዎች በእየሞያቸው የተለያዩና በሺ የሚቆጠሩ በጣም ጥልቅ የሆነ ምርምር የተደረገባቸው መጻሕፍት እንደ ጸራልን የተረጋገጠ የማይካድ እውነት ነው።

ስለዚህ እኔም ለእናት ሀገሬና ለእናት ቤተ ክርስቲያኔ የሚጠቅሙና እንዲሁም ደግሞ ለዓለም ታሪክ ጸሐፊዎች የሚረዳ የተዛባውን በትክክል

ከማስረጃ ጋር አርሜ አስተዋጽዖ የሚያደርጉ ብዙ የሆኑና የተለያዩ መጻሕፍቶችን አዘጋጅቼ በገንዘብ /ኢኮኖሚ/ እጦት ምክንያት ሳይታተሙ ተጠርዘው የተቀመጡ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ በአክብሮት አሳስባለሁ።

ቢሆንም ይህ ጥናት የተዘጋጀው ደግሞ እውነት ወዳጆች የሆኑ በዓለም የተዛባውን ታሪክ እንዲቃናላቸው ፈልገው፣ የወጣቶች ዝግጅት /ፕሮግራም/ በሚል ርዕስ፣ ይዘው ትክክለኛ የሆነ መልስ የሚሰጣቸውን ሰው በመፈለግ ላይ እንዳሉ፣ በአዩ ተሸመ ልሣኑና በወጣት ያሬድ ይፍሩ አማካኝነት ወደኔ ይዘዋቸው እንደ መጡ እውነት ሲሆን፣ ፈረንጆቹ ለሁላችን የላኩልን የምሥጋና ደብዳቤ ከቪዲዮ ክር ጋር በዚህ ጥናት ውስጥ በመጨረሻ ገጽ የቀረበ ስለሆነ ይመልከቱ። ስለዚህ በዚል ሎክ መሪነት ከቢ.ቢ.ሲ ስኮትላንድ ተነስተው እውነት ፍለጋ ኢትዮጵያ መጥተው ስለ ሠብዓ ሰገሌች ምንነት ላቀረቡልኝ ፬ት /4/ ዓይነት





ጥያቄዎች የሰጠኋቸው ጥናታዊ የሆነ መልስ፣ በቪዲዮ ቀርፀው ለዓለም ሕዝብ በኢንተርኔትና በሲኤን ኤን ያስተላለፉትን፣ ለወገኖቼ ይጠቅማል ብዬ በመገንዘብ፣ ከ፲ሩ (10) የቢ.ቢ.ሲ. (B.B.C.) ጥያቄዎች ከተዘጋጀው መጽሐፍ ጋር ጥያቄውም ተመሣሣይ በመሆኑ ፪ኛ/2/ መጽሐፍ በማድረግ ያቀረብኩት መሆኑን ለአንባብያን በትህትና አስገነዝባለሁ።

አባ ተስፋ ሥላሴ ምነስ

## መቅድም፤

ስለ ሰብአ ሠገል፤ ማለት ብልሆችና ጠንቋዮች፤ ወይም ጥበበኞች፤ በየእምነቱና ቋንቋው ሁሉ ብዙ የሆነ መላምት ተነግሯል ተጽፏልም፤ ከዚህ ሁሉ ማለትም ከተነገረውና ከተጻፈው ኃይለ ቃል ሁሉ እውነትም ሐሰትም እንዳለበት አይካድም።

ነገር ግን ማንኛውም ሰው ሁሉ እኔ ያልኩት ነው እውነት የሚል መሆኑንም የታወቀና የተረጋገጠ ሲሆን፤

የተደጋገመ ብዙ የሆነ ሐሰትም እውነት ይመስላል ቢባልም ነገር ግን በውስጣችን ሆኖ የምትከራከረን ሕሊና ወይም ነፍስ ግን እውነትና ሐሰት ምን እንደሆነ ለይታ ታረጋግጥልናለች።

በዚህ ምክንያት ነው ሕሊናቸው አላርፍ ብላ እውነት ፍለጋ መጽሔት አሜናቸው /ካሜራቸው/ አንጣጥረው ብዙ ገንዘብ አውጥተው ሀገር አቋራጭ ከቢ.ቢ.ሲ. (B.B.C) ስኮትላንድ ተነስተው የወጣቶች

ፕሮግራም /ዝግጅት/ በሚል ርዕስ በቢል ሉኬ መሪነት ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ስለ ሠብአ ሠገሎች ምንነትና ማንነት ትክክለኛውና እውነቱን ለማወቅ ለጠየቁኝ፤ በአጭሩ ሆኖ በቂ የሆነ መልስ ሰጥቻቸዋለሁ።

ቢሆንም እኔም ሕያው እግዚአብሔር የብርሃን አምላክ መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ እውነቱን እንዲገልጽልኝ በመጠየቅና በጥንት ዘመን ከእነሥዕሉና ሐረጉ ጭምር በብራና የተጻፉትን መጻሕፍት ማስረጃነት ስለ ጥበበኞቹ ሰዎች ማንነትና ስማቸው የትውልድ ሐረጋቸውና የተወለዱበትን ሥፍራ ሳይቀር በዚህ ጥናት ውስጥ ሰውን በማያደክም መልኩ በአጭሩ የገለጽኩት ስለሆነ በጽሞና እንዲያነቡት በትህትና አሳስባለሁ።

አባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ

፭ሺ፱፻፺፭ /1995/ - ፭ሺ፱፻፺፮ /1996/





# ክፍል አንድ

## 1-ሀ የትርጉም ዘይ

ይህ ጥናት ለመጀመሪያ ጊዜ የተዘጋጀው ከላይ በተጠቀሰው ርእስ መሠረት፤ በእንግሊዝኛ ቋንቋ በቃል እየተነገረ ነበር በቪዲዮ የተቀረጸው።

ስለዚህ አሁንም ይህ በኢትዮጵያዊኛ ቋንቋ በጽሑፍ የተዘጋጀው ጥናት ወደ ተለያዩ የላዕድ ቋንቋዎች ለትርጉም ዘይ እንደሚያመች ሆኖ መጻፉን ለተርጓሚዎች አሳስባለሁ።

ይህም የሚሆነው ደግሞ ጸሐፊዎቹ ወይም ደራሲያኑ በተለያዩ ቋንቋዎች የሰለጠኑና የሚያውቁ ከሆነ ብቻ ነው፤ አለበለዚያ ግን ለመተርጎም የሚያስቸግር ከመሆኑም በላይ፤ ቢተረጎምም መሠረተ ሀሳቡ የተፋለሰ ይሆንና ለመግባባት ያስቸግራል።

እስከ ዛሬ ድረስ በዓለም ውስጥ በጽሑፍ የቀረቡ የመንግሥታት ውሎችና የሃይማኖቶች

ዶግማዎች እንዲሁም የድርጅቶች ስምምነቶችና ልዩ ልዩ የሆኑ የምሥጢር ውሎችና ደብዳቤዎች ለትርጉም እንዲያመቹ ሆነው በአዋቂዎች ባለመቀረጻቸው የትርጉም ልዩነት ፈጥረው፣ መንግሥታትንና ሕዝቦችን በማሩጀት ላይ እንደሆኑ አይካድም።

ለምሳሌ ያህል የውጫሌ ውል በኢትዮጵያና በኢጣሊያ እንዲሁም ደግሞ የማይጨው ውል መጥቀሱ በቂ የሆነ ማስረጃ ነው እላለሁ። የተለያየ ትርጉም ሰጥቶ ጦርነት ማስነሣቱን አይካድም።

## 2-ለ. <u>አጭር ታሪክ ስለ አይሹር ፩ኛ/1/፤</u>

<u>ስለ ክርስቶስ መወለድ የሚጠቁመውን ኮከብ ለመጀመሪያ ጊዜ ያየው ንጉሥ ኢትዮጵያዊ ነው</u> ይባላል? ተብሎ በቃል ለተጠየኩት መልሱ አይሹር ፩ኛ/1/ ነው የሚል ሲሆን፣ ዘለዓለማዊ የሆነ ፈጥሮ የሚገዛ፣ መፍጠሩና መግዛቱ የባሕሪዩ የሆነ፣ ሕያው እግዚአብሔር የሰውን ሥጋ የመወሐዱን ምሥጢር





ከነቢያቶቹ ሁሉ በፊት አስቀድሞ የገለጸለት፣ መናገሻ ከተማው በኦሊስ ሆኖ፣ የኢትዮጵያና የመካከለኛው ምሥራቅ በሙሉ ንጉሠ ነገሥት ለነበረው ለኢትዮጵያዊው <u>አይሹር አንደኛ</u> ነበር። በመጻሕፍተ ሰሎሞን ወሲራክ በአንድምታው ላይ በታሪኩ ክፍል ፲፱፻፲፮ (1916) ዓ.ም. ተመልከት፣

ይኸውም ሕያው አምላክ ፍጹም <u>ሰው</u>፣ ፍጹም <u>አምላክ</u>፣ ሆኖ ከቅድስት ድንግል የሚወለድ መሆኑን በኢትዮጵያዊው ንጉሠ ነገሥት አይሹር ፩ኛ/1/ አድሮ ያናገረውን ትንቢት ሙሉ ቃል ከእነማስረጃው እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

ስለዚህ ንጉሠ ነገሥት አይሹር ፩ኛ/1/ ለተከታዮቹና ለመኳንንቶቹ በጽሑፍ ያስተላለፈው ትንቢት የሚለው ከጥዋቱ ፀሐይ እንደወጣች ልክ ፫ት/3/ ጫማ በዘመናችን አንጋገር ከጥዋቱ ፫ት/3/ ሰዓት እንደሆነ ማለት ነው።

ቢሆንም ጂራቱ ፲፫ት/13/ ክንድ የሚያህል ፯ት/7/ ጎበረ ቀለማት ያለው በጣም ቆሚያምር

ኗሪታም የሆነ ከከብ ከምሥራቅ በኩል ሲወጣ ከታየና ከሕያው አምላክ ለማየት የተፈቀደላቸው ሰዎች ብቻ ሲያዩት፣ የዓለም ብርሃንና መድኃኒት የሆነ ከድንግል የመወለዱ ምልክት ነውና ወዲያውኑ በፍጥነት ሳይጠራጠሩ፣ ወርቅ፣ ከወርቅ የተሠራ ሙካሽ ጥላ፣ የቀጭኔ ወይም የፈረስ ጭራ፣ የዝባድ ሽቱና የወይራ ቅባት፣ ይውሰዱለት፣

እንዲሁም ንዑሀ የሆነ ዕጣንና ከርቤ፣ ገጸ በረከት ወይም እጅ መንሻ፣ ይዘው ከብዙ ሠራዊት ጋር ይከተሉት፣ እየመራ ከቦታው ያደርሳቸዋል፣ የሚል ነበር፣ የአይሹር አነጋገርና ትንቢት፣ ስለ ስጦታው ማቴ.ም.፪ ቁ.፲፩-፲፪(2.11-12) መዝ.፸፩-፸-፲፪ (71.8-12) ተመልከት።

ትንቢቱ የተነገረውና የተጻፈው ደግሞ ፪ሺ፲፪ /በ2012/ ከ.ፊ /B.C/ መሆኑንም መጽሐፈ ምሥጢር ዘአዶናይ ራፋኤል በሚገባ የሚያስረዳ ሲሆን፣ መጽሐፉ የጥበባትና የምሥጢራት ሁሉ ምንጭ እንደሆነ አይካድም።

በኋላም ስለ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ ቅዱስ ዳዊት፣ ኢሳይያስ፣ ስምዖንም የሕፃኑን መወለድ ሳታይ አትሞትም ተብሎ ትንቢት የተነገረለት ነው።





እንዲሁም ደግሞ ጠንቋዩና አስማተኛው በልዓምም አህያ ያናገረችው ሲሆን፣ እርሱም ከያዕቆብ ቤት ኮከብ ይወጣል ብሏል፣ ዘኁ.ም.፳፬/ ቁ.፲፯-፲፰/24 ቁ.17-18/፣ መዝ.ም.፻፵፩፣ ቁ.፲፩-፲፭/ 131፣11-15/፣ ኢሳ.ም.፯፣ ቁ.፲፫-፲፭ /7ቁ.13-15/፣ ሚል.ም.፭፣ ቁ.፮-፬/5ቁ.2-4/፣ ማቴ.ም.፪፣ቁ.፪-፲፪/2 ቁ.2-12/፣ ዮሐ.ም.፯፣ ቁ.፵፪-፫/7ቁ.42-3/፣ ሉቃ.ም.፩፣ቁ. ፳፭-፴፯/1ቁ.28-36/፣ ማቴ.ም.፩፣ቁ.፳፩-፳፭ /1ቁ.21-25/ ሉቃ.ም.፲፬፣ቁ.፭-፴/14.5-30/ ይመልከቱ።

**➡ ይሁን እንጂ ከዚህ ላይ ደግሞ የኢትዮጵያውያንን ሥርወ መንግሥት አመጣጥና የሥልጣን ውረድ ተዋረድ እንዴት እንደ ነበረ አንካሩን ብቻ ለማስታወስ ያህል በአጭሩ እገልጻለሁ፣**

በ ፭፱፻፶ (5950) ከ.ፊ. (B.C.) ኢዮጵያ የሚባል የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ንጉሥ የነገሠበት ዘመን ሲሆን፣ እምነቱም ከጎይሎች ሁሉ በላይ የፍጥረታት ሁሉ ምንጭና መገኛ በሆነ ለዘለዓለም በማያበራ ፀሐይ ነው።

1.፩. ይኸውም ንጉሠ ነገሥት የሚባለው በሥሩ ፭ት(5) ንጉሦች ሲኖሩት ሲሆን፤

2.፪. ንጉሥ የሚባለው ደግሞ በሥሩ ፭ት (5) ልዑሎች ሲኖሩት ነው፤

3.፫. ልዑል የሚባለውም በሥሩ ፭ት(5) ራስ ልዑሎች ሲኖሩት ሲሆን፤

4.፬. ልዑልራስ የሚባለው ደግሞ፣ በሥሩ ፭ት(5) ራሦች ሲኖሩት ነው፤

5.፭. ራስ የሚባለው ደግሞ በሥሩ ፭ት(5) ደጃዝማቾች ሲኖሩት ሲሆን፤

6.፮. ደጃዝማች የሚባለውም በሥሩ ፭ት(5) ፊታውራሪዎች ሲኖሩት እንደሆነ ባይካድም፤

7.፯. ፊታውራሪ የሚባለውም በሥሩ ፭ት(5) ቀኛዝማችና ግራዝማች ሲኖሩት ነው፤

8.፰. ግራዝማችና ቀኛዝማች የሚባለውም በሥሩ ፭/5/ ብላታዎች ሲኖሩት ሲሆን፤

9.፱. ብላታዎች የሚባሉት ደግሞ በስሩ ፭ት(5) ባራምባራሶች ሲኖሩት ነው።





የሌላውም የሥልጣን ሐረግና ሰንሰለት ውረድ ተዋረድ እንደዚሁ የሚቀጥል መሆኑን የታወቀ ነው።

## 3.ሐ. ጥበበኞቹ ነገሥታት ማለት?

፩/1/ ጥበበኛ

፪/2/ አዋቂ

፫/3/ ብልህ

፬/4/ ተንኮለኛ

፭/5/ አሳሳች

፮/6/ አስተማሪ

ጥበበኛ ከከብ ቆጣሪ፤ ምሥጢር አዋቂ፤ አሠራሩ የማይታወቅ አስተዋይ፤ የተደበቀው ምሥጢርና ነገር አውጪ፤ ጠንቋይ፤ የሰውን ልብ መርማሪ፤ ሸረኛና መሰሪይ፤ ብዙ ማለት የሚቻል ቢሆንም በተለይ ደግሞ የዚህ ዓለም ነገሥታቶችና መሪዎች ለአገዛዛቸው ሲሉ በብዙ መልኩ ሁሉ ጥበበኞችና ክፉዎች ዋሾዎች፤ እንደ ዕስስት ተለዋዋጮች እንደሆኑ የማይካድ እውነት ነው።

ይሁን እንጂ በመሠረቱ የጥበብ ምሥጢሩ ለማንም ያልተሰጠ ትርጉሙ የማይታወቅ ሰማያዊ ሲሆን፤ በፍጡራን ዘንድ በሰው ልጆች አእምሮ በፍጹም የማይመረመር፤ የማይከሰት ድብቅ የሆነ ምሥጢር ቢሆንም፤ በሰው ልብ አድሮ ጥበባትን ይሰጣል።

ነገር ግን ለጊዜው ጥበብ ማለት ሆኖዕና መድኃኒት ራሱ ባለቤቱ ዘለዓለማዊ የሆነ የብርሃን አምላክ መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ሕያው እግዚአብሔር መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዱናል።

ይኸውም ቅዱሳን የሆኑ ከዘለዓለማዊው የብርሃን አምላክ አብረው የነበሩና ቃል በቃል የተነጋገሩና የተማሩ፤ አብረው የበሉና የጠጡ ሐዋርያት፤ እንዲሁም የእነርሱ ደቀ መዝሙር የነበረ፤

በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆነና የቆጵሮስ የመጀመሪያ ኤጲስቆጶስ የነበረ ቅዱስ ኤጲፋንዮስና ደግሞም የአሌክሳንዲሪያው ፓትርያርክ የነበረው ኢትዮጵያዊ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ ከመጽሐፍ ቅዱስ





አውጣጥተው ስለ ጥበብ የጸፉልንን ቃንቋው ለዘመኑ ሰው እንዲገባ በሚገባ በማሻሻል፤ ከዚህ ቀጥሎ አቅርቤዋለሁና በፍቅር እንዲያነቡት እጠይቃለሁ።

## 4.መ. <u>አይቴ ብሔራ ለጥበብ</u>፤

የጥበብ አገሯ ወዴት ነው፤ ማደርያዋስ የትነበር፤ ቦታዋንስ ማን ያውቃል፤ የነዳናዋስ ፍለጋ በወዴት ይገኛል፤ ባሕሩን ተሻግሮ ከኢትዮጵያ ድንበር የሚገኝ በወርቀ አፈር /የዝማም/ ቀይ ወርቅ የገዛት ማን ነው፤

ከደመናስ በላይ ወጥቶ ያያት ማን ነው፤ ሟች የሆነ ፍጡር ጉዳናዋን አያውቃትም፤ በሰው ልጅ አእምሮ ውስጥም አትታወቅም፤

ከሰው ሁሉ ዘንድም ተረሳች፤ በሰማይ በራሪ የሆኑ ረቂቃን /መላእክት/ እንዲሁም ከሌሎች ፍጥረታትም ሁሉ ተሠወረች፤ ነገር ግን እርሷን ያገኙ ከእግዚአብሔር ጋር ተወዳጁ፤ እርሷን የሚጠሉ ደግሞ ዳግም ሞትን ይሞታሉ።

ጥበብ ከፀሐይ ውበት ይልቅ እርሷ ታምራለች፤ የሰማይ ከዋክብትና ብርሃናትም እርሷን አይመሳሰሏትም፤ የፍጥረታት ሁሉ ምንጭና መጀመሪያ ስትሆን በፈቃዷ ፍጡር ከሆኑ ብርሃናት ጋር ስትነጻጸር ትገኛለች፤

ቀዳማዊት እንደመሆኗ መጠን ፍጥረታትን ሁሉ ታድሳለች በየትውልዱም በጻድቃን ሰውነት ስትመላለስ ትኖራለች። ከከበረ ዕንቁ ሁሉ እርሷ ትበልጣለች፤ ክብር የተባለው ሁሉ ለእርሷ መጠኗ አይደለም አይመሳሰላትም።

ምክርና የአእምሮ ጽናት ለደጋጉቹ ሰዎች ትሰጣለች፤ ነገሥታቱ በእርሷ ፈቃድ ይነግሣሉ፤ ኃያላኑም በእርሷ ኃይልን ያገኛሉ፤

አዋቂዎቹም በእርሷ ጥበብን ተምልተው እውነትን ይጽፋሉ፤ ደጋጎቹ በእርሷ ይከብራሉ፤ መኳንንቱም በእርሷ የምድርን ፍሬ ይበላሉ፤ በምድር የሚኖር ሕዝብንም ይገዛሉ፤





አራሾችም በእርሷ ፈቃድ የመሬትን ፍሬና በረከት ሁሉ ያገኛሉ፤ የሚወዷትን ትወዳለች ሕጓን የሚጠብቁትንም ሁሉ ትጠብቃለች፤ በእውነት መንገድም ዘወትር ትገኛለች፤ በእውነት በንፁህ ልብ ሆነው ከፈለጓትም በፍጥነት መልስን ትሰጣለች፤ በእውነት ለሚያውቋት ሰዎች ሀብትንና እድሜን ትሰጣቸዋለች መዝገባቸውንም ትባርካለች።

ሁሉን የሚያውቅና የሚረዳ ንፁህ የሆነ ሰው በእውነት ያውቃታል፤ ሁሉን የሚያስተውል እውነተኛ ሰው እርሱ መንገዷ የቀና ብርሃን መሆኑን ይረዳል፤

ጥበብ የተባለ የነበረና ያለ የሚኖር ሰማያዊና ምድራዊ የሆነ ኃይል ለባለሟሉ ለያዕቆብና ለቅዱሱ ለኧኤል /ለእሥራኤል/ ሰው የመሆኑን ሚስጢር ገለጠላቸው።

ከዚህም በኋላ ዓማኑኤል ያለአባት ከድንግል ተወልዶ፤ በምድር ላይ ታየ እንደሰውም ተመላለሰ፤

ጥበብ በሴትም በወንድም ዖታ እንደምትጠራ እየተረዳን ነው፤ በጥናቱ መሠረት፤

እነሆ ጥበብ ቤትን ሠራች፤ ሰባት አእማድን ወይም ምሰሶዎችን አቆመች። ከዚያም በኋላ የራሷን ሥጋ በመስቀል ላይ አረደች፤ የራሷንም ደም ለመድኃኒት በመስቀል ላይ አፈሰሰች፤ በማድጋዋም የራሷን ደም ወደ ወይን ለውጣ አቀረበች ማዕዷንም አዘጋጀች፤ ባሮቿንና አገልጋዮቿን ሰፋ ላለ ጊዜ እንዲያስተምሩ ላከች።

ሰነፎች የሆኑና ዕውቀትም ያነሳቸው ሰዎች ወደኔ ይምጡ እያለች ተናገረች፤ የእኔን ጎብስት ብሉ፤ ሥጋየ ነው፤ የኔን ወይን ጠጡ ደሜ ነው፤ በማለት አወጀች። በእውነት የእኔን ሥጋ ይበሉና ደሜን ይጠጡ ዘንድ ስንፍናን ትተው በንስሐ ይኑሩ እያለች አስጠነቀቀች።

ከላይ አስቀድሜ የገለጽኩት ቢሆንም፤ ሐዋርያትና ኤጲፋንዮስ ዲዮስቆሮስ ሊሉት የፈለጉትን ምሥጢር ከዚህ በታች ይገልጹታል፤





ይኸውም ጥበብ ያልነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ በሥጋው መሥዋዕትነት ያዳነን በደሙ ፈሳሽነት የፈወሰን በማለት ገልጸውታል።

ክቡራን አንባቢያን አይቴ ብሔራ ለጥበብ የሚለው ንዑስ ርዕስ ስታነቡ ለሰው በሚገባ ቋንቋ ለመግለጽና ለመተርጉም እንደተቸገርኩ ይገባችኋል ብዬ አምናለሁ፤

ምክንያቱም የተጻፈበት ዘመን በጣም ሩቅ ስለሆነ ግዕዙም ኢትዮጵያዊኛውም ማለትም አማርኛው በፍጹም የማይቀራረቡ የተቃረኑ ስለሆኑብኝ ነው የተቸገርኩት።

አሁንም መጽሐፉን ለማመሳከር ለምትፈልጉ ወገኖች ሁሉ እኔ አርሜ ለተረጉምኩት ስሀተት መስሎ ከታያችሁ ይቅርታ እጠይቃለሁ።

አባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ

፲፱፻፺፭ - ፲፱፻፺፮ /1995-1996/

# ክፍል ሁለት፤

## 1/፩/ መልስ ስለ ጥያቄ ቁጥር አንድ፤

ኢየሱስ ክርስቶስን እስከ ቤተልሔም ማለትም ቤተ ነብስት ድረስ ሄደው የጐበኙት ሰብአ ሰገሎች ይባላሉ፤ ጥበበኞችና ብልሐተኞች ማለት ሲሆን፤ እነዚህም ሦስት ታላላቅ ነገሥታትና ሁለት ልዑሎች ሲሆኑ፤ በድምሩ አምስት ናቸው። ሁሉም በዘር ሐረጋቸውና ትውልዳቸው ኢትዮጵያውያን እንደሆኑ አይካድም።

ቢሆንም እስከ ዛሬ ድረስ ሦስቱ ጥበበኞች ወይም ጠንቋዮች ተብለው በደፈናው ከሚጠሩ በስተቀር ወይም የምሥራቅ ሰዎች ናቸው ከማለት ሌላ ሀገራቸውንና ስማቸውን በትክክል የሚጠቅስ ማስረጃ አልተገኘም ነበር።

አብዛኞቹ ሀገሮች ደግሞ በሥዕል ሲገልጿቸው አንዱ ጠይም ወይም ጥቁር ኢትዮጵያዊ ነው ሲሉ፤ ሁለቱ ቀያዮቹ ደግሞ የዓረብ ሰዎች ይሏቸዋል።





በዚያን ዘመን አብዛኞቹ የዓረብ መሪዎችና ሕዝቦች ኢትዮጵያውያን እንዲነበሩ ባይታበልም፤ ስለዚህ ሰዎች ባያስተውሉት ነው እንጂ ኢትዮጵያውያን እኮ ፬/4/ ዓይነት አበባ ቀለም ናቸው፤

ይኸውም ሙሉ ጥቁር፤ ጠይም፤ ቀይ ዳማ፤ ሙሉ ቀይ፤ ኤርምያስ ም.፲፫ ቁ.፳፫-፬ /13.23-4/ በዚህ መሠረት አሁን ሁሉም ኢትዮጵያውያን ለመሆናቸው መጽሐፈ ትውልድ ዘአቡነ አዳምና መጽሐፈ ምሥጢር ዘአዶናይ ራፋኤል ያስረዱናል። /የብራና/

1.፩. ከላይ የተጻፈውን ዓረፍተ ነገር በይበልጥ ግልጽ ለማድረግ፤ እነርሱ ባያውቁት ነው እንጂ ኢትዮጵያውያን እኮ በትንቢቱ መሠረት አራት ዓይነት አበባ /ሞዛይክ/ ቀለም ሲሆኑ፤

እነዚህም ከሌላ ሕዝብ የተዳቀሉ ሣይሆኑ የአንድ አባትና የአንዲት እናት ብቻ እንደሆኑ

አይካድም፤ ስለዚህ ሰብአ ሰገሎች በሙሉ ኢትዮጵያውያን ናቸው፤

ማለትም ነቢዩ በተናገረው ትክክለኛው ቃል መሠረት፤ ኢትዮጵያዊ አበባ መልኩን ነብር ዝንጉርጉርነቱን እስከ ዓለም ፍጻሜ ይለውጥ ዘንድ ይችላልን? ነበር የሚለው የመጀመርያው መጽሐፍ ቅዱስ፤ ሰይጣን ያደረባቸው ሰዎች የበከሉት መጽሐፍ ደግሞ ኢትዮጵያዊ መልኩን ነብር ዝንጉርጉርነቱን ይላል፤ ቢሆንም ፬/4/ ዓይነት ቀለም መሆኑን የሚያስረዳ ነው። ይኸውም፤

1.፩. ሙሉ ጥቁር፤

2.፪. የጥቁር ጠይም፤

3.፫. የቀይ ዳማ፤

4.፬. ሙሉ ቀይ፤ ናቸው፤

ኤር.ም.፲፫ቁ.፳፫-፬ /13.23-4/ ይመልከቱ።

2.፪. እንዲሁም ደግሞ ኢትዮጵያውያን እንደ ቀለማቸው አሁንም ከዓለም ሕዝብ ተለይተው የተፈጠሩት ከእነምግባቸው ነው፤ ይኸውም ጤፍን





በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መዝሙረ ዳዊትና በጥንት የሰብአ /ሳባ/ ቋንቋ የሚጠራው ዘንዶ ወይም እባብ በማለት ሲሆን፤

ትክክለኛ የሆነ ትርጉሙ ደግሞ ጥቁርና ቀይ ጤፍ እንደሆነ አይታበልም፤ ስለዚህ ጤፍ ለኢትዮጵያውያን በመለኮት ተባርኮ የተሰጣቸው ምግባቸው ነው። መዝ.፸፫/፸፬/ ቁ.፲፫-፲፭(73.74.13-15) ቢሆንም ከጤፍ ሌላ እንደተባለው ዘንዶና እባብ ቢባል ደግሞ ኢትዮጵያውያን በአሪቱ ሕግ መሠረት ርኩስ የሆነ ነገር ፈጽሞ እንደማይበሉ የታወቀና የተረጋገጠ ነው።

3.፫. አሁንም እንደገና በትውልድ ዘሩ ኢትዮጵያዊ የሆነ ዕዝራ ሱቱኤልም ስለ ጤፍ ምርጥ ምግብ መሆኑን ሲያስረዳ ግዮንና ኤፍራጥስ፤ ጤግሮስና ኤፌሶን፤ የሚፈልቁባት ሀገር የበቀለና በኤደን ገነት የግዮን ወንዝ ዙሪያዋን በመክበብ የሚያጠጣት (በተራራ መካከል) ለሚኖሩ ሕዝቦች የተሰጠ ጤፍ የቅዱሳን ምግብ ነው በማለት

ገልየታል፤ ዕዝ.ሱቱ.ም.፬ ቁ.፶፩-፫ (4.51-3) የብራናውን ተመልከት የታተመው ቁንጽል ነው።

4.፬. <u>ታላቁና</u> በትውልድ የዘር ሐረጉ ኢትዮጵያዊ የሆነ ነቢዩ ሕዝቅኤል ደግሞ ስለ ጤፍ ምግብነትና በጣም ጠቃሚ የሆነ መድኃኒት መሆኑን ሲያብራራ፤

አንተም <u>ጤፍንና አጃን፤ ስንዴንና ገብስን፤</u> ምሥርንና ባቄላን፤ በእንጎቻ ጋግረህ በተኛህበት ጉንህ ፮፻፷፮ (666) ቀን ብላ ትታደሳለህ ከተለያየ በሽታም ትፈወሳለህ ይላል፤ የጥንቱ የብራናው መጽሐፍ ቅዱስ ለየት ባለ አገላለጽ፤ የታተመው የተፋለሰ ነው። <u>ሕዝ.ም.፬ቁ.፱-፲</u>(4.9-10) ተመልከት።

5.፭. <u>የዘንዶና</u> አባብ ምግብነት ዛሬ በዓለም ውስጥ ተወዳጅ ሲሆን፤ ነገር ግን አሁንም በድጋሚ ኢትዮጵያውያን በአሪቱ ሕግ መሠረት ርኩስ የሆነ ያልተቀደሰ እንስሳ ፈጽመው አይበሉም፤ ዘሌዋ.ም.፲፩ ቁ.፩-፵፯ (11.1-47) ዘዳግ.ም.፲፬ ቁ.፫-፳፪ (14.3-22) ይመልከቱ።





## 1-ሀ. <u>የነገሥታቱ ስምና የትውልድ ቦታ፤</u>

፩ኛ/1/ ናሁ አዳም ከኢትዮጵያ፤

፪ኛ/2/ ራይናስ ከምሥር /ግብጽ/

፫ኛ/3/ አሕራም ከየመን ናቸው።

ስለዚህ በትንቢቱ መሠረት አይሹር ፩ኛ/1/ እንደተናገረው ሁሉ ኮከቡን በመጀመሪያ ጊዜ በምሥራቅ በኩል ሲወጣ ለማየት የታደሉት ከዚህ በላይ ስማቸው ከእነ አገራቸው ጭምር የተጠቀሱት ፫ት/3/ ነገሥታት ብቻ ሲሆኑ፤ ኮከቡን ያዩት ደግሞ እንደ አጋጣሚ ሆኖ ሦስቱም ነገሥታት በነገሡ በ፲፫ኛው/13/ ቀን መሆኑን መጽሐፈ ትውልድ ዘአቡነ አዳም ይናገራል፤

ይሁን እንጂ <u>የጉዞው መሪ የኢትዮጵያና</u> የመካከለኛው ምሥራቅ ንጉሠ ነገሥት የነበረው ናሁ አዳም ከወንድሙ ጋር ሲሆን፤ መዝ.፻፴፪ /132/ ተመልከቱ።

በመጽሐፈ ሚስጢረ ካህናት ዘአዶናይ ራፋኤል እንደ ተመዘገበው፤ ተከታዮቹ ደግሞ

የላዕላይና የታህታይ ምሥር /ግብጽ/ ንጉሥ የነበረው ራይናስ ከወንድሙ ጋርና፣ የየመኑ ንጉሥ አሕራም ናቸው፣ መዝ.፸፩.ቁ.፱-፲፪/71.9-12/ ይመልከቱ፣

የጥሏቸው ታሪክ በግመል፣ በፈረስና በቅሎ፣ በአህያ፣ ሲሆን፣ ብዙ የሆነ ሠራዊት እንዳስከተሉም አይካድም፣ የሄዱትም ሲዊዝ ካናል ከመከፈቱ በፊት መንገድ ነበረ በዚያ ነው የተሻገሩት፣ ቢሆንም ከቦታው ለመድረስ የወሰደባቸው ጊዜ <u>ከአንድ</u> ዓመት እስከ <u>ሁለት</u> ዓመት ነው። ማቴ.፪ ቁ.፩-፲፮ (2.1-18) ይመልከቱ፣

## 2-ለ. <u>ኖስተርዳሞስና የኢትዮጵያ</u>

<u>፩ሺ፱፻፺፬ /1994 ዓ.ም./</u>

ይሁን እንጂ በ፩ሺ፱፻፸፬ /1974 ዓ.ም./ እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር በአቴንስ ዩኒቨርሲቲ በነበርኩበት ጊዜ የዓለም የቀንና የዘመን አቆጣጠር ጥናት በሚል ርዕስ በተደረገው ውይይት ላይ ተሣትፌ ነበር።





የዘመናት አቆጣጠር እንዴት በእየሀገሩ ሁሉ የተለያየ ሆነ፣ በተለይ ደግሞ በክርስቲያኖች ዘንድ፣ ከሆነ የየትኛው አገር አቆጣጠር ነው በትክክል የሆነ፣ በማለት ከተለያዩ ሀገሮች ለመጡ ተማሪዎች ይጠይቁ ነበር።

ስለዚህ እኔም ስለ ሀገሬ የዘመን አቆጣጠር ተጠይቄ በአጭሩ የሰጠሁትን መልስ አስታውሳለሁ፣ ይኸውም አስቀድሜ ከላይ እንደጠቀስኩት ሁሉ፣ አምላካችን ከድንግል የመወለዱን ሁኔታ ከነቢያቶቹ ሁሉ በፊት የተገለጸውና ምልክቱም ጭምር የተነገረው ለኢትዮጵያውያን ነገሥታት መሆኑ እውነት ነው፣ በማለት ነበር ያስረዳሁት፣ በዚህም መሠረትነት ሰብአ ሰገሎች በኮከብ እየተመሩ መጥተው በድንገት በመግባት የኢየሩሳሌምን ከተማ አስጨነቋት፣ ንጉሥ ሄሮድስና መኳንንቱም ተሸበሩ፣

ጥበበኞቹም ነገሥታት በትንቢቱ መሠረት በኮከቡ እየተመራን ነው የመጣነውና የአይሁዶች

ንጉሥ የተወለደው በየትኛው የይሁዳ አውራጃ ነው ብለው ጠየቁት፤

ሄሮድስም ወዲያውኑ ካህናቱንና ጠንቋዮቹን ጠይቆ ነገሩ እውነት መሆኑን ስለተረዳ እናንተም እንደምታውቁት ሁሉ በቤተልሔም አውራጃ ነው፤

ነገር ግን ጌቶቼ እናንተ እጅ ነስታችሁ ስትመለሱ፤ እኔም በተራዬን ሄጄ እሰግድለታለሁ ብሎ ነበር የሸኛቸው። ማቴ.ም.፪. ቁ.፪ ፩-፲፪(2.1-12)

ይህም የሆነበት ዘመኑ ከ፲፮-፲፬/16-14/ አመተ ዓለም ወይም ከ.ፊ /B.C/ ነበር፤ ስጦታቸውን ለሕፃኑ ከእናቱ ጋር እንዳበረከቱ ወዲያውኑ አመተ ዓለም መሆኑ ቀርቶ ፩ድ/1/ ዓመተ ምሕረት መስከረም ፩(1) ወር ፩ኛ (1) ቀን ተባለ፤

ስለዚህ የአምላካችንና የመድኃኒታችን መወለድ በኢትዮጵያውያን አቆጣጠር መሆኑን የማይካድ እውነት ነው፤ በማለት ነበር ለጠየቁኝ የሰጠሁት መልስ።





በእውነትም ከዓለም የቀን አቆጣጠር ውስጥ ትክክለኛው የኢትዮጵያ መሆኑን የሚያስረዳ ሁለተኛ ማስረጃ ደግሞ፤ በፈረንሣይ ሀገር የነበረው ባለ ራዕዩና ትንቢተኛው የኖራንሲስካን መነኩሴ፤ የነበረው ኖስተርዳሞስ ከዛሬ ፭፻፷ /560/ ዓመት በፊት አስቀድሞ ስለ ኢዮርክ ሁለት መንትያ የሆኑ ፎቆች መፍረስና እንዳልነበሩ ይሆናሉ ብሎ ትንቢት የተናገረው በ፩፹፩፻፺፬ /1994 ዓ.ም./ በ፩ኛ/1/ ወር በ፩ድ/1/ ቀን ይፈጸማል ነበር ያለው ሆነ /ተፈጸመ/፤ የሚያስደንቅ ነው።

ቢሆንም ኖስተርዳሞስ በ፩፹፩፻፺፬/1994 ዓ.ም./ ይሆናል አለ እንጂ በእገሌ ሀገር አቆጣጠር አላለም፤ ነገር ግን ፩፹፩፻፺፬ /1994 ዓ.ም./ መስከረም ፩ድ/1/ ቀን ፩ኛ/1/ ወር የኢትዮጵያውያን አቆጣጠር ብቻ ነው ይህም እውነታ በሁሉም ዘንድ የታወቀና በትንቢት የተረጋገጠ ስለሆነ ለመታሰቢያነት በዚህ ታሪካዊ የሆነ ጥናት ውስጥ መዝግቤዋለሁ።

## ሐ. ስለ ሰብአ ሠገል መግለጫ፤

የሰብአ ሠገሎች ቁጥር ፫ት/3/ ነገሥታትና ፪ት/2/ ልዑሎች በድምሩ ፭ት/5/ መሆኑን ከላይ በተደጋጋሚ ተገልጿል፤ ቢሆንም ሰማያዊ የሆነ አምላክ በትንቢቱ መሠረት ምድራዊ ሰው ሆኖ ከቅድስት ድንግል ማርያም በተዋሕዶ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ሆኖ በቤተ ጎብስት /ቤተልሔም/ በከብቶች በረት ተወልዶ እንደተገኘ የማይካድ እውነት ነው፤ መላእክትና እረኞች መስክረዋል። ሉቃ.ም.፪.ቁ.፰-፳፩ (2.8-21)

ስለዚህ ሰማያዊና ምድራዊ ዙፋን ወይም መንበር ወደ ተዋሐዳቢት የቤተ ጎብስት /ቤተልሔም/ ቤተ መቅደስ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ለመግባት የታደሉት ከሕያው አምላክ እንዲገቡ ተፈቅዶላቸው ከስጦታ ጋር የገቡት ከፍ ብሎ በእየማዕረጋቸው የተጠቀሱት ፭ቱ/5/ ሰብአ ሠገሎች ብቻ እንደሆኑ አይታበልም።





ይሁን እንጂ የእናት ኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ይህን ታሪካዊና እውነተኛ የሆነ የሰብአ ሠገሎችን ምሳሌያዊ መርሐ ከእግዚአብሔር መሆኑን አምና በመቀበል፤

ከዚያን ጊዜ አንስቶ ማለትም ከመስከረም ፩ድ/1/ ቀን ፩ኛ/1/ ወር ፩ድ/1/ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ፤

1.፩ኛ. <u>በሦስቱ</u> ነገሥታት ምሳሌ <u>ሦስት</u> ቁሶች፤

2.፪ኛ. <u>በሁለቱ</u> ልዑሎች ምሳሌ ደግሞ <u>ሁለት</u> ዲያቆናት በድምሩ ፭ት/5/ ልዑካን ሲሆኑ እነዚህ <u>አምስቱ</u> ብቻ ቤተ መቅደስ ውስጥ ገብተው በመቀደስ መሥዋዕት እንዲያሳርጉ መስናለች፤ እስከ ዛሬ ድረስም እየተፈጸመና እየተሠራበት መሆኑን አይካድም።

የካህናቱ ቁጥር ከ፭ት/5/ ከጐደለ የቅዳሴው ሥነ ሥርዓት ይታጐላል እንጂ በፍጹም አይቀደስም፤ ነገር ግን ቀዳሲያኑ ማለትም የካህናቱ ቁጥር ከ፭ት/5/ በላይ ከሆነ ደግሞ <u>ሁለተኛው</u> አማናዊ

ምሳሌ እንደ ሽዕቱ/24/ ካህናተ ሰማይ ስለሆነ የቅዳሴው ሥነሥርዓት የሚፈጸም መሆኑን ለማያውቁት ሰዎች አስገነዘባለሁ።

አባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ ።

## ፪/2/. <u>መልስ ስለ ጥያቄ ሁለት፤</u>

የጉዟቸው ታሪክ በትንቢቱ መሠረት የዓለም መድኃኒት ሆኖ ለተወለደው ሕፃን ኢየሱስ ክርስቶስን ከቅድስት እናቱ ጋር እስከ ቤተ ጎብስት /ቤተልሔም/ ድረስ ሄደው መጉብኘት ሲሆን፤ ትንቢቱን ከእነምልክቱ ሳይቀር የተናገረው ደግሞ አይሹር ፩ኛ/1/ በ፪ሺ፲፪ /2012/ /ከ.ፊ/ /B.C/ መሆኑን በተደጋጋሚ ከላይ ተገልጿል።

ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው ሁሉ ትንቢቱ የተነገረው ረጅም ጊዜ ቢሆነውም፤ ነገር ግን ነገሥታቱ ዕድለኞች ሆነው በእነርሱ ዘመን በ፩ድ/1/ ዓ.ም. ሰማያዊው አምላክ፤ ምድራዊ ሰው ሆኖ በከብቶች በረት ተወልዶ በሕፃን መልክ አማኑ





ኤልን ማየትና እጅ መንሻ ማቅረብ ምን ያህል ዕድለኛነት ነው ያስደንቃል።

እንዲሁም ደግሞ ከመጀመሪያው ሲነሱ ጀምሮ እስከ ቤተ ጎብስት /ቤተልሔም/ ድረስ የሄዱት በትንቢቱ መሠረት በኮከቡ እየተመሩ ነው፤ ይህንንም ታሪካዊ የሆነ ጉዞ የኢትዮጵያ ሊቃውንት በእየገዳማቱና አድባራቱ እንዲሁም ደግሞ ታሪኩ ባለበት በወንጌሉ በጣም በሚያምር ሁኔታ ጅራታሙ ኮከብ ሳይቀር እንዴት እንደሚመራቸው በሥዕል አስለውት ይገኛል።

## ፫/3/. <u>መልስ ስለ ጥያቄ ቁጥር ሦስት</u>

ሦስቱ ጥበበኞች ወይም ሰብአ ሰገሎችና ጠንቋዮች ወርቅ ከርቤና ዕጣን፤ ጥላና ሞሪ፤ ቅባትና ሺቱ ስጦታ ይዘው ብዙ የሆነ ሠራዊት አስከትለው በትንቢቱ መሠረት ከድንግል በድንግልና ወደ ተወለደው ሕፃን ኢየሱስ ክርስቶስ ወይም መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል አስቀድሞ በሰየመው

ለዓማኑኤል የከበረ ስጦታና ገጸ በረከት እጅ መንሻ ለመስጠት ሲሆን፤

የስጦታዎቹ ምሳሌና ትርጉማቸው ደግሞ የሚያመለክቱት የዓለም መድኃኒት በመሆን ከቅድስት ድንግል ማርያም ለተወለደው ሕፃን ኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበላቸው ገጸ በረከቶች የሚተነብዩለት ከዚህ ቀጥሎ በሙሉ ሣይሆን በከፊል አቀርባለሁ።

፩/1/. ስለ ሕዝቡ በደልና ኃጢአት ስትል ግርፋትና መሰቀል አለብህ፤

፪/2/. ኃጢአተኛ ሣትሆን ስለ ሕዝብህ ስትል መራራ የሆነ ሐሞትና ሞት ይጠብቅሀል፤

፫/3/. ሕዝብህ ሞቶ እንዳይቀር ስትል ደግሞ ለማስነሣት ሚች ፈራሽ ደካማ የሆነ የሰውን ሥጋ ስለተወሐድህ በተናገርከው ቃል መሠረት ወደ አፈር ትመለሳለህ፤ መቃብርም አፏን ከፍታ ትጠብቅሀለች። ኢሳ፤ም.፶፫፤ቁ.፭-፲፪ /53.7-12/፤ የሐዋ.ሥ፤፳፭-፶ /8.26-40/፣





ዘፍ.፪፤፲፮-፲፰/2.16-18/፣ ዘፍ.፫፤፲፱-፳/3.19-20/ ይመልከቱ።

1-ሀ. የነገሥታቶች ንጉሥ ነህ ሲሉ፤ ወርቅ ዘውድ ጥላ በትረ መንግሥት እጅ መንሻ አቀረቡልህ።

2-ለ. የካህናቶች ካህን ሊቀ ካህናት ነህ ሲሉ፤ ዕጣን፤ቅባትና ጭራ፤ አክሊል ገጸ በረከት ሰጠህ።

3-ሐ. የአማልክቶች አምላክ ነህ ሲሉ፤ ደግሞም ስለ ሰው ልጆች ሁሉ መከራና ሥቃይ ለመጋራት ስትል በመስቀል ላይ መራራ የሆነ ሐሞትን መጠጣት አለብህ በማለት አጠጡህ፤ ከርቤ፤ በትረ መስቀል፤ ሽቶ አምሐ አቀረቡልህ፤ መዝ.፷፩፤፱-፲፪ /71፤9-12/፤ ኢሳ.ም.፷፤፮-፰/60.6-8/ መዝ.፷፩፤፲፮-፳ /21ቁ.16-20/፤ መዝ.፷፰፤፳፩-፳፬ /68ቁ.21-24/፤ ማቴ.፳፯፤፴፪-፶ /27፣32-50/፣ ማር.፲፭፤፮-፴፯ /15፣6-37/፤ ሉቃ.፳፫፤፲፰-፵፮ /23፣18-46/፤ ዮሐ.፲፱፤፭-፴፩ /19ቁ.5-31/ ይመልከቱ።

ነገሥታቱ በቤተልሔም ለተወለደው ሕፃን ለኢየሱስ ክርስቶስና ለቅድስት እናቱ ለድንግል ማርያም ስጦታቸውን ካበረከቱ በኋላ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ትእዛዝ በነፋስ ኃይል በብርሃን ሠረገላ በሰውር ዓለምን ዙረው ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ በኋላ በዙፋናቸው ላይ አልተቀመጡም፤

ወዲያውኑ የክብር ልብሶቻቸውን አውልቀው በማስቀመጥ ለብሰትውና ወደ በረሀና ወደ ጫካ ነበር የሄዱት፤ ዋልድባ /አርምሐ ደጋ/ ከአበው ጋር ተቀላቅለዋል፤ ምግባቸውም እንደ ማርና ወተት የምትጣፍጥ ለቅዱሳን የተፈቀደች ዕፀ ዋለ. ናት።

ሦስቱ ነገሥታትና ሁለት ልዑሎች በድምሩ አምስት ሰብአ ሰገሌች ይባላሉ፤ እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ በሕይወት ይኖራሉ እንጂ አይሞቱም፤

ምክንያቱም በትንቢቱ መሠረት ዕድለኞች ሆነው የሰውን ሥጋ የተዋሐደው የአምላክን ልደት በማክበራቸው ሲሆን፤ ዛሬ በሕፃን መልክ ያያችሁት ተመልሶ ለዳግም ትንሣኤ መጥቶ እስከምታዩት





ድረስ ሞትን አትሞቱም ብሎ ቅዱስ ገብርኤል ስለነገራቸው ነው።

ራሱ የነፍስ ፈጣሪ መድኃኔዓለም አ.የሱስ ክርስቶስም በቃሉ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ በምድር ላይ የማያሞቱ አሉ ባለው መሠረት ለምሳሌ, ያህል አ.ትዮጵያዊው ሄኖክና አይሁዳዊው ኤልያስ እንዲሁም አ.ትዮጵያዊው ዕገሪ ሱቱኤልና አ.ትዮጵያኑ ቅዱስ ያሬድና አባ ሕርያቆስ በሕይወት ይገኛሉ። ማቴ.ም. ፲፮፣ ፳፰ /16፣28/ ማር.ም.፱ ቁ.፩-፪ (9.1-2) ሌሌችም አሉ ብዙ ናቸው።

ሰብአ ሰገሌችን በክብር ተመስሉ ያመራቸው የነበረና አስቀድሞ የሕፃኑን መወለድ ያበሰረው ራሱ ቅዱስ ገብርኤል መሆኑን መጽሐፈ ሄኖክ ያልታተመው ትልቁ የብራናው መጽሐፍ ያስረዳል፤ የሄኖክ መጽሐፍ ፩ኛ (1) ብቻ ሣይሆን ፫ት(3) መሆናቸውን ዕጠቁማለሁ።

ስለ ሰብአ ሰገሌች እውነተኛ ታሪክ ከላይ ከፍ ብሎ በአጭሩ እየተብራራ እንደመጣው ሆኖ

ሳለ፤ ነገር ግን በአንዳንድ የውጭ ሀገሮች ደራሲያን ስለ ሦስቱ ጥበበኞች ስምና ሀገር በአንዳንድ መጽሐፍ ላይ ተገልጸ የሚገኝ ቢሆንም፤

ነገር ግን ግምታዊ ከሚሆን በስተቀር ማስረጃ ያልተጠቀሰለት ስህተት መሆኑን በዚህ አጋጣሚ አስገንዝባለሁ፤ ቢሆንም እያወቁ ከአንዱ በስተቀር በሙሉ ኢትዮጵያውያን ናቸው ብሎ ለመጻፍ ትንአትና ምቀኝነት እንደ ጠፈራቸው አይካድም።

## ፬/4/. <u>መልስ ስለ ጥያቄ አራት</u>፤

ከርቤ በኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ (ኦርቶዶክስ) ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጥቅሙ ብዙ መሆኑን የታወቀ ቢሆንም፤ ነገር ግን በጥያቄው መሠረት በኢትዮጵያ ተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን፤ የከርቤን ጥቅምና ምሳሌ በሚገባ አጠናቅቃ ታውቃለች።

የከርቤ ጥቅሙ በአመት ፩ድ/1/ ቀን ብቻ <u>የዓርብ</u> ስቅለት ልክ ፮ት/6/ ሰአት ሲሆን ለመስቀልክ





ማለትም ስለ ስቅለትህ የሚለው ስግደት ሲሰገድ በዕጣን ፈንታ በከርቤ ብቻ ለመታሰቢያነት ታጥኖለች፤ ከሀናቱም ጥቁርና ቀይ ነጭ የተቀላቀለበት ልብስ ተከህኖ ለብሰው ነው የሚያጥኑት፤ ይህም የሐዘን ምሳሌ እንደሆነ አይታበልም።

ስለዚህ ከላይ ከጥያቄ ሦስት ፤ ጀምሮ በትንቢቱ መሠረት ስለ ከርቤና ዕጣን፤ ወርቅ ስለሌላም ስጦታዎች በእጭሩ ሆኖ የታሪኩ አጠጣጥ በሚገባ የተብራራ ቢሆንም፤ የኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በአመት ፩ድ/1/ ቀን ፩ድ/1/ ሰአት ብቻ በዕጣን ፈንታ በከርቤ በመጠቀሟ በታሪክ ዘንድ ከዓለም የተለየች እንደሚያደርጋት አይካድም።

ስለ <u>ከርቤ</u> ጥቅሙ በኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ብዙ መሆኑን ከፍ ብሎ በጠቀስኩት መሠረት አሁንም ለመጠቆም ያህል በከፊል ነው፤ የምገልጸው።

1.፩. ከርቤ ፯ቱን/7/ ዓይነት የተለያዩ ቀለማትን

ለማውጣትና /ለመሥራት/፤ ያገለግላል፤

2.፪. <u>ከርቤ</u> የተለያዩ ሥዕሎችን ለመሣል ያስፈልጋል።

3.፫. <u>ከርቤ</u> የተለያዩ የባሕል መድኃኒቶች ለመቀመምና ለመሥራት ያሠምራል፤

4.፬. <u>ከርቤ</u> ሠሣዕናን ማለትም ጥበብና መድኃኒት ያገናል፤ ወዘተርፈ።

ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቀጥተኛ ቤተ ክርስቲያን የብሉይና የሐዲስ ኪዳን <u>የሁለቱም</u> ሕጐች ባለቤትና መሥራች ስለሆነች ከብሉይ ኪዳን ጊዜ ጀምሮ በቤተ ምኩራብና ወይም ቤተ እግዚአብሔር በነዘናቶቿ ዕጣን ታጥን እንደ ነበር ሁሉ፤

አሁንም በሐዲስ ኪዳን ጊዜም ከቀድሞ በበለጠ በዕጣን ጊዜ ብቻ በየቀኑ የሚጸለይ ከብሉይና ከሐዲስ ከተለያዩ መጻሕፍት የተውጣጣ <u>ጸሎተ</u> <u>ዕጣን</u> የሚባል መጽሐፍ በተለይ አጽፋ፤ በመድኀኖና በመጸለይ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ፳፬/24/ ሰአት ሙሉ ታጥናለች ትጸልያለች፤





መሥዋዕተ ቁርባን የነግህና የሠርክ ማለትም የጥዋትና የዘጠኝ ሰዓት ታቀርባለች ነገር ግን ከላይ አስቀድሞ እንደተብራራው ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአመት ፩ድ/1/ ቀን በ፮ ሰአት /6/ የዓርብ ስቅለት ብቻ በዕጣን ፈንታ በከርቤ ታጥናለች።

ብሉይና ሐዲስ የተወሐዱበት ሥርዓት ይህ በእናት ኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ያለው ነው። ዘጸ.ም.፴፥፩-፲፩ /30ቁ.1-11/፤ ዘሌ.ም.፪፥፩-፲፫ /2ቁ.1-5/ ዘሌ.ም.፲፮፥፩-፲፯ /3ቁ.1-17/፤ ሉቃ.ም.፩፥ ፰-፲፫ 1ቁ.8-13/፤ ይመልከቱ።

በዚህ ዓይነት ጥርት ብሎ የተሠራ ነው። የእናት ኢትዮጵያ ቀጥተኛ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ታሪክ እላለሁ።

አይሸር ፩ኛ/1/ ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሔም ሲወለድ የሚያመለክተውን ኮከብ በ፪ሺ፲፪ /2012/ ከ.ፊ /B.C/ እንደተነበየ ሁሉ ቅዱስ ዳዊትም ፩ሺ፭፻፺/1500/ ከ.ፊ /B.C/ ልጁ የዓለም መድኃኒት

የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሔም አውራጃ ሲወለድ እጅ መንሻ የሚያመጡለትን እነማን እንደሆኑ አስቀድሞ ትንቢት ተናግሯል።

ይኸውም የኢትዮጵያ ሰዎች በፊቱ ይሰግዳሉ ማለትም ስመታን ያቀርባሉ፣ ጠላቶቹም አፈርን ይበላሉ፣ ሲል ደግሞ የማያምኑትን ሕዝቦች አህዛብን ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ሰብአ ሰገሎች ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን በሚገባ አረጋግጧል። መዝ.፸፩፣ ቁ.፱-፲፩ /71.ቁ.9-11/ ይመልከቱ።

A.ሀ. ስለዚህ ተርሴስ የተባለችው የዛሬዋ አዶሊስ ስትሆን፣

B.ለ. ደሴቶች የተባሉት ደግሞ በባሕር ውስጥ የሰጠሙትን ሳይቀር ዳሕላቅና ሐኒሽ ናቸው፣

C.ሐ. ምጽዋዕና አሰብ ስማቸው እስከ ዛሬ ድረስ ያልተለወጠ ሲሆን፣

D.መ. በርበራ ደግሞ የጥንቱ የኢትዮጵያ ወደብ የነበረ ጥንቲ ነው፣

E.ሠ. ቀይ ባሕር እንዳለ ሲሆን፣





F.ረ. ዛሬ የሕንድ ባሕር የሚባለው ደግሞ የኢትዮጵያ ባሕር ይባል እንደ ነበር ባይካድም፣

ዓረብ ማለት በቁሙ ዓረቦችን ሲሆን፣ ሳባ ደግሞ ኢትዮጵያ ነው፣ በዚህ ዓይነት መልኩ ጥርት ብሎ የቀረበ ታሪክ ሲሆን፣ ማንም ሰው አጣምሞ ሊያቀርበው አይችልም፣

የሰብአ ሰገሎች ስምና ሀገር ከላይ ከጥያቄ አንድ ጀምሮ በማገባ ተብራርቷል፣ ቢሆንም ከዚህ በላይ ለተጻፈው ሁሉ መልስ የሚሰጠን ተረፈ ዳዊት መሆኑን እጠቁማለሁ። መዝ.፸፩፣ ቁ. ፱-፲፪ /71ቁ.9-12/ መዝ.፻፸፪፣፩-፪/132 ቁ.1-2/ መዝ.፷፯ ቁ.፴፱-፵ /67:29-30/ ይመልከቱ። ዋናው ተረፈ ዳዊት ነው።

| | | |
|---|---|---|
| ዳዊት | ፩፻፶ | - 150 |
| ተረፈ ዳዊት | ፩፻፶ | - 150 |
| መዝ. ዳዊት | ፩፻፶ | - 150 |
| ድምር ፣ | ፬፻፶ | - 450 ነው። |

አነሳስቶ ላስጀመረን አስጀምሮም ላስፈጸመን ለዘላለማዊ የብርሃን አምላክ ለሀያው እግዜአብሔር መድኃኒአለም እየሱስ ክርስቶስ ክብርና ምስጋና ይግባው።

አባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ
፲፱፻፺፭-፲፱፻፺፮ /1995-1996 ዓ.ም./





# ምስጋና

BBC
Television

BRITISH BROADCASTING
CORPORATION
TELEVISION CENTRE
WOOD LANE, LONDON W12 7RJ
TELEPHONE: 0181-7438000
FAX: 0181-576 1157

11 January 1997

Yared Yifru
P.O.Box 90188
Addis Ababa
Ethiopia